አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት
የጆርናሊዝምና ፣የኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍና ፎክሎር
ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የሀድያ ሴቶች የስራ ላይ ዘፈኖች [illegible]

በ

ቀለመወርቅ ተክሌ

ሰኔ 200[illegible]

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# የሀድያ ሴቶች የስራ ላይ ዘፈኖች ትንተና

በ

ቀለመወርቅ ተክሌ

ሰኔ 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የሀድያ ሴቶች የስራ ላይ ዘፈኖች ትንተና


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዚምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር


ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር የ ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

ቀለመወርቅ ተክሌ



ሰኔ 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዚምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የሀድያ ሴቶች የስራ ላይ ዘፈኖች ትንተና

በ

ቀለመወርቅ ተክሌ

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ

ስም ዘሪሁን አስፋው ፊርማ ________ ቀን 27/10/04

የውስጥ ፈታኝ

ስም ________ ፊርማ ________ ቀን ________

የውጭ ፈታኝ

ስም [illegible] ፊርማ ________ ቀን 27/10/04

ሰኔ 2004 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## ምስጋና

በመጀመሪያ ከጥናቱ ርእስ አመራረጥ ጀምሮ እስከ ጥናቱ መጨረሻ ድረስ የመመረቂያ ፅሁፌን ተከታትለው ላረሙልኝ አማካሪዬ ለተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በመቀጠል መረጃን በመስጠት ፈቃደኛ ለሆኑት ለሀድያ ብሄረሰብ አባላት፣በተለይ በሆሳዕና በጤና ተቋም ውስጥ ለሚሰራው ለውድ አብርሀም መጫ ለስራው መሰራት ትልቅ አስተዋፅኦ ያደረገልኝ በመሆኑ፣እንዲሁም ለጥናቱ በተመረጡት በሁለት ወረዳዎች ውስጥ ከእኔ ጋር ገጠር ድረስ በመሄድ ለጥናቱ አጋዥ ይሆናሉ ብለን ያመንባቸውን አቅርቦቶች በማቅረብ ለተባበረኝ ፣ለአዬ መጫ እና ለሲሳይ አበበ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

ዲጂታል መቅረፀ ድምፅ ላዋሰኝ ለውድ ጓደኛዬ ተወልደ ብርሀን፣የተለያዩ መፅሀፍትን ላዋሰኝ ዋልተንጉስ መኮንን፣ እንዲሁም በመቅረፀ ድምፅ እና በቪዲዮ የተሰበሰቡትን የቃል መረጃዎች ወደ ፅሁፍ በመቀየርና ከሀድይኛ ቋንቋ ወደ አማርኛ ለተረጎሙልኝ ፣ጎጋቱ ሀብታሙ እና ደስታ ደርጋሶን ላመሰግናቸው እወዳለሁ።

## አጠቃሎ

በሀዲያ ዞን የሴቶች የስራ ዘፈኖች ላይ እኔ እስከማውቀው ድረስ ከዚህ በፊት የተደረገ ጥናት አላጋጠመኝም።የሀድያ ብሄረሰብ ሴቶች በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎቻቸው ላይ ያዜማሉ ወይም ይዘፍናሉ።በዘፈኖቹ የሚደረድሯቸው ቃል ግጥሞች የተለያዩ ጉዳዮችን የሚያነሱ ናቸው።የዚህ ጥናት ዋና ትኩረትም ቃል ግጥሞቹ የሚያነሷቸውን ጉዳዮች መተንተን ነው።

ጥናቱ አውድ ተኮር በሆነ ትንተና ላይ የተመሰረተ ነው።ለጥናቱ መረጃዎች የተሰበሰቡት በቃለ መጠይቅና በምልከታ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ነው።መረጃ አቀባዮች የተመረጡት በታላሚ የናሙና አመራረጥ ስልት ነው።ጥናቱ ያተኮረባቸው የሴቶች የስራ አጋጣሚዎች ፤ወተት መናጥ፤ ሙቀጫ መውቀጥ፤ስንደዶ መልቀም፤እረኝነት፤እንሰት መፋቅ፤ወፍጮ መፍጨት፤የጓሮ አትክልት መኮትኮት እና እንጨት ለቀማ ናቸው።በእነዚህ የስራ አጋጣሚዎች ላይ በጠቅላላ አንድ መቶ ሀምሳ ስድስት ቃል ግጥሞች ተሰብስበዋል።በመስክ ሴቶቹ ሲዘፍኗቸው የተሰሙት ዘፈኖች ብዛት በየአውዳቸው ሲመደቡም በእንሰት መፋቅ አስራ ሁለት፤በኩትኳቶ ሀያ አምስት፤በስንደዶ ለቀማ አርባ አንድ፤በወፍጮ ሀያ አንድ፤በወተት መናጥ ሀያ ስድስት፤በእንጨት ለቀማ አምስት፤በእረኝነት አስራ ዘጠኝ፤በወቀጣ ሰባት ናቸው።ከነዚህም ግጥሞች ውስጥ አርባ ሰባቱ ቃል ግጥሞች ተመርጠው ተተንትነዋል።በጥናቱ እንደታየው ቃል ግጥሞቹ ገሚሶቹ ከስራው አይነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሲሆኑ ገሚሶቹ ደግሞ የሌላቸው ናቸው።

በዘፈኖቹ የተነሱት ጉዳዮች ስራን ስለመስራት፤የእንሰት ተክልን ስለ ማወደስ፤ስለ እረኛ ፤ስለ ወተት ፤ስለ ዘር ሀረግ ፤ስለ ዝናና ጀግንነት ፤ስለ በሬ ፤ስለ ጨዋታ፤ስለ ጥፈራዎች፤ስለ ውበት አድናቆት፤ስለ ምግብ ዝግጅት፤ስለ ሀድያ ሴቶች ማንነት እና ስለ ከንፈር ወዳጅ ናቸው።

ከጥናቱ እንደተገኘው በስራ ዘፈኖች ውስጥ በመደጋገም የተነገሩት የሴቶቹን በስራ መተባበርና ብርታት የሚየሳዩ መሆናቸውን በመብረቅ እና ጅረት ውሀ ተመስለዋል።እንዲሁም ሴቶቹ የሚመሰሉባቸው የዱር አራዊት እንደ አውራሪስ፤ተኩላ፤አንበሳ እና ነብር መሆናቸው ታውቋል።

## ማውጫ

ገፅ

ምስጋና ........................................................................ I

አጠቃሎ ........................................................................ II

1.መግቢያ ........................................................................ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................................ 2

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ........................................................................ 2

1.3 የጥናቱ አላማዎች ........................................................................ 3

1.4 የጥናቱ ጥያቄዎች ........................................................................ 3

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................................................ 4

1.6 የጥናቱ ወሰን ........................................................................ 4

1.7 የጥናቱ ዘዴ፣ መረጃ አሰባሰብ ፣የናሙና አመራረጥና አተናተን ........................................................................ 5

1.7.1 የአጠናን ዘዴ ........................................................................ 5

1.7.2 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ........................................................................ 5

1.7.3 የናሙና አመራረጥ ........................................................................ 6

1.7.4 የመረጃ አተናተን ........................................................................ 7

1.8 የመስክ ስራ ........................................................................ 7

1.8.1 ከመስክ በፊት ........................................................................ 8

1.8.2 በመስክ ላይ ........................................................................ 8

1.9 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች ........................................................................ 9

1.9.1 ያጋጠሙ ችግሮች ........................................................................ 9

1.9.2 የተወሰዱ እርምጃዎች ........................................................................ 10

1.10 የጥናቱ አደረጃጀት ........................................ 10

2.ክለሳ ድርሳናት ........................................ 11

2.1. የንድፈ ሀሳብ ቅኝት ........................................ 11

2.1.1 የስራ ዘፈን ምንነት ........................................ 11

2.1.2 የቃል ግጥም ........................................ 12

2.1.3 ቃላዊ ክዋኔ ........................................ 13

2.1.4 የቃል ግጥም አውድ ........................................ 14

2.1.5 የስራ ዘፈኖች ጠቀሜታ ........................................ 14

2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........................................ 15

2.2.1 በሀድያ ብሄረሰብ ላይ ያተኮሩ ጥናቶች ........................................ 15

3 .የጥናቱ አካባቢ ........................................ 19

3.1 መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ ........................................ 19

3.2 የሀድያ ብሄረሰብ መተዳደሪያ ........................................ 20

3.3 የማህበራዊ ልማት አገልግሎቶች ........................................ 20

4.ዘፈኖች የተከወኑባቸው የስራ አጋጣሚዎች ........................................ 22

4.1 እንስት መፋቅ (Wees Duugga) ........................................ 22

4.2 የጓሮ አትክልት ኩትኳቶ (Duubbi kaashsha korchimma)........ 25

4.3 ስንደዶ ለቀማ (Migra feerimma ) ........................................ 26

4.4 ወፍጮ (Litimma) ........................................ 27

4.5 ወተት መናጥ (Ado gimmiishshimma) ........................................ 28

4.6 እንጨት ለቀማ (Haqqa feerimma )... ................................ 29

4.7 እረኝነት (Laro allaarimma) ................................ 31

4.8 ሙቀጫ መውቀጥ (tumimma) ................................ 32

5.የስራ ላይ ዘፈኖች ትንተና................................ 34

5.1 በእንስት መፋቅ ላይ የተዘፈኑ................................ 34

5.2 በጓሮ አትክልት ኩትኳቶ ላይ የተዘፈኑ................................ 38

5.3 በስንደዶ ለቀማ ላይ የተዘፈኑ................................ 44

5.4 በወፍጮ ስራ ላይ የተዘፈኑ................................ 51

5.5 በውተት መናጥ ላይ የተዘፈኑ................................ 59

5.6 በእንጨት ለቀማ ላይ የተዘፈኑ................................ 66

5.7 በእረኝነት ላይ የተዘፈኑ................................ 69

5.8 በወቀጣ ላይ የተዘፈኑ................................ 74

ማጠቃለያ................................ 77

ዋቢ ፅሁፎች................................ 80

አባሪ አንድ................................ 85

አባሪ ሁለት................................ 122

አባሪ ሶስት................................ 128

## 1፤መግቢያ

የስራ ላይ ዘፈኖች በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚታወቁ ሲሆኑ እንደ አካባቢው ባህልና ቋንቋ የተለያዩ አከዋወን አሏቸው፡፡የስራ ዘፈኖች የማህበረሰቡን ውስጣዊ እርካታ ለመግለፅ፤ለስራው ማስኬጃ ወይም ማፋጠን ፤ማንነት መገንቢያ ወይም መግለጫ ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው፡፡በኢትዮጵያ የሚኖሩ የተለያዩ ብሄረሰቦች በስራ አጋጣሚዎቻቸው ላይ የሚዘፍኗቸው ዘፈኖች የብሄረሰቡ መለያና መታወቂያ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ሆኖም እነዚህ የስራ ላይ ዘፈኖች የትውልዱን አስተሳሰብ፤አመለካከት እና ጥበብ አቅፈው የያዙ ናቸው፡፡እነዚህ የማንነት መገንቢያ ወይም መቅረጫ የሆኑትን ዘፈኖች በቂ የሆነ ትኩረት በሀገራችን አልተሰጣቸውም፡፡በዚህም የተነሳ የሀድያ ሴቶች የስራ ላይ ዘፈኖች ትንተና በሚል ርዕስ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

የስራ ላይ ዘፈኖች ከማህበረሰቡ አኗኗር ዘይቤ ጋር የተቆራኙ ሲሆኑ የሚዘፈኑበትም አላማ ግላዊ ፍላጎትን ለማንፀባረቅ፤የጋራ የሆነ መስተጋብር ለመፍጠር እና ውስጣዊ ወይም ጥበባዊ ፍላጎቶችን ለማርካት ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ የተቃኙት የስራ ላይ ዘፈኖች የብሄረሰቡን አስተሳሰብ እና አኗኗር የሚያመላክቱ ሲሆኑ ክዋኔውንም ጭምር የሚያሳዩ ናቸው፡፡ጥናቱ አምስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን በመጀመርያው ክፍል የጥናቱ ዳራ፤አነሳሽ ምክንያቶች፤የጥናቱ አላማዎች፤የጥናቱ ጥያቄዎች፤የጥናቱ ጠቀሜታ፤የጥናቱ ወሰን፤የአጠናን ዘዴ፤የመረጃ አሰባሰብ ፤የናሙና አመራረጥ፤የመረጃ አተናተን፤የመስክ ስራ፤ከመስክ በፊት፤በመስክ ላይ፤ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች የጥናቱ አደረጃጀት ይገለፃሉ፡፡ሁለተኛው ክፍል የንድፈ ሀሳብ ቅኝትና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የቀረበበት ሲሆን ሶስተኛው ክፍል ደግሞ የጥናቱን አካባቢ የሚያሳይ ነው፡፡ አራተኛው ክፍል ዘፈኖች የተከወኑባቸው የስራ አጋጣሚዎችን ሲያብራራ በመጨረሻውና በአምስተኛው ክፍል ዘፈኖቹ ትንታኔ የተሰጠባቸው እና የማጠቃለያ ሀሳቦች እንዲሁም አባሪዎችን አካቶ የያዘ ክፍል ነው፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ሀዲያ ዞን በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሚገኝ ሲሆን፣በሰሜን ከጉራጌ ዞን በምስራቅ ከስልጤ ዞን በደቡብ ምስራቅ ከአላባ ልዩ ወረዳ፣ በደቡብ ከምባታና ጠምባሮ ፣በደቡብና ደቡብ ምስራቅ ወላይታ ዞንና ኦሮሚያ ክልል ይዋሰናል።ዞኑ በ10 ወረዳዎችና በአንድ የከተማ አስተዳደር የተዋቀረ ነው።እነዚህም ግቤ ፣ሚሻ ፣ሶሮ ፣ሌሙ ፣አንሌሙ ፣ዱና ፣ምስራቅ ባደዋቾ ፣ምዕራብ ባደዋቾ፣ጎምቦራ ፣ሻሾጎ እና ሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ናቸው።የዞኑ አስተዳደር ዋና ከተማ ሆሳዕና ሲሆን ከአዲስ አበባ ከተማ 230 ኪሎ ሜትር ላይ በስተደቡብ አቅጣጫ ይገኛል።

የሀድያ ብሄረሰብ ታሪኩን፣ ስሜቱን ፣ፍላጎቱን ፣እምነቱን ፣ባህሉን ፣ወጉን፣ልማዱን እንዲሁም አመለካከቱን የሚያንፀባርቅባቸው የተለያዩ የስነ-ቃል ዓይነቶች አሉት።ከእነዚህም መካከል ጥቂቶቹ ተረቶች ፣እንቆቅልሾች ፣አፈታሪኮች ፣የስራ፣የአረም ፣የአጨዳ ፣የውቂያ የምርት መሰብሰቢያ ዘፈኖች ፣የህፃናት ማባበያ ናቸው።

ይህ ጥናት የሚያተኩረው ከስነ-ቃል አይነቶች አንዱ በሆነው የስራ ላይ ዘፈን ሲሆን የሀድያ ሴቶች የተለያዩ ስራዎችን በሚያከናውኑበት ጊዜ የሚያዜሟቸው ቃል ግጥሞች ይተነትናል። የሀድያ ብሄረሰብ ሴቶች በቤትም ሆነ በመስክ የተለያዩ ስራዎችን ያከናውናሉ።ስለሆነም የሴቶች የስራ ድርሻ ወቅታዊ ብቻ ሳይሆን የእለት ተእለት የህይወታቸው አካል ነው።በዚህም ምክንያት በወቅትም ያለወቅትም ሊሰሩ የሚችሉ ሴቶች በመሆናቸው ጥናቱ ሴቶችን ተተኳሪ አድርጓል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

በክፍሉ በተሰጠው የቃል ግጥም ኮርስ ያገኘኋቸው የተለያዩ ፎክሎራዊ እውቀቶች በቃል ግጥም ላይ ይበልጥ እንዳተኩር ገፋፍተውኛል።በዚህም የተነሳ በተለይ ደግሞ ሴቶች በስራ ላይ የሚያዜሟቸው ዘፈኖች ስበውኛል።በዚህ ጉዳይ ላይ ጥናት ለማድረግ ሳንሰላስል የሀድያ ብሄረሰብ ሴቶች በስራ አጋጣሚዎች ላይ በቡድንም ሆነ በግል በመሆን ሀገረሰባዊ ዘፈኖችን እንደሚዘፍኑ የአካባቢው ተወላጆች የሆኑ ጓደኞቼ ጠቆሙኝ።ሌሎች የማውቃቸው ሰዎች ደግሞ በሀድያ ብሄረሰብ ሀገረሰባዊ ዘፈኖች በስራ አጋጣሚዎቻቸው ላይ እንደማይለወጡ አሁን እንደቀሩ ነገሩኝ እኔም የቆመበትን ምክንያት ወይም ችግር

ለማወቅ ካለኝ ጉጉት የተነሳ ጥናቱን ለማካሄድ ተነሳሳሁኝ፡፡ሌላው ደግሞ ከዚህ ቀደም እኔ እስከማውቀው ድረስ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ ጥናት ተጠንቶ ስላላገኘሁ ጥናቱን ለማካሄድ ተነሳሳሁ፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሀድያ ዞን በገጠር ውስጥ በሌሙ ወረዳ፣በአናሌሙ ወረዳ ፣በምሻ ወረዳ እና በጎምቦራ ወረዳዎች የሚኖሩ ሴቶች የተለያዩ ስራዎችን በሚያከናውኑበት ወቅት የሚያዜሟቸውን ግጥሞች ከአውዳቸው መሰብሰብ ፣የስራዎቹን የአከዋወን ሂደት መግለፅ እና ባዜሟቸው ዘፈኖች ውስጥ የሚያነሷቸውን ጉዳዮች መግለፅ እና መተንተን ነው፡፡ከዚህ በመነሳት የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታል፡፡

- የሀድያ ሴቶች የስራ ዘፈኖቹን የሚያዜሙባቸው የስራ አይነቶች ምን ምን እንደሆኑ መለየት፣
- ሴቶች የተለያዩ ስራዎችን ሲያከናውኑ የሚያዜሟቸው ዘፈኖች ምን ምን ጉዳዮችን የያዙ መሆናቸውን ለይቶ መግለፅ እና መተንተን ፣
- ግጥምና ዜማው ከስራው አይነት ጋር ግንኙነት እንዳላቸውና እንደሌላቸው ማሳየት፣
- ሴቶቹ ለራሳቸው የሚሰጡት ግምትና ቦታ ምን እንደሆነና በወንዶችም የሚሰጣቸው ግምት ምን እንደሆነ መግለፅ፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጥያቄዎች

ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡

1. የሀድያ ሴቶች በቡድን የሚያከናውኗቸው አበይት የስራ አይነቶች ምን ምን ናቸው?
2. በሀድያ ሴቶች የስራ ዘፈን ምን ምን ጉዳዮች ይነሳሉ?
3. ዘፈኖቹ ለስራው እና ለሚሰሩት ሴቶች ያላቸው ፋይዳ ምንድን ነው?

4. ሴቶቹ ስለራሳቸው ያላቸው ግምት ምንድነው? በወንዶቹስ አመለካከት እንዴት ይታያሉ?

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል የሚል እምነት አጥኚዋ አላት፡፡

- ሴቶቹ በስራ አጋጣሚዎች ላይ የሚያዜሟቸው ቃል ግጥሞች መሰብሰባቸው ሰፊ ጥናት ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች መነሻ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡
- ሴቶቹ በሚከውኗቸው የስራ አጋጣሚዎች ላይ በሚያዜሟቸው ቃል ግጥሞች ስለራሳቸውም ሆነ ስለአካባቢያቸው ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ ለሚሹ የተወሰነ እውቂያ ይሰጣል፡፡
- የሀድያ ሴቶች የህይወት ፍልስፍናን ለመጠቆም እንዲሁም የሴቶችን ጉዳይ ለሚከታተሉ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት መረጃ ይሰጣል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በሀድያ ዞን ከሚገኙ አስር ወረዳዎች በአራቱ ብቻ ነው፡፡ በናሙናነት የተመረጡት ወረዳዎች ሊሙ፣አንሌሙ፣ምሻ እና ጎምቦራ ናቸው፡፡ ጥናቱ በእነዚህ ወረዳዎች የተወሰነበት ምክንያት ለጥናቱ ከተመደበው ጊዜ አንፃር ሁሉንም ወረዳዎች ለመሸፈን ባለመቻሉ ነው፡፡በዚህ ጥናት የሚተኩረው በስራ ግጥሞቹ ውስጥ በሚንፀባረቁት ጉዳዮች ላይ ብቻ ነው፡፡

ይህ ጥናት ይዞት ከተነሳው አላማ አንፃር የቃል ግጥም አይነቶች አደራረሳቸውን ፣ስልታዊና ቅርፃዊ መልካቸውን አይዳስስም፡፡

## 1.7 የጥናቱ ዘዴ፣የመረጃ አሰባሰብ፣የናሙና አመራረጥና አተናተን

ይህ ክፍል የጥናቱን የአጠናን ዘዴ፣የመረጃዎች አሰባሰብ፣የናሙና አመራረጥ፣እና አተናተንን አካቶ የያዘ ነው፡፡

### 1.7.1 የአጠናን ዘዴ

የሀዲያ ሴቶች የስራ አከዋወንና ዘፈኖቻቸው ላይ ተገቢ የሆኑ መረጃዎችን አሰባስቦ ለመግለፅና ለመተንተን እንዲያስችል ገላጭ የምርምር ዘዴን ተጠቅሜያለሁ፡፡‹‹A descriptive Study is "Concerned With and designed only to describe…"በዚህም መሰረት ጥናቱ የሚያተኩረው አውድ ተኮር በሆነ የአጠናን ዘዴ ላይ ነው፡፡ አውድ ተኮር ያጠናን ስልት ሴቶቹ ባዜሟቸው ዘፈኖች ውስጥ ምን ምን ጉዳዮች እንደተነሱ ከማህበራዊ፣ ባህላዊ እና አውዳዊ አንፃር ለማጥናት ያስችላል፡፡ Bauman (1983 ፣362) እንደሚሉት የቃል ግጥም መገኛ ወይም መፈጠሪያ ከሆኑት ማህበራዊና ባህላዊ መቼቶች አንፃር መጠናትና መተንተን ያለባቸው መሆኑን በመግለፅ የአውድ ተኮር አጠናንን አስፈላጊነት አመልክተዋል፡፡

### 1.7.2 መረጃ አሰባሰብ

በዚህ ጥናት የተሰበሰቡት መረጃዎች ከካልአይ እና ከቀዳማይ ምንጮች ናቸው፡፡ካልአይ ምንጮች ከመፃህፍት ከተለያዩ ጥናታዊ ፅሁፎች የተገኙ ናቸው፡፡እነዚህም ምንጮች ጥናቱን ስርአት ለማስያዝ ፣ለማደራጀት እና በንድፈ ሀሳብ መሰረት ለመተንተን እና ለመግለፅ አገልግለዋል፡፡

ቀዳማይ ምንጮቹ የተለያዩ የስራ አይነቶች የተከወኑባቸው ተፈጥሯዊ መቼቶችን ከመስክ የተገኙ ዘፈኖች (ቃል ግጥሞች) እና መረጃ አቀባዮችን ያካትታሉ፡፡እነዚህም ምንጮች በቦታው ተገኝቶ  የስራ ዘፈኖችን አጋጣሚዎች እና አውዳዊ መረጃዎች ለመሰብሰብ ለማደራጀት፣ለመግለፅና ለመተንተን አገልግለዋል፡፡

መረጃዎቹም በቪዲዮ ፣በካሜራ እና በቴፕ ሪከርደር እንዲሁም በማስታወሻ የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ከመስክ የተገኙ መረጃዎችን በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች መሰብሰብ ለመፃፍ

አስቸጋሪ የሆኑትን ሁነቶች ከአውዱ በቀጥታ ለመሰብሰብ ያስችላል።Okpewho (1992 ፣63-64 )

በመስክ መረጃን ለመሰብሰብ የሚያግዙን የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ የተባሉት መሆናቸውን Goldsteine (1964፣79) እና ፈቃደ አዘዘ (1991፣91-96) ገልፀዋል።በመሆኑም እነዚህን ዘዴዎች በመጠቀም ጥናቱ ተካሂዷል።

እንደ Goldsteine (1964፣77) አገላለፅ በፎክሎር ጥናት ከመስክ መረጃዎችን በቀጥታ ማግኘት የሚቻለው ምልከታ የተባለውን ዘዴ በመጠቀም በቦታው በመገኘት ጉዳዩን በማየት እና በመስማት ነው። እኔም በቦታው በመገኘት በምልከታ መረጃ ሰብስቤአለሁ።

አንዳንዶቹ የሴቶች የስራ ዘፈኖች ወቅታዊ በመሆናቸው መረጃ ለመሰብሰብ በሄድኩበት ጊዜ ተፈጥሯዊ መቼታቸው በማለፉ ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት በማዘጋጀት መረጃ ሰብስቤአለሁ።

ቃለ መጠይቅ ለአንድ ጥናት አስፈላጊ መረጃ ለማግኘት ቁልፍ ሚና ይጫወታል።ስለዚሁ ጉዳይ ፈቃደ አዘዘ (1991 ፣96-98) አጥኚዎች ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ ለማወቅ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ዘዴ ነው በማለት ገልፀዋል።በዚህም መሰረት ለጥናቱ እገዛ የሚያደርጉ ሰዎችን በመምረጥ በቃለመጠይቅ መረጃ ተሰብስቧል።

በቃለመጠይቅ ያጣኋቸውን መረጃዎች ለማግኘትና እርግጠኛ ያልሆንኩባቸውን ጉዳዮች ለማረጋገጥ የተተኳሪ ቡድን ውይይት አድርጌያለሁ።ውይይቱም በምሻ እና በጎምቦራ ወረዳዎች ላይ የተካሄደ ሲሆን በእያንዳንዱ ቡድን አራት ሴቶችና ሶስት ወንዶች ተሳትፈዋል።

### 1.7.3 የናሙና አመራረጥ

በሀድያ ዞን ከሚገኙት አስር ወረዳዎች መካከል ለጥናቱ የመረጥኳቸው ወረዳዎች ሊሙ ፣አናሌሙ፣ምሻ እና ጎምቦራ ናቸው።የእነዚህ ወረዳዎች የተመረጡበት ምክንያት በወረዳዎቹ ውስጥ የሚኖሩ ተወላጆችን በማወቄ ነው።አንድ አጥኚ የመስክ ስራውን ሳይጀምር በፊት ስለሚሄድበት ቦታ እና መረጃን ስለሚሰጠው ሰው በቅድሚያ ማወቅ አለበት።ስለዚሁ ጉዳይ(Kumar 1991፣162) አንድ አጥኚ በቂ መረጃዎችን በእንዴት ባለ

ሁኔታ እና ከማን ማግኘት እንደሚችል አላማ ይዞ መውጣት እንዳለበትና አላማውን ከግብ የሚያደርስበት (Purpose sampling ) የተባለውን አካሄድ መጠቀም እንዳለበት በፅሁፋቸው ይገልፃሉ።ሴቶች ከሚሰሯቸው ስራዎች መካከል ስምንት የስራ አይነቶች ተመርጠዋል።እነዚህን የስራ አይነቶች የመረጥኩበት ምክንያት የስራ አጋጣሚዎቹ ላይ የሚያዜሟቸው ዘፈኖችን በቀላሉ ማግኘት እንደምችል በመረጃ ሰጪዎቹ አማካይነት ስለተረዳሁ ነው።

## 1.7.4 የመረጃ አተናተን

ዘፈኖቹ በስራው አይነት ፣ከዋኞቹም ከሚሰጡት ምላሽ እና በአውዳቸው ተመድበው ተተንትነዋል። በሴቶቹ የተከወኑት ዘፈኖች በአባሪው ገፆች ላይ በተራ ቁጥር የተዓፉ ሲሆኑ በግራው በኩል በላቲንኛ ፊደል፣በግራው ትይዩ ደግሞ የአማርኛው ትርጉም ተፅፎ ቀርቧል።በተራ ቁጥሮች ከተፃፉት ዘፈኖች መካከል በቅንፍ ውስጥ የገቡት የዘፈን ቁጥሮች ትንታኔ የተሰጠባቸው ግጥሞች መሆናቸውን ይጠቁማሉ።ትንታኔ የተሰጠባቸው ግጥሞች ከላይ በላቲንኛው ፊደል ከስር ደግሞ በአማርኛው ትርጉም ተፅፈዋል።

በአውዱ ላይ ሆነው ክዋኔውን የከወኑት የሴቶች ስም እንደሚከተለው ተገልጿል። አንዳንዶቹን በስማቸው፣አቀንቃኟ እና አቀንቃኞቹ በማለት ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል። የተዘፈኑት ዘፈኖች የከዋኙቹን የህይወት ገፅታ ሙሉ በሙሉ ባይገልፁም እንኳን ከገሀዱ አለም ሁነቶች አንፃር ትንታኔዎች ተሰጥቶባቸዋል።

በዚህ ጥናት አውድ ላይ ክዋኔውን የከወኑት ሴቶች ትክክለኛው ስማቸው እንዲፃፍ ለማይፈልጉት በአጥኚዋ በተሰጡ መጠሪያ ስሞች ተጠቃሽ ሆነዋል። በአጥኚዋ የተሰጠው ስያሜ በአካባቢው የስም አሰያየም ልማድ መሰረት ነው።

## 1.8 የመስክ ስራ

በዚህ ክፍል ከመስክ በፊት እና በመስኩ ላይ የተከናወኑ ተግባራት እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

### 1.8.1 ከመስክ በፊት

ከመስክ በፊት ከተከናወኑት ስራዎች መካከል የመጀመሪያው ካልአይ ምንጮችን በመሰብሰብ ማንበብ ነው። ለዚህ ጥናት ቅርበት ያላቸው ጥናታዊ ፅሁፎች ተነበዋል። ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ነድፌ ሀሳቦች ተዳሰዋል። አዲስ አበባ ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች አማካይነት ተጠኚ አካባቢውንና ህዝቡን ከሚያውቁ ሰዎች ጋር ተዋውቄ ላጠና ስለፈለኩት ጉዳይ በመንገር አንዳንድ መረጃዎችን ማለትም የሴቶች የስራ ላይ ዘፈኖች ዛሬም ድረስ መኖራቸውን ገልፀውልኛል።ለጥናቱ የሚያስፈልጉትን ለምሳሌ መቅረፀ ድምፅ ፣ቪዲዮ ካሜራ እና ፎቶ ካሜራ የመሳሰሉትን አዘጋጀሁ።በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በስድስት ኪሎ ግቢ የሚማሩ የአካባቢው ተወላጅ ከሆኑት ተማሪዎች ጋር በመተዋወቅ እና በመወያየት መረጃዎችን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል አቀድሁ።ከዚያም ለመጀመሪያ ጊዜ የጥናቱን አካባቢ ለማወቅ እና መረጃ አቀባዮቼን ለመተዋወቅ ሆሳዕና ከተማ በመሄድ በዞኑ አስተዳደር ፅህፈት ቤት በመሄድ አቶ ኤርሲዶ አንታሴ እና ሳሙኤል ዘመድኩንን መረጃዎችን እንዴት ማግኘት እንደምችል አነጋግሬ እነርሱም መረጃ የማገኝበትን ቦታ በመጠቆም ፍንጭ ሰጥተውኛል።ከዚያም በተያዘው እቅድ በመመራት የመስክ ስራው ተጀመረ።

### 1.8.2 በመስክ ላይ

የመጀመሪያውን የመስክ ጉዞ ዓርብ ጥር 4፣2004 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ወደ ሆሳዕና አደረግሁ።በማግስቱ ቅዳሜ ጥር 5 ፣2004 ዓም በመስክ ረዳቴ አማካይነት ወደ ዞኑ መስተዳድሩ ፅህፈት ቤት በመሄድ የመንግስት ግንኙነት መምሪያ ሀላፊ የሆኑትን አቶ ሳሙኤል ዘመድኩን እና የባህል ቱሪዝም ሂደት አስተባባሪ ለሆኑት ለአቶ ኤርሲዶ አንቶሴ ስለ ጥናቱ አላማ ማብራሪያ ሰጠሁ።እነርሱም በምን አይነት ሁኔታ ማካሄድ እንዳለብኝ በመግለፅ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ሊሆኑኝ ከሚችሉት ግለሰቦች ጋር አስተዋወቁኝ።

ጥናቱ ሊካሄድ ከታሰበባቸው ወረዳዎች አንዱ በሆነው በሌሙ ወረዳ ሹርሞ ቀበሌ ውስጥ ነዋሪዎች የሆኑት ሴቶች በእንስት መፋቅ ላይ ያዜሟቸውን ዘፈኖች በመቅረፀ ድምፅ እና በቪዲዮ መቅረፅ ችያለሁ።

ሁለተኛው ጉዞ እና የመስክ ስራው የተካሄደው ከ የካቲት 4 እስከ የካቲት 14፣2004 ዓ.ም ባሉት ቀናቶች ውስጥ ነው፡፡በነዚህም ቀናቶች ውስጥ ጥናቱ ሊካሄድባቸው በተመረጡት አራቱም ወረዳዎች ውስጥ ሴቶች በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎቻቸው ላይ የሚያዜሟቸው የቃል ግጥሞች እንዲሁም ጭፈራዎች በቪዲዮ ካሜራ በመታገዝ ተቀርፀዋል፡፡

ሶስተኛው ጉዞ እና የመስክ ስራው የተካሄደው ከ የካቲት 18 እስከ መጋቢት 1፣2004 ዓ.ም ባሉት ቀናቶች ውስጥ ነው፡፡በነዚህ ቀናቶች በአራቱም ወረዳዎች ውስጥ በሚኖሩ ሴቶች የተከወኑት ክዋኔዎች፣እንዲሁም የጥናቱን አላማ ለማሳካት የሚረዱ ዘፈኖች እና አውዳዊ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

## 1.9 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች

### 1.9.1 ያጋጠሙ ችግሮች

የመጀመሪያው ችግር ለምርምር በተመረጡት ወረዳዎች አካባቢ ላይ ዘፈኖቹ የሚዘፈኑበት የስራ አጋጣሚ ወቅት በማለፉ ነው፡፡ለምሳሌ የስንደዶ ለቀማ የሚካሄድበት ወቅት በጥቅምት በመሆኑ ነበር ፡፡

ሁለተኛው ችግር ከታሳቢ መረጃ አቀባዮች እምነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ለጥናቱ በተመረጡት ወረዳዎች ውስጥ ነዋሪ በሆኑት ማህበረሰብ መካከል አብዛኛዎቹ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች በመሆናቸው ምክንያት በስራ አጋጣሚዎቻቸው ላይ መዝፈን የማይገባ ተግባር በመሆኑ መረጃ አቀባዮችን ማግኘት አለመቻል ነበር፡፡

ሶስተኛው ችግር ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ጋር ተያይዞ የመጣ ነው፡፡ለጥናት የተመረጡት ወረዳዎች የገጠር አካባቢ በመሆናቸው የኤሌክትሪክ ስርጭት ባለመኖሩ ምክንያት የቪዲዮ ካሜራ ባትሪ ለመሙላት አስቸጋሪ ነበር፡፡ስራውን ጀምሬ ባትሪው ካለቀ ወደ ከተማ ተመልሼ መሄዱ አንዱ ችግር ነበር፡፡ከከተማ ተመልሼ እስክመጣ ድረስ የሰዎቹ ስሜት እንደ መጀመሪያው ባለመሆኑ መረጃ ለማግኘት አስቸጋሪ ነበር፡፡

ሌላው ሴቶቹ ድምፃቸውም ሆነ ምስላቸው እንዳይቀረፅ ማለታቸው ነው፡፡በዚህም ምክንያት ሴቶቹ በውስጣቸው ያለውን እውነተኛ ስሜቶቻቸውን በነፃነት ለመግለፅ ባለመቻላቸውና የቃል ግጥሞቹ ከአእምሯቸው መጥፋታቸው ነው ፡፡

## 1.9.2 የተወሰዱ እርምጃዎች

የምርምር አላማዬን ለማሳካት እንዲያስችለኝ ዘንድ መፍትሄ ይሆናሉ ብዬ ያመንኩባቸውን ዘዴዎች ሁሉ ተጠቅሜያለሁ፡፡

ተፈጥሯዊ መቼቶች ያለፉባቸውን መቼቶችን ተፈጥሯዊ መቼት በሚመስል መቼቶች በማጀጋጀት በማደራጀት እና በማቀናበር የብሄረሰቡ ዘፈኖች ተሰብስበዋል፡፡

የፕሮቴስታን እምነት ተከታዮች ያልሆኑ ሰዎችን በማፈላለግ ዘፈኖቹ ከነአውዳዊ መረጃቸው ተሰብስበዋል፡፡

በመቅረፀ ድምፁ እና በቪዲዮ ምክንያት ለተፈጠረው ችግር የባህሉ ባለቤት የሆኑትን ከዋኞች መሳሪያው አዲስ ነገር እንዳይሆንባቸው ስለ መሳሪያው ግንዛቤን ለማስጨበጥ እንዲረዳ የተቀረፀውን ምስልና ድምፅ በማሳየትና በማስማት፣ችግሩን ለመፍታት ተችሏል፡፡

## 1.10 የጥናቱ አደረጃጀት

የጥናቱ አደረጃጀት በአምስት ክፍሎች የተከፋፈለ ነው፡፡የመጀመሪያው ክፍል የጥናቱ ዳራ፣የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣የጥናቱ አላማዎች፣ የጥናቱ ጥያቄዎች፣ የጥናቱ አስፈላጊነት ፣የጥናቱ ወሰን ፣ የአጠናን ዘዴ፣የመረጃ አሰባበሰብ ፣ የናሙና አመራረጥ እና የአተናተን ስልትን ያካተተ ነው፡፡ሁለተኛው ክፍል በርዕሰ ጉዳዩ ዙርያ ቀደምት የተሰሩ ጥናቶችንና ለጥናቱ አጋዥ ይሆናሉ ተብሎ የታሰቡትን ንድፈ ሀሳቦች የተቃኙበት ክፍል ነው፡፡ሶስተኛው ክፍል ጥናቱ የሚካሄድበት አካባቢ የጥናቱ አካባቢ፣መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ፣የህዝቡ መተዳደሪያና ማህበራዊ ልማት አገልግሎቶችን አካቶ የያዘ ነው፡፡አራተኛው ከመስክ በተገኙት መረጃዎች ላይ ገለፃ የተሰጠበት ክፍል ነው፡፡አምስተኛው ከመስክ የተሰበሰቡትን ቃል ግጥሞች ትንታኔ የተሰጠበት ነው፡፡ በጥናቱ መጨረሻ ደግሞ ማጠቃለያና የተለያዩ አባሪዎች ቀርበዋል፡፡

## 2፤ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶችና ንድፈ ሀሳቦች ተቃኝተው ቀርበዋል፡፡

### 2.1 የንድፈ ሀሳብ ቅኝት

ይህ ክፍል የስራ ዘፈን ምንነትና ፤ የቃል ግጥም ምንነት፤ዐውድ ፤ ክዋኔ እና በስራ አጋጣሚዎች ላይ የሚዜሙት ቃል ግጥሞች ፋይዳቸው የሚገለፅበት ነው፡፡

#### 2.1.1 የስራ ዘፈን ምንነት

የስራ ዘፈኖች አድካሚና አሰልቺ ስራዎችን በጋራ ለመስራት፤ስራውን በቅልጥፍና ለማከናወን ፤በቡድንም ሆነ በግል የሚዘፈኑ ዘፈኖች ናቸው፡፡የስራ ዘፈኖች አብዛኛውን ጊዜ የሚዘወተሩት አድካሚ በሆኑ የስራ አጋጣሚዎች ላይ ነው፡፡በተለይም የቴክኖሎጂ እድገትና ዘመናዊነት ባልታየበት በገጠሩ አካባቢ በሴቶችና ወንዶች ፤በቡድንም ሆነ በተናጥል ይከወናሉ፡፡ የስራ ዘፈኖች የአንድን ማህበረሰብ የአኗኗር ሁኔታ፤ባህል እና ልማድ የሚገልፁ በመሆናቸው የባህላዊ ዘፈን አካሉች ናቸው፡፡ (Leach፤1949 ፤1181)

የስራ ዘፈኖች በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወኑ ሲሆኑ የመከሰቻ አጋጣሚዎቹም አብዛኛውን ጊዜ እንደ ጀልባ ቀዘፋ፤ውቂያ፤እርሻ የመሳሰሉት አድካሚና አሰልቺ ስራዎች ናቸው ሲሉ Finnegan Ruth (1998 ፤231) ገልፀዋል፡፡

የስራ ዘፈን ሰዎች በቤት ወይም በመስክ ሆነው ስራዎቻቸውን እየሰሩ የሚያዜሙት የስነቃል አይነት ነው፡፡የስራ ዘፈኖች በመጀመሪያ በአንድ ግለሰብ ከተፈጠሩ በኋላ የማህበረሰቡ ሀብት ይሆናሉ፡ይህም የስራ ዘፈን በቃል የሚተላለፍ በመሆኑ በተወሰነ መልኩ ሊለዋወጥ ይችላል፡፡ከዚህም የተነሳ ሴቶችና ወንዶች በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎቻቸው ላይ የሚከውኗቸው ዘፈኖች የተለያዩ ቅርፆች ሊኖሯቸው ይችላሉ በማለት (ዘሪሁን አስፋው፤1992፤46 ) በፅሁፉ ገልጿል፡፡

የስራ ዘፈን በአንድ ዘመን ውስጥ ያለውን ማንኛውም አይነት የህይወት ፍልስፍና፣ባህል፣ኢኮኖሚ፣ማህበራዊና ስዋዊ ጉዳዮችን ሲያንፀባርቅ የሚችል ቃላዊ የጥበብ ስራ ነው፡፡

የስራ ዘፈኖች የሚካሄደውን ስራ በማጀብ ለስራው ማስኬጃና የስራውን አድካሚነት ወይም አስልቺነት በሚሰሩት ሴቶች ስሜት እንዳይሰማቸው ከማድረጋቸውም ባለፈ ስራው እንዲሰራ ያደርጋሉ፡፡ እንዲሁም የስራ ዘፈኖች ለስራው እንደ ትልቅ አቅርቦት በመሆን በመላው አፍሪካ ሀገር ይታመንባቸዋል ሲሉ Finnegan Ruth (1970፣206 ) ጠቅሰዋል፡፡

Finnegan Ruth (1970፣239) ፣ዘሪሁን አስፋው (1992፣28) ፣ፈቃደ አዘዘ (1991፣86) የቃል ግጥሞች ሲከወኑ ከስራው አይነት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ቁርኝት እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡

Finnegan “በጋራ ከሚዜሙ የቃል ግጥሞች መካከል ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የስራ ላይ ዘፈኖች ናቸው፡፡”Barry (1987፣274) ሀገረሰባዊ ዘፈን በሰዎች ልጆች የህይወት ልምምድ ውስጥ በደስታም ሆነ በሀዘንም ሁኔታ የሚፈጠር የሰው ሀብት ነው፡፡

### 2.1.2 የቃል ግጥም

ለቃል ግጥም ብያኔ መስጠት እጅጉን አስቸጋሪ መሆኑ ቢታወቅም ቅሉ አንዳንድ ምሁሮች ከሰጡበት ሀሳብ በመነሳት ቃል ግጥም ማለት እንዲህ ማለት ነው እንላለን፡፡ቃል ግጥም ማለት በቃል ተፈጥሮ ከትውልድ ትውልድ የሚሸጋገር በአብዛኛው ማህበረሰቡ ዘንድ ሊገኝ የሚችል በተለያዩ መልኮች የሚቀርብና ባህላዊ ዘፈኖችን የሚይዝ የስነቃል አይነት ነው፡፡ Finnegan (1970፣22) ቃል ግጥምን በተመለከተ ፍፁምና ግልፅ የሆነ ድንበር ማስቀመጥ የለብንም ሲሉ ዕፈዋል፡፡ቃል ግጥም ማለት አደራረሱ፣ አከዋወኑ፣ ተስተላልፎው እና አቀራረቡ ብዙ ጊዜ በቃል እና በመዜም የሆነ በዘፈን፣ በሙሾ፣ በእንጉርጉሮና በሌሎች ተመሳሳይ ዜማዊ ቅርፆች ውስጥ የሚገኝ ሕዝባዊ ግጥም ነው፡፡”ፈቃደ አዘዘ (1991፣86)፡፡

### 2.1.3 ቃላዊ ክዋኔ

ክዋኔያዊ ትወራ ቃላዊውን ክዋኔ ለማጥናት በጣም ጠቃሚ የሆነ ዘዴ ነው። ይህም አካሄድ አውዳዊ ዘዴ በመባል ይታወቃል። አንድ ሰው በውስጡ ያሰበውን ቃል በአንደበቱ ካልተናገረው በአድማጩ ዘንድ እውቅና እንደማያገኝ ሁሉ በቃል የሚነገር ወይም የሚዜም በክዋኔ እስካልታየ ድረስ አይታወቅም። "For Oral Literature the basic existence is performance." Abrham Rogers (1968፣107) ለአንድ ቃላዊ ዕሁፍ መሰረታዊ ህልውናው ክዋኔ ነው ሲሉ ጠቅሰዋል ።ሴቶች በቤት ውስጥም ሆነ በውጭ በሚሰሯቸው የስራ አጋጣሚዎች ላይ የሚያዜሟቸው የቃል ግጥሞች መኖራቸው የሚታወቀው ሲከወኑ ብቻ ነው።

ስለ ቃል ግጥም ህልውና "It is Practice and Performed in Many Areas of the World." በብዙ አገር የቃል ግጥም ክዋኔ በመኖሩ ህልውናውን እንዲያስጠብቅ አድርጎታል ይሁንና እንዲህ ነው በማለት ቁርጥ ያለ ድንበር የማይበጅለት መሆኑንም ጠቅሰዋል። Finnegan (1977፣3)

የቃላዊ ግጥም አከዋወን ስንል አፈፃፀሙን ነው። ፎክሎሩ ተግባቦትን የሚፈጥርልን ሲከወን  ነው። በሴቶቹ የሚዘፈኑት ዘፈኖች የመከወኛ ወቅት፣ ቦታና አጋጣሚዎች ያስፈልጋቸዋል። አንዳንድ ጊዜ በተመሳሳይ የስራ አጋጣሚዎች ላይ የሚዜሙት ዘፈኖች እንደ ሁኔታው ሊለያዩ ይችላሉ።

> Performance differ from One other,depending on such factors as the Age and energy of the Performer, the nature of the Occasion (death or merriment), the type of setting (Cult enclave or open square), wther or not any musical whether it is a solo or a group act. Okpewho፣ (1992 ፣42).

አንዱ ክዋኔ ከሌላው ክዋኔ በተለያዩ ምክንያቶች ሊለያይ ይችላል። ከእነዚህም ውስጥ የከዋኙ ዕድሜና ጉልበት፣ የክዋኔው ባህሪይና አይነት (ለሐዘን ወይም ለደስታ መሆኑ)፣ የአካባቢው ሁኔታና አይነት (ሀይማኖታዊ ስፍራ ወይም ደግሞ ግልጥ አደባባይ መሆኑ)፣

ሙዚቃዊ መሆኑና አለመሆኑ፣ የግለሰብ ወይም የቡድን ስራ መሆኑና አለመሆኑ...ወዘተ ናቸው።

### 2.1.4 የቃል ግጥም አውድ

ሴቶች በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይ የሚዘፍኗቸው ዘፈኖች ምን አይነት መልእክት እንዳላቸው ለማወቅ የሚያስችለን ስራው በሚካሄድበት ቦታና ወቅት ላይ በአካል ተገኝተን አውዱን በመመልከትና በመስማት ነው።ስለዚሁ ጉዳይ Goldstein(1970፣270) ተፈጥሯዊ መቼቱን መፍጠር የሚያስችል ወይም ተሳታፊዎችን የሚያነሳሱ ሁኔታዎችን መፍጠር ያስፈልጋል። Dundes (1965፣278) አክለውም ሁሉንም ነገሮች ወይም ጉዳዮች በአውድ ብቻ እንረዳቸዋለን ማለት አይደለም።

Dan ben Amos(1982፣216-218) Contextual Analysis ስለ አውዳዊ ትንተና በዝርዝር ፣ማህበራዊ አውድ ወይም ጠባብ አውድ ፣ባህላዊ አውድ ወይም ሰፊ አውድ፣ሁኔታዊ አውድ በማለት ገልፀዋል።ማህበራዊ አውድ ስለሴቶች ቡድን አደረጃጀትና በስራ ላይ የሚዜሙትን ዘፈኖች እንዲሁም በከዋኞችና በተመልካቾች መካከል ያለን ግንኙነትን ሲያጤን ሁኔታዊ አውድ ደግሞ ሴቶች ለሚያዜሟቸው ዘፈኖች መከወን መንስኤ የሆኑ አጋጣሚዎችን ያብራራል። እንዲሁም ስራው በማን እንደተሰራና ፣መቼቱን ሁኔታውን ይመለከታል።ስለዚሁ ጉዳይ ደግሞ Dundes(1965፣279) ‹‹የቃል ግጥሞችን ሀሳብ በሚገባ ለመረዳት መንስኤያቸው የሆኑትን አውዳዊ ቅርፆች መመልከት እንዳለብን ጠቅሰዋል።››

### 2.1.5 የስራ ዘፈኖች ጠቀሜታ

Finnegan (1977፣3) አስተያየትና አባባል ሴቶች ማንኛውንም ስራ በሚሰሩበት ጊዜ የሚያዜሙት ዘፈን በአካላቸውና በመንፈሳቸው የሚሰማቸውን ድካማቸውን ይቀንስላቸዋል።የቃል ግጥሞቹ በከዋኞቹ ስነ ልቦና ላይ የማዝናናት ሚናዎችን ይጫወታሉ።ዘሪሁን አስፋው ፣(1992፣46)፣ፈቃደ አዘዘ፣(1991፣18)። እንዲሁም በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሴቶች በሚዘፍኗቸው ዘፈኖች አማካይነት የአንድ ቡድን አባል ከማድረጉም ባሻገር እንደ መረጃ አሰራጭ ተደርገው ይታሰባሉ። Finnegan (1977፣3)

የስራ ላይ ዘፈኖች ለከዋኞቹ የሚሰጡት ጥቅም በስራው ክብደት ምክንያት ለሚሰማቸው የሰውነት ድካምና መዛል ብርታት ይሰጣቸዋል።Okpewho (1992፣106 ) ፊቃደ (1991፣17) እንዲሁም ዘሪሁን (1992፣46) የስራን ዘፈን ጥቅም የማዝናናት ሚናዎች እንዳሏቸው ገልፀዋል።የሰው ልጆች ስራን እንዲሰሩ እንዲሁም የውስጥ ስሜቶቻቸው እንዲበረቱና በውጪው የሰውነት ክፍሎቻቸው እንዲታገዙ ያደርጋል።"Each Of these songs clearly reveals some spirit of competion."Okpewho (1992፣ 111) በስራ ወቅት የሚዜሙት ዘፈኖች የውድድር መንፈስን ያጭራሉ።በማለት በፅሁፋቸው ገልፀዋል።

የስራ ዘፈኖች ሴቶች በስራ ጫና ምክንያት የሚፈጠርባቸውን ድካም እና መሰላቸት ከማስወገዳቸውም በላይ በባህሉ በሴቶች ሊባሉ ወይም ሊነገሩ የማይደፈሩ ጉዳዮችን የሚናገሩባቸው ነፃ መድረኮች ናቸው ።በሴቶቹ ስሜት ውስጥ ያለን ነቀፌታ፣ሀዘን፣ ደስታ፣ ፍቅር ወዘተ.የመሳሰሉትን በስራ ዘፈኖች አማካይነት ሊነገሩ ስለሚችሉ የስራ ዘፈኖች ጠቀሜታ ከፍ ያለ ነው ።

## 2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንኡስ ርእስ ስር ተጠናቅረው የቀረቡት ቀደምት የምርምር ስራዎችና ለጥናቱ እገዛ ያደረጉ ንድፈ ሀሳቦች ናቸው።

የጥናቱ ቅኝት በዋናነት በሀድያ ላይ በተሰሩ ጥናቶች ላይ ያተኩራል። በተጨማሪም ከእኔ ጥናት ርዕስ ጉዳይ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጥናቶች ይመለከታል።

### 2.2.1 በሀድያ ማህበረሰብ ላይ ያተኩሩ ጥናቶች

በዚህ ክፍል የሚቀርበው ቅኝት በሀድያ ብሄረሰብ ላይ የተደረጉ ጥናቶች እና ከእኔ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገናኙት ጥናቶች ላይ ብቻ ይሆ ነው።

Ulrich Braukamper (1973) "The Correlation of Oral Traditions and Historical Records in Southern Ethiopia A Case Study of the Hadiya-Sidama Past." በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት በዋናነት ባለፉት ዘመናት በሀድያ ሲዳማ የነበሩትን ቃላዊ ባህልና ታሪካዊ አመጣጡን እንዲሁም አሁን ያለበትን ሁኔታ የሚያትት ነው።ሁለታችንም የምንመሳሰልበት ጉዳይ ስለ ቃላዊ ባህል ማንሳታችንና ጥናታችን በሀድያ ዞን ላይ

ማተኮሩ ነው። የምንለያይበት የምናጠናው ጉዳይና ነገሮችን የምናይበት መነፅር ነው።እኔ ከፎክሎር አንፃር የማህበረሰቡን ባህል፣ አስተሳሰብ ፣እምነት ፣ምኞት ፣ደስታና ሀዘን ወዘተ. ያሉትን ጉዳዮች ደርቤ ስመለከት እሳቸው ግን ባህሉን ከታሪክ አኳያ የተመለከቱት በመሆኑ ነው።

አስቴር ሳሙኤል በ (1974 ዓ.ም.) ‹‹የሀዲያ ብሄረሰብ የዘፈን ግጥሞች ››በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ዕሁፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ባቀረበችው ጥናታዊ ፅሁፍ 178 ግጥሞች ሰብስባ።የግርዘት፣የሰርግ ፣የስራና የአብዮታዊ ዘፈን ግጥሞች በማለት ከፋፍላ ከቅርፅና ከይዘት አንፃር ትንታኔ ሰጥታለች። በስራ ላይ የተዘሙት ዘፈኖች ጭብጦች ስለ ገበሬዎች ስራ መሄድና መምጣት ፣ስለ ሰነፍና ጎበዝ ገበሬዎች፣ስለ ሴቶች ነቀፌታና ውዳሴ የሚገልፁ መሆናቸውን አሳይታለች።

አስቴር ከጠቀሰቻቸው የዘፈን ግጥሞች መካከል አንዱ የስራ ላይ ዘፈን መሆኑ፣የሷ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል ልዩነቱ ደግሞ በእሷ ጥናት ግጥሞቹ ከቅርፅና ከቋንቋ አንፃር መተንተናቸውና ግጥሞቹ በሁሉቱም ፆታ የሚዜሙ መሆናቸው ነው።

ሻውል በቀለ (1989 ዓ.ም.) ‹‹የሀዲያ ወጣቶች የከንፈር ወዳጅ የዘፈን ግጥሞች ጥናት››በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ አቅርቧል።ጥናቱ ያተኮረው የዘፈን ግጥሞችን በመሰብሰብ ከይዘትና ከቅርፅ አንፃር መተንተን ላይ ሲሆን ግጥሞቹን የይዘት ትንተና አድርጓል። የግጥሞቹ ይዘት ፍቅር፣ ውዳሴ፣ነቀፋ ፣ፅናት፣ዕምንት፣ዘር፣ውበትንና ሀብትን የሚያወሱ በማለት ከፋፍሏቸዋል። የግጥሞቹ መከሰቻ አውዶችም በሰርግ ዋዜማና በሰርግ እለት ፣በስጦታ ቀን ፣ መሳሳሚያ ቦታ ፣አከርማ ሲቆጭ ፣ስፌት ሲሰፋና ምግብ ቤት ውስጥ መሆናቸውንም ጠቋሟል።

የሁለታችንም ጥናት ርዕስ የዘፈን ግጥሞችን የሚመለከት በመሆኑ እንመሳሰላለን ። ሻውል ግጥሞቹን ከቅርፅ አኳያ የተመለከተበት ሲሆን እኔ ደግሞ በዘፈኖቹ ውስጥ የተነሱትን ጉዳዮች በመፈተሽ፣በተጨማሪ የእኔ ጥናት የሴቶች የስራ ዘፈን ላይ ሲሆን የእሱ ደግሞ በሁለቱም ፆታ የሚዜሙ በመሆኑ እንለያያለን።

ሌላው ጥናት የ Ulrich Braukamper and Tilahune Mishago (1999) "Praise and Teasing:Naratives Songs of the Hadiyya in Southern Ethiopia." በሚል ርዕስ

ያቀረቡት ነው።ጥናቱ መግቢያው ላይ የሀድያን መልክዓ ምድር አቀማመጥ፣ታሪክ፣ኢኮኖሚ፣ማህበረሰባዊ አሰፋፈር እና ማህበራዊ ባህላዊ እምነቶች ተገልጿል።የማህበረሰቡን ባህልና ታሪክ ከማጥናታቸውም ባሻገር በዋናነት ትኩረት ያደረጉት በቀብር ስነስርአትና በሽክላ ስራ ወቅት በሚዜሙ የሀድያ ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ዘፈኖች ላይ ነው።

ከ Ulrich Braukamper እና Tilahune Mishago ጋር ያለኝ ተመሳስሎ ከሌሎች አጥኚዎች አንፃር ሲታይ የጎላ ነው።ይኸውም በሀድያ በተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ ስለሚዘፈኑ ባህላዊ ዘፈኖች ላይ ማተኮራችን ነው።ዘፈኖቹ የተሰበሰቡበትም መንገድ ያመሳስለናል።ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት የሚለየው በሚጠኑት ጉዳዮች በምናይበት መነፅር ነው።እኔ ከፎክሎር አንፃር የማህበረሰቡን ባህል፣ አስተሳሰብ ፣እምነት ፣ምኞት ፣ደስታና ሀዘን የመሳሰሉትን ጉዳዮች ደርቤ ስመለከት እነርሱ ግን ባህሉን ከታሪክ አኳያ ነው የተመለከቱት ።

Gedion Addise (1999 ) "A Socio-Economic and Cultural History Of The Hadiyya (1941-1991)." በሚል ርዕስ ለታሪክ ትምህርት ክፍል ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ አቅርቧል።በዚህ ጥናት ዘፈኖች፣ግጥሞች፣ዳንሶች፣ጨዋታዎችና የሙዚቃ መሳሪያዎች ተተኩሮባቸዋል።በጌዲዮን ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ ባህላዊ ዘፈኖች በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎች ላይ ማለትም በግብርና ፣በቤት ስራ፣በእንስት ፍቀት ና በልደት ግብዣ በምግብ ዝግጅት እንደሚከወኑ ተገልጿል።ዘፈንና ግጥሞቹ ደግሞ ፣የስራ ዘፈኖች ፣ባህላዊ የፋንዳኖ ዘፈኖች ፣ለአዲስ መሪዎች የተዘፈኑ ዘፈኖች፣የቀብር ስርአት ዘፈኖች፣ የሰርግ ዘፈኖች ፣የጦርነት ዘፈኖች ና በተለያዩ በአላት ጊዜ የሚዜሙ ተብለው ተጠቅሰዋል።ከጌዲዮን ጥናት ጋር የእኔ ጥናት የሚመሳሰለው ቃላዊ ግጥሞችን ከነአውዳቸው በማየቱ ነው።ልዩነታችን አተያያችን ነው። ጌዲዮን በዋናነት ያተኮረው የሀድያ ህዝብ ኢኮኖሚያዊ ና ባህላዊ ታሪክ ሰብስቦ ማስቀመጥ ላይ ሲሆን የእኔ ደግሞ የማህበረሰቡ በስራ ዘፈኖች አማካይነት የሚታየውን ፎክሎራዊ ገፅታ መተንተን ነው።

አዳነች ካሳ ( 2001 ዓ.ም.)‹‹የሀድያ ሴቶች በቡድን በሚከውኗቸው ተግባራት ላይ የተመሰረተ ቃላዊ ባህል ጥናት›› በሚል ርእስ በ 2001 ዓ.ም. ለኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ክፍል ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ አቅርባለች።የዚህ ጥናት ዋና አላማ ቁሶችን

ከቁስንታቸውና ከባህል መገለጫቸው አንፃር ትንታኔ ማቅረብ፤በቁሶችና በሀድያ ሴቶች መካከል ያለውን ግንኙነት አጉልቶ ማሳየት ነው፡፡

ጥናቱ በሶስት የክወና ቡድኖች በተከወኑ አራት ቁሶች ላይ የተመሰረተ ትንታኔ አድርጓል፡፡ሁለት ሀገረሰባዊ ምግቦች፣ሁለት ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ የጆባ ምንጣፍና የስፌት ቁሶች ላይ ነው፡፡ቁሶቹ ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ፋይዳ ተጠቅሷል፡፡የእኔና የእሷ ጥናት የሚመሳሰሉት ሁለታችንም በስራ አጋጣሚዎች ላይ ማተኮራችን ነው፡፡ልዩነታችን ደግሞ የእኔ ጥናት ትኩረት ቁሶች ላይ ሳይሆን በስራው ላይ በሚዜሙት ግጥሞች ላይ መሆኑ ነው፡፡

ከሀድያ ውጭ በሌሎች አካባቢዎች በሴቶች የስራ ላይ ዘፈኖች የተደረጉ ጥናቶች ተመልክቻለሁ፡፡እነዚህ ስራዎች በሴቶች የስራ ዘፈኖች ላይ የተሰሩ በመሆናቸው ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ህዝበ አዳም ገላ(1986) ‹‹የደጀን ሴቶች የስራ ላይ ዘፈን››፣ዘሀራ ሰይድ(1992 ) ‹‹የደሴ ዙርያ ሴቶች የስራ ላይ ግጥም››፣አመነ ወርቁ (1993) ‹‹በቾኻ አካባቢ የሴቶች የስራ ላይ ግጥሞች››፣የኔ አለም አረዶ (1997)‹‹የጥዬ አካባቢ ሴቶች የስራ ላይ ግጥሞች››፣ብርሀኑ አሳዬ (1999) ‹‹በባንጃና በአንካሻ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች በአዊኛ የሚያዜሟቸው የስራ ላይ ግጥሞች በሚል ርዕስ የተሰሩት ናቸው፡፡

# 3፣የጥናቱ አካባቢ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ አካባቢ፣መልክዐ ምድራዊ፣ኢኮኖሚውና መሰረተ ልማቶችን በተመለከተ መረጃዎች ይገለፃሉ።

የሀድያ ዞን ዋና ከተማ ሆሳዕና ሲሆን ከአዲስ አበባ በስተደቡብ 230 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ፣ከክልሉ ዋና ከተማ ከዐዋሳ በስተ ሰሜን ምዕራብ 168 ኪሎ ሜትር ላይ ይገኛል። ዞኑም አስር ወረዳዎችና አንድ የከተማ አስተዳደር የያዘ ነው።ወረዳዎቹም ሶሮ፣ሊሙ፣አንሊሙ፣ምስራቅ ባደዋቾ፣ምዕራብ ባደዋቾ፣ ዱና፣ጎምቦራ፣ምሻ፣ሻሸጎና ጊቤ ናቸው።

## 3.1 መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ

የሀድያ ዞን በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ህዝቦች ክልል የሚገኝ ሲሆን በሰሜን ከጉራጌ ዞን በምስራቅ ከስልጤ ዞን ፣ከደቡብ ምስራቅ ከአላባ ልዩ ወረዳ ፣በደቡብ ምዕራብ ከከምባታ ጠምባሮ እና በምዕራብ ከጊቤ ወንዝ ጋር ይዋሰናል። የሀድያ ዞን የመሬቱ የቆዳ ስፋት 346958.8 ሄክታር ሲሆን የህዝቡ ብዛት ደግሞ የከተማ ወንዶች ቁጥር ብዛት 83310፣የከተማ ሴቶች ቁጥር ብዛት 78,380 ፣የገጠር ወንዶች 606,376 ፣የገጠር ሴቶች 618919 ሲሆኑ በአጠቃላይ 1386984 የሚያህሉ መሆናቸው  በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ህ/ክ/ መንግስት (የሀድያ ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ፣2004 ዓ.ም።) ባወጣው መፅሄት ላይ ተገልጿል።የዞኑ የአየር ንብረትም 40% ደጋ፣ 46% ወይናደጋ 12% ቆላማ እንደሆነ ተገልጿል።በሀድያ ዞን ከፍተኛ ተራሮች የሚገኙባቸው ስፍራዎች እንዳሉም በ2003 ዓ.ም.በደቡብ /ህ/ክ/መንግስት የሀድያ ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ እንደገለፀው ሰንግዬ ፣ቱላ ፣ሸንቆላ ፣ደንጋውራ ...እንዲሁም ወንዞቿም ጎምቦራ ፣ሲንታላ ፣ሳና ይባላሉ።የተፈጥሮ መስህቦቿ አጋሞ ፏፏቴ ፣ሀብቾ ፏፏቴ ፣በዮ ሀይቅ ፣ባቴና ዋሻ ፣ዋሪቁ ፏፏቴ ፣ሁናሴ ደን ፣አሊዳና ሀደዬ ዋሻ፣የዳንማ ተክል ድንጋይ ...ናቸው።

## 3.2 የሀድያ ብሄረሰብ መተዳደሪያ

የሀድያ ማህበረሰብ በከብት እርባታ ስራ ላይ ተሰማርተው ለብዙ ዘመናት እንደቆዩ አሁንም በዚሁ ስራና በእንሰት ምርት እንዲሁም በንግድ ስራ እንደሚተዳደሩ የቃል መረጃ አቀባዮቹ ወ/ሮ አበራሽ ላሊሶ (ቃለመጠይቅ የካቲት 9/2004 ፣አቶ ኤርሶዶ አንቶሴ 11/2004) ገልፀውልኛል።

የሀድያ ሴቶች ከእንሰት ተክል በሚገኙት ማለትም ጆባ ምንጣፍ፣ሰሌን ፣መጥረጊያ እና ፣ዘንቢሎችን በመሸጥ የኑሯቸው መደጎሚያ እንደሆነ ወ/ሮ አበራሽ ላሊሶ ጠቅሰውልኛል።ሌላው በተጓዳኝ በከተማውም ሆነ በገጠሩ አካባቢ ያሉ ወጣቶች ወደ ደቡብ አፍሪካ በመሄድ የንግዱን ስራ በከፍተኛ ሁኔታ እንደተቆጣጠሩት አቶ ኤርሲዶ አንቶሴ ገልፀውልኛል።ከዚህም የተነሳ የሚተዳደሩበት የገቢ ምንጭ ንግድ መነገድ ሆኗል፡፡

በሀድያ ገጠሩ አካባቢ የሚኖሩ ገበሬዎች የሚያመርቱት ምርት ከራሳቸው ቀለብ ተርፎ ወደ ሆሳዕና ከተማ ጤፍ፣ስንዴ፣ በቆሎ፣ገብስና ሌሎችንም የእህል አይነቶች አመቱን በሙሉ አንድ ቀን ሳያቋርጡ በቀን ቢያንስ ከ50 ጭነት በላይ በበቅሎና በፈረስ ለሸማቾች ያቀርባሉ።በሀድያ ገበሬዎች ከምርት አመራረት ጋር በተያያዘ መልኩ ትንሹ ካናዳ የሚል ስያሜ እንደተሰጣቸው (ቃለ መጠይቅ የካቲት 11/2004 ፣አቶ ኤርሲዶ አንቶሴ) ገልፀውልኛል።

## 3.3 ማህበራዊ አገልግሎቶች

የመገናኛ አገልግሎት የመንገድ ስርጭትን በተመለከተ ከሆሳዕና...ሾኔ97 ኪ/ሜ ፣ከሆሳዕና.... ጊምቢቹ 32 ኪ/ሜ ከሆሳእና...አንሾ 551.157 ኪ/ሜ፣ከሆሳእና...ሞርሲጦ 18 ኪ/ሜ ፣ከሆሳዕና.....ሆመቾ 30 ኪ/ሜ ፣ከሆሳዕና .....ቦኖሻ 56 ኪ/ሜ....ላይ ባለው ወረዳዎች እንዲሁም ሆሳዕና ከሁሉም ወረዳ ዋና ከተሞች ከአዲስ አበባ፣ከቡታጅራና ዱራሜ፣ከአርባ ምንጭ ፣ከወላይታ ፣ከአዋሳ ና ከድሬደዋ ጋር በመኪና ትራንስፖርት ትገናኛለች።

በሀድያ ዞን  የጤና ተቋማት በ2003 ዓ.ም. 1 ሆስፒታል ፣55 ጤና ጣቢያ ፣293 ጤና ኬላ ፣20 የገጠር መድሀኒት ቤት ፣2 ፋርማሲ ፣21 መድሀኒት መደብር ፣7 ላብራቶሪ እና 101 የግል ክሊኒኮች ይገኛሉ።

የትምህርት ዘርፍ አገልግሎትን ስንመለከት የትምህርት ቤቶች ብዛት ከ አንድ እስከ አራት 177 ፣ከ አንድ እስከ ስምንት 250 ፣ከዘጠኝ እስከ አስር 16 ፣ከአስራ አንድ እስከ አስራ ሁለት 1 ፣ከዘጠኝ እስከ አስራ ሁለት 6 ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ።

በዞኑ የውሃ አቅርቦት እጥረት አለ።ለችግሩ መከሰት ምክንያት የሚሆነው የአካባቢው የከርሰ ምድር ውሃ እጥረት መሆኑን በዞኑ ማስተባበሪያ መምሪያ ዕሁፍ (1999፣11) ተጠቅሷል።

# 4. ዘፈኖች የተከወኑባቸው የስራ አጋጣሚዎች

ይህ ክፍል ዘፈኖቹ የተከወኑባቸውን የስራ አጋጣሚዎችና የስራውን አከዋወን ያቀርባል፡፡የሀድያ ሴቶች በግልም ሆነ በህብረት ሆነው በሚከውኗቸው የስራ አጋጣሚዎች ማለትም የእንሰት መፋቅ፣የጓሮ አትክልት ኩትኳቶ፣ስንደዶ ለቀማ፣ ወፍጮ መፍጨት፣ወተት መናጥ፣እንጨት ለቀማ፣እረኝነት እና ሙቀጫ መውቀጥ ናቸው፡፡የእነዚህም የስራ አጋጣሚዎች መረጃቸው በፎቶ ቀርበዋል፡፡

## 4.1 የእንሰት መፋቅ (Wees Duugga)

አንድ እንሰት ለመፋቅ ደርሷል የሚባለው በእንሰቱ እናት ወይም ጫፍ ላይ እንደ ሙዝ መሰል አበባ ወደታች ሲያዘቀዝቅ ነው፡፡(ቃለመጠይቅ፣ሉምበሴ ኤርሲዶ፣20/06/04)፡፡በዚህን ጊዜ ሴቶች እንሰቱን ለመፋቅ የሚያስፈልጋቸውን ቁሶች ያዘጋጃሉ ወይም ከጎረቤቶቻቸው ይዋሳሉ፡፡ከዚያም የእንሰት መፋቅ ክህሎት ያላቸው ሴቶች ከየአቅራቢያቸው ይጠራራሉ፡፡ገሚሶቹ ሴቶች የሚፍቁትን የእንሰቱን ውጤት የሚያስቀምጡበት ጉድጓድ ይቆፍራሉ፡፡ገሚሶቹ ደግሞ ከእንሰቱ ተክል ላይ ቅጠላቅጠሉን ቆርጠው መሬቱ ላይ እና የተቆፈረው ጉድጓዱ ውስጥ ያነጥፋሉ፡፡ገሚሶቹ የእንሰቱን ስር ቆፍረው ያወጡና በእንጨት በተሰራ ባህላዊ ቁስ ይጨፈጭፉታል፡፡የእንሰቱን ግንድ ሰነጣጥቀው ይከፋፈሉታል፡፡ከዚያም የመፋቁን ስራ በሚያካሂዱት ሴቶች ቁጥር ልክ ቋሚ ጠፍጣፋ እንጨቶች ባልተቆረጡ የእንሰት ግንዶች ላይ ያስደግፏቸዋል፡፡ከእንሰት ግንድ የሰነጣጠቋቸውን በእንጨቱ ጫፍ ላይ ያስራሉ፡፡ ሴቶቹ መፋቁን የሚያካሂዱት ቆመው ወይም በትንሽ ወንበር ላይ ተቀምጠው እግራቸውን በታሰረው የእንሰት ግንድ ላይ ሰቅለው ከእንጨት በተሰራ ባህላዊ የእንሰት መፋቂያ የእንሰት ግንዱን ከላይ ወደ ታች ይፍቁታል፡፡ እንሰቱ ሲፋቅ ከእንሰቱ የሚወጣው ፈሳሽ ውሀ ወደ ተዘጋጀለት ጎድጓዳ ሳህን ውስጥ ይገባል፡፡ይህም ፈሳሽ ውሀ ‹‹ቡላዕ›› ተብሎ ይጠራል፡፡ሴቶቹ ግንዱን ፍቀው ከጨረሱ በኋላ በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ይከቱታል፡፡በጉድጓዱ ውስጥ ከአንድ አመት እስከ ሁለት አመት ድረስ ይቆያል፡፡(ቃለመጠይቅ፣ሉምበሴ ኤርሲዶ፣20/06/04)፡፡

ፎቶ 1.



1.አስሚቱ ከበደ 2 ሉምበሴ ኤርሲዶ 3. አንሾ ፋቴ እና ሌሎችም እንስት እየፋቁ የወደፊት ምግባቸውን እያዘጋጁ (ማክሰኞ 20/06/2004)

በእንስት መፋቅ እውድ በሀድያ የገጠሩ ክፍል በስሜን በሚገኘው ሌሞ ወረዳ በ አሼ ቀበሌ ነዋሪ በሆኑት በወ/ሮ አስሚቱ ከበደ መኖሪያ ግቢ ውስጥ ሲሆን የእንስት ፍቀት የተካሄደው ከተሰያዩ መንደሮች በመጡ ስምንት ሴቶች ነው፡፡

ከእነዚህም ሴቶች መካከል አምስቱ ሀድያዎች ሲሆኑ ሁለቱ ከምባታዎች ፤አንዷ ጉራጌ ናት ፡፡ ሁሉም በተሰያየ የዕድሜ ክልል ውስጥ ይገኛሉ፡፡ስምንቱም ሴቶች ባለትዳሮች ናቸው፡፡ከልምድ ማነስ የተነሳ ያላገቡ ሴቶች በእንስት ፍቀት ስራ ብዙም አይሳተፉም፡፡የቤተሰብ ሀላፊነትን የተረከበች ሴት ከሆነች ትሳተፋለች፡፡የእንስት ፍቀቱን ሲያከናውኑ የሚዘፍኗቸው ዘፈኖች በክብርና በጭብጨባ የታጀቡ ናቸው፡፡ በተለይም የስራው ማለቂያ ሲቃረብ በአንድ ላይ ተሰብስበው እልልታን በማሰማት ይጨፍራሉ፡፡

ፎቶ 2.



ሀከላ ኑሬ ሀሚቾ እየደመሸች

በእንሰት ፍቀት ጊዜ የእንሰቱ የታችኛው ስር ከመሬት ስር ተቆፍሮ ይወጣል።የስሩ መጠሪያ ስሙ ሀሚቾ ይባላል።ይህ አይነቱ አሰራር በሀድይኛ ቋንቋ እና ባህል ‹‹ሀሚቾ ይደመሻል›› ይባላል።በባህሉም ተወዳጅና ታፋጭ ምግቦች ከሚባሉት የሚመደብ ነው።ከእንሰት ተክል ለምግብነት የሚያገለግሉት ግንዱ ተፍቆ ስሩም ተጨፍጭፎ (ተደምሾ) ነው።

ከእንሰት ተክል እንደ ቆጮ፣ቡላ፣ሀሚቾ የመሳሰሉት ለምግብነት ይውላሉ። በእንሰት ተክል የሚሰሩት ቁሳቁሶች እንደ ጆባ፣ታጫ፣ጅራፍ የመሳሰሉት ናቸው።በሀድያ በገጠሩ አካባቢ

የተለያዩ የእንስት አይነቶች ይገኛሉ።ከእነዚህም መካከል ለአብነት ያህል ዲንሾ፣ጦሮራ ፣ወጨሬዳና ኡንጂንግ የተባሉት ይገኙበታል።

## 4.2 የጓሮ አትክልት ኩትኳቶ (Duubbi Kaashsha Korchimma)

በሀድያ ብሄረሰብ በገጠሩ አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች ቤታቸው አቅራቢያ ባለው ባዶ ስፍራ ላይ ከሚተክሏቸው የጓሮ አትክልቶች መካከል አንዱ ጎመን ተክል ነው። (ቃል አቀባዩ ወ/ሮ ሀንዲሴ በቀለ) በመጀመርያ ጎመን ለመትከል ስናስብ በአፈር መደብ እንሰራለን ከዚያም የጎመኑን ዘር በመደቡ ላይ እንዘራዋለን።የዘራነው ዘር አድጎ ለመተከል ሲደርስ ወደ ጓሯችን አምጥተን እንተክለዋለን ሲሉ ገልፀውልኛል (ቃለ መጠይቅ፣5/06/04) ።ከዚያም በየአስራ አምስት ቀናቶች ውስጥ በሀድይኛ ቋንቋ ‹‹ሄዱ›› በተባለው መኮትኮቻ ይኰተኮታል።

ፎቶ 3.



1.ሀንዲሴ በቀለ 2 አበራሽ አጪሶ እና ሌላዋ ጎመን ኩትኮታ ላይ ሰኞ 5/6/2004

የጎመን ተክል በሁለት ወራት ውስጥ ለምግብነት ይደርሳል።ሴቶቹ ጎመኑን አብስለው ለእንጀራ እና ለቆጮ ማባያ ያደርጉታል።ሌላው አይብ፣ ጎመን እና ቆጮ አንድ ላይ ተደርገው ቡሌንታ የተባለውን ባህላዊ ምግብ ይሰሩበታል። በደጋማው የሀድያ ክፍል በምሻ ወረዳ የኩትኳቶ ስራ በማንኛውም ወቅት ይካሄዳል።በቆላው አካባቢ ወቅታዊ

ነው፡፡የኩትኳቶ ስራ አድካሚና አሰልቺ በመሆኑ ሴቶች በሚኮተኩቱበት ጊዜ ከሚበሉት ምግብ ይልቅ ቦርዴን መጠጣት ይመርጣሉ፡፡በተጨማሪም የሰውነት ድካማቸውን ለመርሳት የተለያዩ ዘፈኖችን ይዘፍናሉ፡፡

በዚህ አውድ ሴቶች ከምሻ ወረዳ ዋስንበታ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት በዚህ አውድ በጎመን ኩትኳቶ ተግባራት ላይ የተሳተፉ ሴቶች ናቸው፡፡ሴቶቹ መሬቱን በመኮትኮቻ እየኮተኮቱ ከዚያም ባህላዊ ዘፈኖችን ተራ በተራ እየተቀባበሉ ያዜማሉ፡፡

## 4.3 ስንደዶ ለቀማ ( Migira feerimma)

በሀድያ ብሄረሰብ ስንደዶን የሚለቅሙት ሴቶች በህብረት ሆነው ነው፡፡ለቀማው የሚከወነው ከጥቅምት ወር ኢጋማሽ እስከ ህዳር ባለው ጊዜ ነው፡፡ለቀማው የሚካሄደው የሳር ግጦሽ ወይም ውሀ ባለበት አካባቢ ነው፡፡ስንደዶ የሚባለው በአይን የሚታየው ሳር መስል ሳይሆን ከሳር መስል ውስጥ ተፈልቅቆ የሚወጣው የሳር አይነት ነው፡፡

ፎቶ 4.




1. መረጡች ስየም 2. ብርቱካን ስለሞን 3. ሙሉ ኪኢሚሶ እና ሌሎችም ስንደዶ እየለቀሙ ማክሰኞ የካቲት 6/2004.

ሴቶች ስንደዶን ለተለያዩ ቁሳቁሶች መስሪያነት ይገለገሉበታል። ከስፌት የሚገኙ እንደ መሶብ፣ሰፌድ ወዘተ የመሳሰሉትን ቁሶች ይሰሩበታል። በተጨማሪ ስንደዶ ለጎጆ ቤቶች ከላይ እንደ ማርያ በመሆን ያገለግላል።

## 4.4 ወፍጮ መፍጨት (Liitimma)

በሀድይኛ ቋንቋ ወፍጮ ማለት ሊትማ ማለት ነው። በገጠሩ አካባቢ ያሉ ሴቶች ስንዴ፣ገብስ ፣ማሽላ ፣በቆሎ ወዘተ የመሳሰሉትን የእህል አይነቶች በባህላዊው መፍጫ በእጆቻቸው በመፍጨት አብስለውና ጋግረው ባሎቻቸውን፣ ልጆቻቸውን እንዲሁም እራሳቸውን ይመግባሉ።

ፎቶ 5.



1. ወ/ሮ ሲቦ ኤርመኮ ለምግብነት የሚሆነውን ገብስ እየፈጨ የካቲት 5/2004

ከመረጃ አቀባዮቼ መካከል ወ/ሮ ሲቦ ኤርመኮ በዚህ ወረዳ ዘመናዊ የእህል መፍጫ ቢኖርም በእጃችን የመፍጨት ልማዱን አልተውነውም። ምክንያቱም በዘመናዊ ወፍጮ የተፈጨ እህል አይበረክትም፣እህሉ ጣዕም ያጣል ።በዘመናዊ ወፍጮ በተፈጨ ዱቄት የሚጋገረው

ቲጣ ለጤና ተስማሚ አይሆንም የሚል ፍራቻ አለ ብለውኛል ።(ቃለ መጠይቅ የካቲት 5፣2004)

በወፍጮ አውድ ላይ የምንመለከታቸው ወ/ሮ ሲቦ ኢርመኮ በምሻ ወረዳ ቱላ ቀበሌ ነዋሪ ናቸው። በባህላዊ ወፍጮ የተለያዩ የእህል አይነቶችን ከሚፈጩ ስድስት ሴቶች መካከል አንዷ ሲሆኑ የአምስት ሴቶች ልጆችና የሁለት ወንዶች ልጆች እናት ናቸው።ወ/ሮዋ በጉልበታቸው በመንበርከክ፣ገብሱን በወፍጮው መሀል ላይ ካደረጉ በኋላ መጁን በሁለት እጆቻቸው ጫን በማድረግ ወደታችና ወደላይ እጆቻቸውን በመመላለስ ገብሱን ያደቁታል።ወ/ሮዋ እህል ሲፈጩ በወፍጮውና በመጁ ድምፅ በመታጀብ ያዜማሉ።

## 4.5 ወተት መናጥ(Addo gimmiishshimma )

ወተት መናጥ በሀድያ ንጠር አካባቢ ይከወናል።አብዛኛውን ጊዜ ወተት የሚናጠው በአሮጊቶችና በልጆች ነው።ወንድ ወተት መናጥ አይፈቀድለትም።በብሄረሰቡ እምነት ወተት እና ቅቤ እርጥብ በመሆናቸው ስራው እርጥብ በሆኑ ሰዎች መከወን አለበት ተብሎ ይታመናል። ‹‹እርጥብ››የሚለው ቃል የሚወክለው ወላድ ሴቶችን ነው። በዚህ ምክንያት ወንድ መናጥ የለበትም ቢንጠውም ቅቤው አይወጣም የሚል እምነት እንዳላቸው ወ/ሮ ሙሉነሽ ኢርጎን፣(29/06/04) ገልፀውልኛል። በተጨማሪም ወንድ ወተት የገፋ እንደሆነ አቅመ ደካማ ነው ተብሎ ስለሚቆጠር መሆኑን ነግረውኛል።

ፎቶ 6




1.ወ/ሮ ሙሉነሽ ኢርጎን ወተት እየናጡ የካቲት (29/06/2004)

በገጠሩ አካባቢ ወተት የሚናጠው ከጎኑ ትንሽ ቀዳዳ ባለው ማሰሮ ነው። ሴቶቹ ወተቱን በማሰሮው ከጨመሩ በኋላ የማሰሮውን አፍ በቆዳ ጥፍር አድርገው ያስሩታል ።ቀዳዳውንም በትንሽ ውታፍ ነገር ይወትፉታል።በዚህን ጊዜ በአንድ እጃቸው የማሰሮውን ጆሮ በመያዝ ወደታች ይገፉትና ወደ ላይ ቀና ያደርጉታል።ትንሽ እንደገፉት የወተቱ ሀይል ቆዳውን እንዳይፈታውና ወተቱ እንዳይፈስ በማሰሮው ቀዳደ ውስጥ የወተፉትን ውታፍ በመንቀል ያስተንፍሱታል ።በገጠሩ አካባቢ የወተት መናጥ የማያቋርጠው የወተት ኪራይ ያልተለመደ በመሆኑ፤ለመብልና ለመጠጥ እንዲሁም ለፀጉራቸው የሚሆናቸውን ቅቤ ፣አይቤና አጓት ከሚንጡት ወተት ስለሚያገኙ ነው።

## 4.6 እንጨት ለቀማ (Haqqa feerimma )

በሀድያ ገጠሩ አካባቢ ተወላጅ የሆኑ ሴቶች ልጆች ቤተሰቦቻቸውን ከሚደግፉባቸው አንዱ የስራ አይነት እንጨት ለቀማ ነው።እንጨት ለቀማ ደን ባለበት አካባቢ፣የግል ባልሆነ ዱር ወይም እፅዋት በብዛት ባሉበት አካባቢዎች ላይ ይካሄዳል።

ፎቶ 7.




1.ፈዲላ አማን 2.አምሪያ አብደላ 3.ራውዳ ወረቂቾ እና ሌሎችም ለማገዶ የሚሆንን እንጨት እየለቀሙ ዕሁድ 18/06/2004.

ሴቶቹ ልጆች ከየቤታቸው ትናንሽ ፋስ መጥረቢያ በመያዝ ወደ መስክ ይወጡና ሊደርሱበት የሚችሉትን ወይም ማደግ ያልቻለውን ዛፍ ይቆርጣሉ።ከዚያም የቆረጡትን እንደ አቅማቸው በገመድ ወይም በቃጫ አስረው በወገባቸው ላይ ካስቀመጡት በኋላ ገመዱን በትከሻቸው ላይ በማምጣት ተሸክመው ይሄዳሉ።

በጥናቱ አካባቢ በአሁኑ ጊዜ የእንጨት ለቀማ በብዛት ሲከወን አይታይም።የዚህ ምክንያቱ ደኑ እየተመነጠረ መሬቱ ለእርሻ በመዋሉ ነው። እንጨት ለቀማና ሸክም የተካሄደው በአንሌሞ ወረዳ በገደሊቾ ቶሬ በተባለው ቀበሌ ውስጥ በሚኖሩ ሰባት ሴቶች ልጆች ነው ።ሴቶች ልጆች ለእንጨት ለቀማ ከመኖሪያ ቤታቸው አካባቢ ራቅ ብለው እንዳይሄዱ በቤተሰቦቻቸው ይመከራሉ።ሙሼቤ ሙንዲኖ[1](18/06/04)።

ይህ የሚመከረው ርቀው በሚሄዱበት ጊዜ ለጠለፋ ና ለተለያዩ ጥቃቶች እንዳይደረጉ ጭምር በማሰብ ነው።ሴቶቹም በአቅራቢያቸውና ከአካባቢያቸው ሳይርቁ ቅጠላቅጠሉችና ጭራሮዎች በማግኘታቸው ደስታ ተሰምቷቸው ይዘፍናሉ።

ፎቶ 8.



የለቀሙትን እንጨትና ጭራሮ ተሸክመው እየዘፈኑ ወደ ቤታቸው ሲሄዱ

በአንሌሙ ወረዳ ቀበሌ በንደሊቾ ፋራ ተገኝቼ በነበረበት ጊዜ እንጨት ሲለቅሙ ካገኘኋቸው ሴቶች ልጆች መካከል በእድሜ አነስ ያለችው ነጃት ከማል ዜማውን በማቀንቀን ስትጀምር የተቀሩት በመቀባበል ለስራውና ለዜማው ድምቀት ሲሰጡትና በመጨረሻም እንጨቱን በጆርባቸው አዝለው ወደ መጡበት ሲመለሱ ሲዘፍኑ ተመልክቻለሁ ::

## 4.7 እረኝነት ( Laro allaarimma)

የሀድያ ህብረተሰብ ህይወት የተመሰረተው በግብርና እና በከብት እርባታ በመሆኑ የእረኝነት ስራ እንደ አንድ የስራ መስክ ይቆጠራል።እረኝነት በሴቶችም በወንዶችም ይካሄዳል።

በጎምቦራ ወረዳ ሰጌ ቀበሌ ላይ የእረኝነትን ስራ ሲሰሩ ያገኘኋቸው ሴቶች አምስት ናቸው።ከእነዚህም ሴቶች መካከል (ዱባለች ፍቅሬ፣ የካቲት ፣29/2004) የእረኝነት ስራ በሁለት አይነት ፈርጆ እንደሚከናወን ገልፃለች።

አንዱ የእረኝነት አይነት ተራ በተራ በሀድይኛ (Koore ) ማለት ሲሆን ይኸውም መልካም ጉርብትና ያላቸው አባወራዎች የየቤቱን ከብቶች በማሰባሰብ ከአካባቢው ራቅ አድርገው ተረኛው እንዲጠብቅ የሚደረግበት ነው።

ፎቶ 9.




1.ዱባለች ፍቅሬ ፣ከበደች ባቻሬ ና ሌሎችም ከብቶችን ወደቤታቸው ሲመልሷቸው 29/06/2004.

አረኛው ከመስክ ወደ ቤት ከብቶቹን ይዞ ሲመለስ የከብቶቹ ባለቤቶች እንኳን ደህና መጣህ በማለት ቤማዊ ግጥምን በማሰማት ይቀበሉትና ጠዋት ቆጥረው እንዳስረከቡት ሁሉ ከብቶቻቸውን ቆጥረው ይቀበላሉ።(ቃለ መጠይቅ፣ዱባለች ፍቅሬ፣29/06/04)። በእድሜያቸው ለጋነትና ተማሪዎች በመሆናቸው ይህንን የእረኝነት ተግባር ሴቶች አይሰሩም ።ሁለተኛው የእረኝነት አይነት የየራሳቸውን ከብቶች በየግላቸው ወደ ዱርና ግጦሽ ወደአለበት በመውሰድ የሚጠብቁበት የእረኝነት አይነት ነው።

## 4.8 ሙቀጫ መውቀጥ (Tumimma)

በሀድያ ብሄረሰብ በገጠሩ አካባቢ ወቀጣ የሚካሄደው በግለሰብ ወይም በቡድን ነው ። እኔ የተመለከትኩት የወቀጣ ስራ የተካሄደው በጎምቦራ ወረዳ ቀበሌ ዋቤቶ በሚባል አካባቢ ሲሆን ከዋኜውም ያሳተፈው እህል ለመውቀጥ አቅም ያላቸውን ሴቶች ብቻ ነው።ወቀጣው የተካሄደው በባህላዊ መውቀጫ ነው። የሚወቀጠው እህል በውሀ ለጥቂት ደቂቃ ከተዘፈዘፈ በኋላ በወንፊት ላይ በማድረግ ውሀውን እንዲጨርስ ተደረገ።

ፎቶ 10.



1.ከሚ ደሌቦ 2. አየለች ዱብ አለ 3. ትእግስት ኤርሞ እና ሌላዋ ለገንፎ የሚሆን ገብስ እየወቀጡ ቅዳሜ የካቲት 29/2004.

ከዚያም እህሉን ወደ መውቀጫው አፍ ውስጥ ካስገቡት በኋላ ዘነዘናውን በሁለት እጃቸው በመያዝ ወደላይ እና ወደታች እያደረጉ ወቀጣቸውን ቀጠሉ።ወቃጮቹ ሴቶች በተሳታፊዎች በሚሰሙት ጭብጨባ ና ዘነዘናው በሚያሰማቸው የምት ድምፅ ጋር በማስማማት የተለያዩ ባህላዊ ዘፈኖችን በመዝፈን ክወናውን አካሂደዋል።

ምንም እንኳን ወቀጣ በባህሉ የሴቶች ስራ ነው ተብሎ ቢወሰንም በቤት ውስጥ የተለያዩ ዝግጅቶች ሲኖሩ ወንዶችም የግድ ይሳተፋሉ። መውቀጫና ዘነዘና ባህላዊ ቁሶች ናቸው። እነዚህ ባህላዊ ቁሶች የሚበጁት ከዋንዛ እንጨት በወንዶች ነው።

## 5. የስራ ላይ ዘፈኖች ትንተና

በዚህ ምዕራፍ ሴቶች በህብረትና በግል ሆነው በየስራ አይነቶቹ ባዜሟቸው ዘፈኖች የተነሱት ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ እንመለከታለን። በዘፈኖቹ የተነሱት ጉዳዮችም ስለ ስራ ፣የእንሰት ተክልን ስለ ማወደስ ፣ስለ እረኛ ፣ስለ ወተት ፣ስለ ዘር ሀረግ ፣ስለ ዝናና ጀግንነት፣ስለ ጨዋታና ጭፈራዎች፣ውበትን ስለ ማድነቅ፣ምግብ ስለ ማዘጋጀት፣ስለ ሀድያ ሴቶች ማንነት እና ስለ ክንፈር ወዳጅ ናቸው።በተከታዩ ክፍል በየስራ አጋጣሚዎቹ ከተዘፈኑ ዘፈኖች የተመረጡ በየአውዳቸው ተለይተው ይተነተናሉ።

### 5.1 በእንሰት መፋቅ ላይ የተዘፈኑ

በሀድያ በኀረሰብ የስራ ባህል የእንሰት ተክል ተቆርጦ የሚፋቅበት ጊዜ ሲደርስ ጎረቤቶች ወይም ዘመድ አዝማዶች ተጠራርተው በህብረት በመሆን እንሰቱን ይፍቁታል።(ቃለ መጠይቅ፣ሀኮላ ኑሬ፣አንጀሾ ቶቴ እና ኢደሜ ደርጋሶ 20/06/04)

በእንሰት መፋቅ ስራ ላይ ያገኘኋቸው ላቆ ጊደሞና መስቀሏ ኦንቶሎ(22/06/04 )የእንሰት ተክልን እንደ ልጃቸው በመቁጠር እሹሩሩ በማለት የሚከተለውን አዚመዋል።

(4) Gibbi wotta'll'n

Weeshshichcho ororoo

Gojo i woronne

Gii mmamoo bu'e

Weesa ororoo *4

እንደ አውራራሽ ልጆቼ

የኔ እንስት እሹሩሩ

በቆሎው ተደጓድ

የቆሞው በላው

እንስት እሹሩሩ

አቀንቃኞቹ ‹‹እሹሩሩ›› የሚለውን ቃል እየተቀባበሉ እንስትን በዜማ ያባበሉበት ምክንያት እንስት ልክ እንደ ህፃን ልጅ እንክብካቤ የሚፈልግ ተክል መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ እሹሩሩ እያልን የምንዘፍነው (ቃለመጠይቅ ፣ለቶ እና መስቀሏ እንቶሎ፣የካቲት22/2004) በመሆኑም መስቀሏ ‹‹የኔ››በማለት በመደጋገም ያዜመችው በሀድያ ባህል የእንስት ተክል የሌለው ግለሰብ በጣም ሰነፍ በመባል ስለሚወገዝ እንስቱ የእሷ ወይም ባለቤትነቷን ለመግለፅ ጭምር ነው፡፡ በሀድያ ብሄረሰብ ልማድ የእንስት ተክል የሚተከለው በወንድየው ወይም በአባወራው ነው፡፡በባህሉ የእንስት መፋቅ በወንድ አይከወንም ፡፡‹‹ከእንስት የሚገኘውን ገቢም ጭምር ለሴቷ እንጂ ለወንዱ የሚሰጥ አይደለም፡፡››(ቃለ መጠይቅ፣ ሀከላ ኑሬ፣አንቾ ቶቴ እና ኢደሜ ደርጋሶ ፣20/06/04) ስለዚህ አቀንቃኟ ከእንስት የሚገኘው ገቢ የሴቷ መሆኑን ለማሳየት በዘፈኗ ‹‹የኔ›› በማለት ጥቆምታ ሰጥታለች፡፡ሌላው ‹‹እንደ አውራሪስ ልጆች››በማለት የተገለፀው ስንኝ ንፅፅራዊ ነው፡፡ ከእንስት ምርት የሚገኘው‹‹ቡላ››ጥሩ ጣእም እንዲኖረው ለተወሰኑ ጊዜያት ለቆጮ በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ይቀበራል፡፡አውራሪስም መሬት በመቆፈር በጉድጓድ ውስጥ ልጆቹን ያስቀምጣል፡፡የአውራሪስ ልጆችም ሆኑ ቡላ ተመሳሳይ በሆነ ሂደት ውስጥ በማለፋቸው ምክንያት በንፅፅር ቀርበዋል፡፡ ቀጥሎ በሰፈረው ግጥም ውስጥ ደግሞ አቀንቃኟ እንስት ለብሄረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ትገልፃለች፡፡

(5)Hawwaa'n qaraare

Hoongaa'n lubato

Hiimina ballina

Haabaam hurbaata

Weesa ororoo *4

የችግረኞች መድሀኒት

የደሀዎች ቁስ

ለቀንና ማታ

ወደር የለሽ ምግብ

እንስት እሹሩሩ*4

(ለቶ ጌደሞ፣እንስት ፍቶት ሀሙስ የካቲት 22/2004 )

አቀንቃኟ በሀድያ ብሄረሰብ ዘንድ እንሰት የሚሰጠውንም ጠቀሜታ ለመግለፅ ‹‹የችግረኞች መድሀኒት ››በማለት አዚማለች፡፡ለሀድያዎች እንሰት የዘወትር ምግባቸው ነው፡፡ከእንሰት ተክል እንደ ቆጮ ፣ቡላ ፣ሀሚቾ የመሳሰሉት ለምግብነት ይውላሉ፡፡እንዲሁም በብሄረሰቡ ዘንድ ቆጮው እንደ ኬክ ማገልገሉን ለመግለፅ ‹‹ጊማሙ ኬክ ››በማለት ቅፅል ስም ተሰጥቶታል፡፡

አቀንቃኟ ‹‹የችግረኞች መድሀኒት›› እያለች ያዜመችው እንሰቱ ከሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች አንፃር ነው፡፡እንሰት በአየር መዛባት ምክንያት የሚመጣውን ድርቅ መቋቋም የሚችል በመሆኑ ጭምርም ነው፡፡‹‹የደካሞች ዋስ›› የሚለው ሀረግ በእርጅና እና በገንዘብ እጦት ምክንያት እርሻን የማረስ ወይም የማሳረስ አቅም ለሌላቸው ወይም በእንሰት ምርት ብቻ ለሚተዳደሩ ሰዎች ዋስ ሊሆን እንደሚችል ለመግለፅ ነው፡፡በሀገሩ ባህል በቀዬው አካባቢ የእንሰት ተክል የሌለው ሰው ብር ለመበደር ቢፈልግ እንኳን የሚሰጠው የለም ምክንያቱም እንደ ዋስ የሚሆነው የእንሰት ተክሉ ነው፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ለቶ ጊደሞ፣19/2004 )

ይህቺው አቀንቃኝ በሌላ ዜማዋ ደግሞ እንሰት ያለው ሰው ክብርና የተለየ ቦታ የሚሰጠው መሆኑን ‹‹ይምራን የእንሰት ባለቤት›› በሚለው ስንኝ ትጠቁማለች፡፡

(11) Abeetoo bachchakku'uyyi

Abeetoo garakkam weesoro

Abeetoo gashakku'uyyi

Abeetoo garakkam gadira

Abeetoo weesi anni awwonse *2

አቤት ቢመነከር ቢፋቅ

አቤት የማያልቅ እንሰት

አቤት ቢታሰብ ቢታሰብ

አቤት የማያልቅ ወተት

ይምራን የእንሰት ባለቤት

በግጥሙ ውስጥ እንስት ከጎሮ እየተቆረጠ ለምግብነት ቢመነጠርና ቢፋቅ የማያልቅ ተክል መሆኑ ተጠቁሟል፡፡‹‹አቤት ቢታሰብ ቢታሰብ›› የሚለው ስንኝ የእንስቱን ብዛትና ከእንስቱ የሚያገኟቸውን ጥቅማጥቅሞች የሚያሳይ ነው፡፡በእንስት የሚገኘውንም ገቢ ሆነ ለምግብነት የሚሰጠው ጥቅም ብዙ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ምንም እንኳን የእንስት ገቢ የሴቶች ቢሆንም በወንዱ ስለሚተከል ባለቤት የሚባለው ወንዱ ወይም ባሏ ነው፡፡ስለዚህም አቀንቃኟ ‹‹ይምራን የእንስት ባለቤት ›› በማለት ያዜመችው አንድም እንስት በብዛት የሚተክል ወንድ ጎበዝ ፣ጠንካራ ሰራተኛ በመሆኑ ሲሆን፣ አንድም በችግር ወይም በድርቅ ጊዜ ከእርሱ ደጅ እንስት ስለማይታጣ ለሰው ይተርፋል በማለት ነው፡፡ ስራን የሚሰራ ሰው ሰርቶም ማሰራት ስለሚችል እንዲህ አይነት ሰው ይምራን ያስተዳድረን የሚል እሳቤን የያዘ ነው፡፡

በሀድያ ብሄረሰብ እንስት የሚፍቁት ሴቶች በደቦ ነው፡፡ ሴቶቹ የመፋቁን ሂደት የሚያከናውኑት በተለያዩ ባህላዊ ጭፈራዎችና ዘፈኖች በመታጀብ ነው፡፡ ከመረጃ አቀባዮቹ መካከል ወ/ሮ ኤርሞ ኬኢሚሶ ባህላዊ ጭፈራና ዘፈን ጥንትም በእናቶቻችን ዘመን ይደረግ የነበረ ስርአት ሲሆን እኛም ጥንት ከእናቶቻችን የሰማነውን ዘፈን በአሁን ዘመን እያልነው እንገኛለን፡፡ አሁን አሁን ግን በእንደዚህ ባለ የስራ አጋጣሚዎች ላይ ባህላዊ ጭፈራዎች እና ዘፈኖች እምብዛም አይከወኑም፡፡ምክንያቱም የማህበረሰቡ እምነት ወደ ክርስትና በመቀየሩ ነው ብለውኛል፡፡ ቃለ መጠይቅ፣ወ/ሮ ኤርሞ ኬኢሚሶ (የካቲት ፣20/2004)፡፡

በእንስት መፋቅ የተሳተፈችው ሌላዋ አቀንቃኝ ከሙል መሀመድ ደግሞ ምንም እንኳን ብዙ እንስት ቢቆረጥም ድካም ተሰምቶን ፍቀቱን እንተወውም የሚል ዘፈን ዘፍናለች፡፡

(10)Garooyyo garooyyo

Meco'l garooyyo ahaa

Waallummi kollinne Waa'isa guungoommo

Wo'isa dandoommo

የምንፍቀው እንስት አያሸንፈንም

አንዱም ሳይተርፍ ሁሉን እንፍቃለን

በስራችን ሁሉ፣ እንደ መብረቅ እንጮሀለን

ልክ እንደ ጅረት ውሀ እንፈሳለን

(ከሙል መሀመድ፣እንስት ፍቀት የካቲት 20/2004)

ከሙል ‹‹የምንፍቀው እንስት አያሸንፈንም›› በማለት ያዜመችው ዘፈን የተቆረጠውን የእንስት ቁጥር ብዛት ይነግረናል።ይህ ስንኝ ለእንሰቱ ባለቤቶች አይዞአችሁ አትፍሩ ምንም እንኳን እንሰቱ ብዙ ቢሆንም ሳንጨርስ ደከመን በቃን አንልም የሚልን ሀሳብ የያዘ ነው።የተቆረጠውን እንስት ሁሉ እንፍቃለን። አቀንቃኟ ‹‹እንደ መብረቅ እንጮሀለን›› በማለት የራሷንና የባልደረቦቿን ድምፅ ከመብረቅ ድምፅ ጋር አነፃፅራለች።የመብረቅ ድምፅ ሀይለኛ ነው። ስራችንን ሁሉ ስንሰራ በዘፈኖቻችን የምናሰማው ድምፅ እንዲሁ ሀይለኛና ጠንካራ ነው።እንደ ጅረት ውሀ እንፈሳለን በማለት ከሙል ያዜመችው ስንኝ አንድ ላይ ወይም በህብረት ሆነን እንሰራለን የሚል ሀሳብ አለው።

## 5.2 በጓሮ አትክልት ኩትኳቶ ላይ የተዘፈኑ

በኩትኳቶ አውድ ሴቶቹ ስራን መስራትና አለመስራት በሰዎች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አዎንታዊና አሉታዊ ጎን የሚገልፁ ዘፈኖችን ዘፍነዋል፡

(22) Qiidane baxu bee'ek

Qiibatanne funaanookko

Angi xissoo qaxa bayukkok

Aq xissoo qaxa buu'nnookko

የሚኒት ብርድ ፈርቶ የተኛ

በሚኒት ወርጭ ላይ ይለምናል

እጁን እስኪያመው የሰራ

አፉን ሞልቶ ይጎርሳል።

(ማተፌ ሲባሞ ፣ ጎመን ኩትኳቶ 11/06/04 )

በሀድያ ገጠር አካባቢ የሚኖሩ ሴቶችና ወንዶች ልጆች ስራን መስራት የሚጀምሩት በማለዳ ነው።ሆኖም ለዚህ ልምምድ እራሳቸውን ያላስገዙ ሰዎች እድል ፈንታቸው የሚሆነው ልመና መሆኑ በዘፈኑ ተገልጿል።አቀንቃኟ ይህንን ዘፈን ልትዘፍን የተነሳሳችበት ምክንያት ጎረቤቷ ያለችውን ሴት በግጥሟ ሀሳቧን ልትገልፅላት ስለፈለገች መሆኑን ተናግራለች። (12/06/04 ) ‹‹ጎረቤቴ አብዛኛውን ጊዜ ብርድን እየፈራች ማለዳ አትነሳም በተጨማሪም ስራ መስራት አትወድም።››በመሆኑም በማህበረሰቡ እና በባልዋ የተጠላች ሴት ነች ።አቀንቃኟ በዘፈኗ ውስጥ በዋናነት ልታስተላልፍ የፈለገችው ጉዳይ ስራን መስራት እንደሚያስከብር ፤እንዲሁም ደግሞ አለመስራት እንደሚያዋርድ ነው። አቀንቃኟ ‹‹አፉን ሞልቶ ይጎርሳል ›› በማለት ያዜመችው ስንኝ ስራን በርትቶ የሰራ ያለ ምንም ስጋት ወይም ፍርሀት እንደሚኖር የሚገልፅ ነው።እንዲሁም ስራን መስራት ለማይወዱ ሴቶች መንቃቃት እንዲሆንላቸው፣ የመስራት መንፈስ እንዲኖራቸው፣ ስንፍናቸውን በማስወገድ በርትተው እንዲሰሩ የሚያደርግ ዘፈን ነው።

ሌላዋ አቀንቃኝ ደግሞ በርትቶ ከመስራት የሚገኘውን ጥቅም የሚያሳይ ዜማን አቀንቅናለች።

(23) Faare'aa baxukkok

Fakkakka buu'nnookko

Daddarukkok diinate siidookko

Diriirukkok duuncha qabaaxxookko

ስራን በርትቶ የሰራ

ተደላድሎ ይኖራል።

የነገደ ያተርፋል

መኝታ የሚወድ ስድብ ያተርፋል።

( ሀንዲሴ በቀለ፣ኩትኪቶ 5/06/04 )

አቀንቃኟ ስራን የሚሰራ ሰው ተደላድሎ እንደሚኖር ፤የነገደም ሰው እንደሚያተርፍ፣መኝታንም የሚወድ ደግሞ እንደሚሰደብ በዘፈኗ ጠቁማለች።በዚህ ስንኝ

፡፡መኘታ፡፡ የሚለው ቃል ስንፍናን፣ አለመስራትን ያመለክታል፡፡ሰነፍ ወይም የማይሰራ ሰው በብሄረሰቡ ዘንድ እንደሚናቅ የሚሰጠውም ቦታ ዝቅ ያለ መሆኑን ዘፈኑ ይጠቁማል፡፡የሀድያ ሴቶች በስራ ብርቱዎች ከመሆናቸው የተነሳ በማህበረሰቡም የሚሰጣቸው ቦታ ከፍተኛ ነው፡፡ ባሎቻችን የሚወዱን ፣የሚያከብሩን ስራን ስለምንሰራ ነው፡፡ስለዚህ ይህን ክብር እና መወደድ ላለማጣት ያለመታከት እንሰራለን ፡፡(ቃለ መጠይቅ ወ/ሮ አለሚቱ ከበደ እና ቦራ ሄገና፣14/06/04)፣ሀንዲሴ በቀለ እና ወ/ሮ ሀከላ ኑሬ 5/06/04) ፡፡

በሀድያ ብሄረሰብ ሴቶች በቤትም ሆነ በመስክ የሚሰሯቸው ስራዎች በርካታ ናቸው፡፡ሴቶቹ በስራዎች ጫና ምክንያት የመጣባቸውን ጭንቀት ለመርሳት ሲሉ የማበረታቻ እና የማንቃቂያ ዘፈኖችን በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎቻቸው ላይ እንደሚያዜሙ ይናገራሉ፡፡ሴቶች ድካማቸውን በሰውነታቸው ህዋሳት አማካይነት ለአእምሮአቸው የሚያስተላልፈውን መልእክት እንዲረሱትና ማህበረሰቡ የጣለባቸውን የስራ ድርሻቸውን እንዲወጡ ስሜቶቻቸውን የሚያነቃቁ ንግግሮች ወይም ግጥሞች ያስፈልጋቸዋል በማለት (ቃለ መጠይቅ፣ሽዎ አሽቦ፣ 12/06/04) ጉዳዩን ገልፀውታል፡፡

(14) Hallelle Hallelle hoo *2

OOsimii Osoyyo

Oroo oo Wotalla

Axxaxxii Kabeera

ሆ ቤሉ ሰዎች

ልጆቼ ታታሪዎች

የተከላ ልጆች

የሜካ ነብሮች

( ሽዎ አሽቦ፣ኩትኳቶ 22/06/04 )

፡፡ሆ በሉ ሰዎች፡፡ በማለት ዜማዋን የጀመረችው አቀንቃኝ በኩትኳቶ ስራ ላይ ተሳታፊ ከሆኑት መካከል አንዷ ሽዎ ነች፡፡በሁለተኛው ስንኝ የተጠቀሰው ሀሳብ የአቀንቃኟን እና

የስራ አጋሮቿ እድሜ ልጆች መሆናቸውን ይናገራል።እንዲሁም ‹‹ልጆቹ ታታሪዎች ።መሆናቸውም በግጥሙ ውስጥ ተገልጿል ።አቀንቃኟ ከብዙ የዱር አራዊቶች መካከል ተኩላና ነብርን የመረጠችበት ምክንያት ተኩላና ነብር ከዱር አራዊት እንስሳት የጀግንነትና የጥንካሬ ተምሳሌቶች በመሆናቸው ነው።ተኩላ የተባለው የዱር አራዊት በባህሪው ደፋር ፣ብቸኛ መሆንን የማይፈልግ ሲሆን ነብር ደግሞ የማይደክም፣የማይሰለቸው ፣ለምሳሌ ሊበላት የፈለጋትን እንስሳ እስኪይዛት ድረስ የሚታገል ነው።ስለዚህ እኛም እንዲሁ ስራችንን በአንድ ላይ በመሆን ተባብረን እንስራለን ፣እንታክትም የጀመርነውን ስራም ከፍጻሜው ሳናደርስ አንተወውም በማለት መረጃ አቀባዮቹ ኢደሜ ጫሚሶ እና ቦራ ሄገና ቃለ መጠይቅ፣(14/06/04) ገልፀውልኛል።

ሌላዋ አቀንቃኝ ደግሞ ተመሳሳይ መልእክት ያላቸውን ቃል ግጥሞች እንደሚከተለው አዚማለች።

(25) Oosim oosoyyo hoo

Itookki hobbuwwaa hoo

Oro ii wottallaa hoo

ልጆቹ ልዩ ናቸው

ሀይለኛ አንበሶች

የተኩላ ግልገሎች

(ኢደሜ ጫሚሶ፣ኩትኳቶ 22/06/2004)

የተለያዩ ሴቶች በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎች ላይ የሀድያ ሴቶች በስራ ላይ ስላላቸው ብርታት፣ትጋት ወዘተ የመሳሰሉትን የሚያሳዩ ተመሳሳይ ዘፈኖችን ዘፍነዋል።ሴቶቹም ስለራሳቸው ያላቸው አመለካከት በተመለከተ ጠንካራ ፣ታማኝ ፣እግዚአብሄርን የምንፈራ ፣በሌሎቹ ነገሮች ተወዳጅ ፣ተፈላጊዎች ነን የሚል እምነት አላቸው። (ቃለ መጠይቅ ሽዎ አሾቦ፣12/06/04፣ኢደሜ ጫሚሶ እና ቦራ ሄገና፣22/06/04)

አቀንቃኟና የስራ ባልደረቦቿ በእድሜ ልጅ መሆናቸው በግጥሙ ተገልጿል። ስራውን የሚሰሩት ልጆች ልዩ መሆናቸውንም ተናግራለች።አንበሳና ተኩላ በባህሪያቸው ሀይለኞች

ናቸው።እደሜ የልጆቹንና የራሷን ብርታት፣ ጥንካሬ ለመግለፅ በተለዋጭ ዘይቤ ‹‹አንበሶች ››እና ‹‹የተኩላ ግልገሎች›› ብላለች።

በኩትኳቶ ስራ ላይ ከተሰማሩት ሴቶች መካከል ደግሞ ቦራ ሄገና ልጆቹ ስራን እንዲሰሩ የሞራል ድጋፍ የሚሰጡ የማንቃቂያ ዘፈኖች ዘፍናለች።

(24) Haleelee haleele hoo *4

Keera ka oosina hoo

Goollam shaayeduyye hoo

Goon saroo woxxiduyye hoo

ለስራ ሆ ብለን እንነሳ ሆ ብለን

ሆ እንዲያው ለእነዚህ ልጆች

ማፍላት ነው ትኩስ ሻይ

ስሟቸው ወንድ የሰራውን ወጥ

(ቦራ ሄገና ፣ኩትኳቶ፣ 22/06/04)

በገጠሩ አካባቢ የኩትኳቶ ስራ አብዛኛውን ጊዜ በማለዳ ስለሚከወን ብርድ ይኖራል። ስለዚህ አቀንቃኟ በቁፋሮ ስራ ላይ ተሰማርተው ላሉት ሴቶች ልጆች ትኩስ ሻይ ማፍላት እንደሚገባ በዘፈኗ አስታውቃለች።ሌላው ‹‹ስሟቸው ወንድ የሰራውን ወጥ ››በሀድያ ባህል ወንድ ወጥ አይሰራም።ይሁን እንጂ ለእንደ እናንተ አይነት ልጆች የሚሆን ወጥ በወንድ ተሰርቷል። በመሆኑም ሴቶቹ ልጆች በወንድ የተሰራውን ወጥ ጣዕም ለማጣጣም ካላቸው ጉጉት የተነሳ ስራውን ያለመሰላቸት እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል ።ሌላው‹‹ ወንድ ››የሚለው ስሆሜ ተምሳሌታዊ ንግግር ነው። በዚህ አውድ ወንድ የሚለው ቃል ጀግና ፣ጎበዝ ፣ጠንካራ የሚል ትርጉም አለው።ዘፈኟም ጀግና የሰራውን ወጥ ስሟቸው በማለት የጥንካሬን ስሜት የሚፈጥር ዘፈን ነው የዘፈነችው።

በዚህ ጥናት አውድ መሰረት በክረምት የሚሰራው ስራ ከወትሮው ስራ አድካሚ እና አሰልቺ በመሆኑ ስራው በእንዴት ባለ ሁኔታ እንደሚሰራ ሀንዲሴ በጎመን ኩትኳቶ ላይ የሚከተለውን ዘፈን አቀንቅናለች።

(31) Hayya laalo hoo haa

Hagayyi baxo

Haleele hoo haa

Ha'mmaa shaanaa

Banxaa intoommo hoo haa

ሆ ብለን እንጫወት

የክረምትን ስራ

ሆ ብለን እንስራ

በአእምሾ ጎመን

ስርተን እንበላለን

(ሀንዲሴ በቀለ ፣ኩትኳቶ ላይ 5/06/04)

በሀድያ ገጠር አካባቢ ስራ የሚበዛው በክረምት ወቅት ነው።ስለሆነም የስራዎቹ አይነቶች ከሌሎች ወቅቶች ከበድ ስለሚሉ ሆ በማለት ስራዎቹ መሰራት እንዳለባቸው በግጥሙ ተጠቅሷል።"ሆ ብለን እንስራ "የሚለው ስንኝ በሁለት መንገድ ልናየው እንችላለን አንደኛው በአንድነት በጋራ ሆነን የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሲዘፍኑ የሚያሰሙትን ድምፅ"ሆ"እያልን፣እየዘፈንን፣እየጨፈርን የሚል መልእክትን የያዙ ናቸው።ሀንዲሴ ይህንን ዘፈን እንድትዘፍን ያነሳሳት ከዝናቡ ጋር ተያይዘው የሚመጡት ችግሮች ናቸው ብላለች።(5/06/04) ዘፈን በመዝፈናቸው የሚያገኙት ጥቅም በስራ የደከመውን አካላቸውን መንፈሳቸውን ማበረታታት እና በሰውነታቸው የተሰማቸውን ድካም መቀነስ ነው።በተጨማሪም በመዝፈናቸው እንደሚዝናኑና እንደሚደሰቱ ገልፀዋል።(ቃለ መጠይቅ፣ሀንዲሴ በቀለ፣አበራ-ስ አጢሶ፣ላጾ ኢደሞ፣05/06/04)

## 5.3 በስንደዶ ለቀማ ላይ የተዘፈኑ

በስንደዶ ለቀማ ጊዜ የተለያዩ ጉዳዮችን የያዙ ዘፈኖችን ያዜማሉ፡፡ከነዚህ መካከል ጥቂቶቹን በምሳሌነት ቀጥለን እንመለከታለን፡፡ቀጥሎ የቀረበውን ያዜመችው መረጠች ስዩም ትባላለች፡፡ይህ ዘፈን ዓርብ የካቲት 6/2004 በስንደዶ ለቀማ ጊዜ የዘፈነችው ነው፡፡

(38) Hadiyyi landi lachchaa lonsoommo

Banxaati intoommoo Lello lellinoommoo

Balli iinso waa'I hoore

የሀድያ ሴቶች ትምህርት እንማራለን

ሰርተን እንበላለን እንጫወታለን

ከቀን መኝታ እግዜር ይጠብቀን

እነዚህ ስንኞች የሀድያ ሴቶች ለፍተው ፣ሰርተው እንደሚኖሩ ይጠቁማሉ፡፡ትምህርትም እንደሚማሩ፣እንዲሁም ጨዋታን እንደሚጫወቱ ያመለክታሉ፡፡ይህም ሴቶቹ ጊዜያቸውን ባግባቡ የሚጠቀሙ መሆናቸውን መገመት ያስችላል፡፡ መረጠች ‹‹እኛ የሀድያ ሴቶች ትምህርትን የምንማረው በትምህርት ቤት ብቻ አይደለም፡፡››ህይወት በራሷ እውቀትን የምታስጨብጥ ትምህርት ቤት ነች፡፡( 9/06/04 ) የሚል ሀሳብም አላት፡፡

በሀድያ በገጠሩ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ለመኝታ ፍራሽ የሚያነጥፉት ከእንሰት ተክል በሚሰራው ጆባ ሲሆን ይህም የመኝታ ጆባ በማታ እንጂ በቀን አይነጠፍም፡፡በሀድያ ባህል የቀን መኝታ እንደ አስነዋሪ ነገር ይቆጠራል፡፡የቀን መኝታ ለአባውንቶች ወይም ለታመመ ሰው በመሆኑም አቀንቃኟ ‹‹ከቀን መኝታ እግዜር ይጠብቀን ››በማለት ያዘለ ዘፍናለች ፡፡

የሀድያ ሴቶች በቡድን ሆኖ የመስራት ባህል አላቸው፡፡እነርሱም ጌጀ፣ግላሴና፣ደዋ በመባል ይታወቃሉ ፡፡በአብዛኛውን ጊዜ ሴቶቹ በነዚህ የስራ አጋጣሚዎች ላይ በህብረት ሆነው ከሚዘፍኗቸው ዘፈኖች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

(32) Hadiyyoosilandi lelloo

Ta uwwayyi lelloo

Waallummi kollinnee lelloo

Woissa aadoommq lelloo

Ta uwwayyilelloo

Waaisa gungoommo lelloo

የሀድያ ሴቶች እንጫወት

ረ እኛ እንጫወት

በመግንበት አቅጣጫ

እንፈሳለን እንደ ውሃ

ኑ እንጫወት

እንደመበረቅ እንጮሀለን

(አበንሽ ኤርመኖ ፣ስንደዶ ለቀማ ማክሰኞ የካቲት 06/2004)

አቀንቃኟ ፡፡በመግንበት አቅጣጫ ፡፡በማለት የገለፀችው ሀሳብ ልንሰራ ያሰብነውን ወይም ያቀድነውን ስራ ለመስራት እንሰማራለን፡፡፡እንፈሳለን እንደ ውሀ፡፡በዚህ ስንኝ ውሀና ሴቶቹ ተነፃፅረው ቀርበዋል፡፡ውሀ ሁል ጊዜ የሚፈሰው ወደ ሚፈልገው አቅጣጫ ነው፡፡ሴቶቹም ልክ እንዲሁ ሊሰሩ የፈለጉትን ለመስራት በአንድ መንፈስ ሆነው ይሰማራሉ ፡፡አቀንቃኟ በዚህ አውድ ውሀን የተጠቀመችው የሴቶቹን አንድነት ፣ህብረት ለማሳየት ነው፡፡

ሴቶች ተሰብስበው ስንደዶን ሲለቅሙ እኛ እንዲህ ነን በማለት ጭፈራውንና ስራውን በማጣጣም እየዘፈኑ ማንነታቸውን ይገልፃሉ፡፡እኛ በስራም ሆነ በዘፈን በጨዋታ ልዩ ነን ለስራ አንለግምም ብርቱና ጀግኖች ነን ፡፡እየዘፈንን መስራታችን ደግሞ ከድሮም ያለ ነው አዲስ ነገር አይደለም፡፡እኛ እንግዲህ እንዲህ ነን በሚል ዘፈን የኛን ማንነት እንገልፃለን፡፡ (ቃለ መጠይቅ አሰሙሽ ሲባሞ፣የካቲት 10/2004)

(43) Enkoomis inkoomisa *2

Eraarem eraarem inkoomisa

Shaabe'l ooso landi ,,

Shumato uwweena ,,

Shoobbukki anno'l beete ,,

Sabukki anno'l beete ,,

እኛ እንዲህ ነን

ከጥንት ጀምሮ እንዲህ ነን

የሻቢ የልጅ ልጆች ,,

ሹመት ሊሰጡን ,,

በሰሙኑን ጊዜ ,,

እምቢ ባይ የሀድያ ልጆች ።

(አሰሙሽ ሲባሞ፣በቀለች ጎዳና፣ብርቱካን ፣ ስንደዶ ለቀማ፣ ማክሰኞ የካቲት 6/2004 )

ሴቶቹ በአንድነት ሆነው ‹‹እኛ እንዲህ ነን››በማለት ያዜሙት ከሌላ አካባቢ ለመጣ ሰው ማንነታቸውን የሚያሳውቁት በስራቸው ነው።ስራቸውን እየሰሩ ስለ እኛ ከሚነገረው ወይም ከሚወራው በላይ እንደምታዩን ነን በማለት አዚመዋል።‹‹ሹመት›› የሚለው ቃል የብሄረሰቡን ባህላዊ መተዳደሪያ ደንብ ያሳያል።ባህላዊ ሹመት አይነቶች የሚጠሩበት ስያሜዎች ፣ገራ አዝማች፣ቀኝ አዝማች፣ ኢማም፣ገራድ ጀላብ፣ወሻብ የመሳሰሉት በመባል መታወቃቸውን (አሰሙሽ፣በቀለች፣ብርቱካን የካቲት፣6/2004) ገልፀዋል።‹‹የሻቢ የልጅ ልጆች››የሚለው ስንኝ ሻቢ የሰው ስም ነው።የዚህም ሰው ልጆች ከላይ ከተጠቀሱት የሹመት ደረጃዎች ለሌሎች መስጠት የሚችሉ መሆናቸው የሚያሳዩን ስንኞች ሹመት ሊሰጡን በሰሙኑን ጊዜ በመባል የተጠቀሰው ስንኝ ነው። እንዲሁም የሀድያም ልጆች ሹመት እምቢ ባይ መሆናቸው በግጥሙ ተጠቁሟል።

በመቀጠል የሚኖሩበትን ወይም ያሉበትን ሰፈር በዘፈናቸው እንዲህ በማለት ያስተዋውቃሉ።

(44) Ni amba'l landi

Maassi biira yoo landi

Mat suume woncoommo

የኛ ሰፈር ሴቶች

የማስ ቢራ ሴቶች

ቋንቋችን አንድ ነው

ሴቶቹ የሚኖሩበትን ስፍራ ሳይቀር በዘፈኖቻቸው የጠቀሱት እንዱ መታወቂያቸው ወይም መለያቸው በመሆኑ ነው ። ‹‹የኛ ››የሚለው ቃል በራሱ ሴሎች መኖራቸውን እና ከሌሎቹ ጋር ልዩነት እንዳላቸው የሚናገር ነው። ስለሆነም የማስ ቢራ ሴቶች ከሌላው ሰፈር ሴቶች እንደሚለዩም ይገልፃል። እነዚህ የማስ ቢራ ሴቶች ‹‹ቋንቋችን አንድ ነው ››ሲሉ አንድነታችን የጠነከረ በአንድ ሀሳብ ላይ የፀናን ማለታቸው መሆኑ ያስታውቃል።

ሴቶቹ የማንነት መገለጫቸው የሆነውን ኃላ የሚጠቅስ ዘፈን አላቸው። ‹‹እኛ የሀድያ ሴቶች ከሌሎቹ ኃላ እንድንለይ ያደረገን ጠንካሮች፣ብርቱዎች፣ጎበዞች እና የስራ ሰዎች በመሆናችን ነው ።››(ቃለ መጠይቅ ፣እቴነሽ አብደላ፣አየለች ባቾሬ 18/06/04) በማለት የሚከተለውን ዘፈን ዘፍነዋል።

(45) Keemmaa'lli hadiyyioosi

Keemmaa'lli mooliilandi

Shaabe'l ooso landi

Inkoomis inkoomisa

Eraarem eraarem inkoomisa

የታላቁ የሀድያ ሴቶች

የትልቁ ዘር ሴቶች

የሻቤ የልጅ ልጆች

እኛ እንዲህ ነን

ከድሮም ያው ነን

በስንደዶ ለቀማ አውድ ፡፡እኛ የታላቁ የሀድያ ሴቶች ነን ፡፡የሚለው ስንኝ አንድም ሀድያ መሆናቸውን የሚናገር ሲሆን ፣አንድም ሀድያ የተባለው ጎሳ ከሌሎቹ ጎሳ ታላቅ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ በተጨማሪ ይህ ጎሳ ጥንትም ዛሬም በጥንካሬው ያለ መሆኑን ግጥሙ ይጠቁማል፡፡

በሀድያ ብሄረሰብ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ከማለዳው አስራ ሁለት ሰአት ላይ ስንደዶን ለመልቀም ውሀ ወደ አለበት ስፍራ ያቀናሉ፡፡ወንዶችም ሴቶችም ልጆች ተገርዘው ወደዚህ ስፍራ ይመጣሉ፡፡ ፡፡ወንዶቹ ቁምጣ ለብሰው ፀጉራቸውን ቅቤ ተቀብተው ብርድ ልብስ ለብሰው ይመጣሉ፡፡ሁለት ወንዶች በመሆን ሄቦንን እያሉ ወደ ሴቶቹ ይመጣሉ ሴቶቹም ስንደዶ እየለቀሙ ሄቦንን በማለት ይቀበሏቸዋል፡፡ከዚያም ወንዱ ለከንፈር ወዳጅነት የፈለጋትን ሴት ሄዶ ይይዛታል፡፡ ወንድየው የያዛትን ሴት ልጅ ከንፈር ቀዳዳ እስኪያወጣ ይስማታል፡፡በዚህን ጊዜ ቀዳዳ የወጣባት ሴት ልጅ በማህበረሰቡ ዘንድ ጎበዝ ፣ጀግና ፣ትልቅ ሴት በመባል ስሟ ይገናል፡፡(ቃለ መጠይቅ፣ጡሙሬ ሀንዳ፣6/6/04)፡፡

የሚከተለው ግጥም ለከንፈር ወዳጅነት የተመረጠችው ሴት የምትዘፍነው ነው፡፡

(49) Biide'l bee'ioosi

Beyyom waaronne

Ansool bee'l oosi

Anga amadoonne

ብርድ ልብስ የሌለው ወንድ

አጠገቤ እንዳይደርስ

አንሶላም የሌለው

እጄን እንዳይዝ

(በቀለች ንጋቱ፣ስንደዶ ለቀማ ላይ 22/06/04 )

በዚህ ግጥም ውስጥ ብርድ ልብስ  ይዞ ያልመጣ ወንድ ሴቷ ባለችበት አጠገብ እንዳይደርስ ተጠቅሷል።በባህሉ ወንዶች ብርድ ልብስ ይዘው መምጣት አለባቸውና ነው።ኤርሞ ኬኢሚሶ (22/06/04) ወንድየው የሴቷን ከንፈር ሲስማት በአንሶላ ወይም በብርድ ልብስ ተሸፍኖ ስለሆነ ብርድ ልብስ የግድ ይዞ መምጣት አለበት ብላለች።‹‹አጠገቤ እንዳይደርስ ›› የሚለው ስንኝ የሚያሳየን አንሶላውን ወይም ብርድ ልብሱን ይዞ ያልመጣ ወንድን እንደማትፈልግ ነው።

ወንድየው ብርድ ልብሱን ወይም አንሶላውንይዞ ካልመጣ እንዲህ ይሰደባል።

(50) Hiyyooyyo *2

Goollaanchi leela'l

Gamina mut angi

Gojina giir il

ሂዮ ሂዮ*2

አንተ ሆዳም ስግብግብ

ምሽቶ ለባ

አንተ ቡዳ

ብርድ ልብስ ወይም አንሶላ ይዞ ያልመጣ ወንድ በሴቷ እንደበት‹‹አንተ ሆዳም ስግብግብ›› ተብሎ ይሰደባል።የስድቡ ምክንያት ለሁለት አላማ ሲባል መሆኑን ኤርሞ ኬኢሚሶ፣(22/06/04) ነግረውኛል።‹‹አንደኛው የወንድየውን ስሜትና ፍላጎት ለማነሳሳት ሲሆን ፣ሁለተኛው ደግሞ ይህ ወንድ ወደፊት ከሴቷ ጋር በሚኖርበት ጊዜ የሚሰድበው ሰው እንኳን ቢኖር እንዴት ባለ ሁኔታ ተግዳሮቱን መወጣት እንደሚችል ለማየት ሲባል

ነው፡፡፡‹ሞሸላቃ ሌባ ››የሚለው ስድብ የሚነግረን ወንድየው ያያትና የወደዳት ሴት ልጅ ንብረትነቷ የአባቷ እና የእናቷ ናት፡፡ስለዚህ የአንተ ያልሆነችውን ሴት ልጃገረድ በእጅህ ለማስገባት ትጥራለህ የሚል እንድምታ አለው፡፡

‹‹አንተ ቡዳ›› በማለት የተጠቀሰው በማህበረሰቡ አመለካከት ቡዳ የሰውን ቀልብ የሚወስድ ወይም የሰውን ልብ የሚበላ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ኤርሞ ኬኢሚሶ(22/06/04)፡፡

አቀንቃኟ ወንድየው ሊበሽቅ የሚችልባቸውን የተለያዩ የማብሸቂያ ቃላቶችን በዘፈኗ ለንዝራለች፡፡

(52) Hiimina bagad bee'l jor

Hixina jajjar bee'l jor

Haqqina meesaan bee'l jor

Gatteena jagar bee'l jor

ለማታ ጦር የሌለህ

ለነገር ማጭድ የለህ

ለመናለሚ ጠገራ የለህ

ምታድርበት ቤት የሌለህ

በሀድያ ብሄረሰብ በገጠሩ አካባቢ የሚኖር አባወራ ወይም ወንድ ልጅ በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ጦር፣ማጭድ፣ጠገራ የመሳሰሉት ቁሶች ሊኖሩት ግድ ይላል ፡፡በመሆኑም በዘፈኑ የተገለፀው ወንድ እነዚህ ሁሉ ቁሶች እንደሌሉት እንዲሁም የመኖሪያ ቤት እንኳን የሌለው መሆኑ ተገልጿል፡፡በተለይ በገጠሩ አካባቢ ‹‹ጦር ››፣‹‹ለበኩር ልጅ ከአባት የሚወረስ ቅርስ ነው፡፡፡ የልጁ አባት ጦሩን ሲያወርሰው ጀግንነቱን ጭምር ይወርሳል ተብሎ ይታመናል በማለት ቃለ መጠይቅ ደስታ ደርጋሶ ፣(23/06/04) ነግሮኛል፡፡በዚህም የተነሳ በአንድ አባወራ ቤት ውስጥ ጦር ከሌለ አባወራው ጀግና አይደለም የሚል አመለካከት አለ፡፡ጦሩ በቤት ካለ ሰውየውን ጀግና ያስኘዋል፡፡በዚህ አውድ ‹‹ ጦር›› የጀግንነት ተምሳሌት ሆኖ በዘፈኑ ቀርቧል፡፡ሌላው ጦር የሌለው አባወራ ከብቶቹን ከአውሬ ፣ልጆቹንና ሚስቱን

ከጠላት ሊታደጋቸው አይችልም የሚል አመለካከት አለ።ስለዚህ አቀንቃኟ እንዳንተ ያለውን ወንድ ማን ይፈልጋል የሚል ሀሳብን የያዘ ዜማ አቀንቅናለች።

(128) Kaa Kaa

Goona uunjakkoone

Geesho'o tumookko

Goorjo'o xaaxookko

Guffa abuullookko yoommo

አንተ አንተ

ወንድ አይሟል

ጌሾ ይወቅጣል

ቤት ይለራል

መሬት ያርሳል።

በሀድያ ብሄረሰብ ባህል በሴቶች ከሚሰሩት ስራዎች መካከል አንዱ ጌሾ ወቀጣ ነው።በባህሉ የሀድያ ወንዶች የማይሰሯቸው ስራዎች እንደ ጌሾ መውቀጥ፣እንጨት መልቀም፣እንሰት ፍቀት እና የሴት ልብስ ማጠብ የመሳሰሉት ናቸው።ደስታ ደርጋሶ፣(21/07/04) ።‹‹ወንድ አይሟል›› የሚለው ስንኝ አንተም ወንድ ትባላለህ እንዳንተ አይነቱ ወንድ ለቤት ስራ እንጂ ለባልነት አይሆንም የሚል ሀሳብ አለው።በሀድያ ብሄረሰብ ጌሾ የወቀጠ ወንድ በማህበረሰቡም በሚስቱም የተናቀ ነው የሚል አመለካከት አላቸው። በመሆኑም አንተ ልክ እንደ ባሪያ የተናቅክ የተረሳህ ዘር ስለሆንክ በስራ ከማገልገል ውጭ ለባልነት ማንም አይፈልግህም የሚል ሀሳብ አለው ።

## 5.4 በወፍጮ ስራ ላይ የተዘፈኑ

የሀድያ ሴቶች ወፍጮ ሲፈጩ የዘራቸውን ሀረግ በመቁጠር ይዘፍናሉ።በተለይም እናቶች ልጆቻቸውን ሲያባብሉ፣ ወተት ሲንጡ ና በባህላዊ ወፍጮ እህልን ሲፈጩ የዘራቸውን ሀረግ በማንሳት እንደሚያዜሙ ተስተውለዋል። አንድ ሰው የሀድያ ተወላጅ መሆኑን ወይም የዘር ሀረጉ ሀድያ መሆኑን የሚያሳየን በስራ አጋጣሚዎች ላይ በሚዘፈኑት ዘፈኖች

አማኒይነት ነው።ዘፈኖቹ በእናቶቻችን ከልጅነታችን ጀምሮ በመደጋገም ሲዜሙ የቆዩ ናቸው።ዘፈኖቹ ለእኛ የሚሰጡን ጠቀሜታ ትዳርን ለመያዝ፣ጠላትና ወዳጃችን ለመለየት፣ማንነታችን ለማወቅና እንዲሁም እንደመታወቂያ በመሆን ያገለግላሉ። ስለ ዘር ሀረግ የተዜሙት ግጥሞች ከጠላት ማስመለጫ መሳሪያዎችም ናቸው።በሀድያ ብሄረሰብ ውስጥ የምትኖር በዘሯ ባርያ የሆነች ሴት በስራ ላይ የሚዜሙትን ዘፈኖች የማዜም ወይም የመናገር ባህል የላትም ምክንያቱም ማህረሰቡ ዝቅተኛ ቦታና ግምት ስለሚሰጣት ነው።(ቃለ መጠይቅ ላምቦ ሲባሞ ፣የካቲት 07/06/2004) ።

(81) Goshookimii agid

Gubeedaamuwwa

Goshakkamii lalleewi goonballamuwwa

ላሚቷን ሚያልቡ ባሪያዎች

ቅልጥማሞች ናቸው

ላሞቹም ጎታሞችም ናቸው

( ላምቦ ሲባሞ ፣ወፍጮ ላይ ፣07/06/04)

ላምቦ የተወለደችበት ዘር ሀረግ ባርያዎች እንደነበሯቸው፣ላሚቷ በባሪያዎች እንደምትታለብ እና ባርያዎቹም በጥሩ ሁኔታ እንደተያዙ የሚያሳየን ዘፈን ዘፍናለች።…ቅልጥማሞች ናቸው ።በማለት የተገለፀው ሀሳብ የባሪያዎቹን ምቾት ፣ ሁኔታ የሚናገር ሲሆን ፣በቤት ውስጥ ያሉትም ላሞች ሊታለቡ የደረሱ መሆናቸው በግጥሙ ተገልጿል።ላምቦ በዘፈኗ ልታስተላልፍ የፈለገችው መልእክት ባርያዎቹ የዘሮቿ ቤት ውስጥ ስራን እየሰሩ በጥሩ ሁኔታ እንደተያዙ እና ጥሩ ምግብ እንደሚመገቡ ነው።

አብዛኛውን ጊዜ በሀድያ ብሄረሰብ ውስጥ እናቶች በባህላዊ ወፍጮ እህል እየፈጩ ልጆቻቸውን ያባብላሉ።የሚያዜሙት ዘፈን ከዘር ጋር የተያያዘ ነው።ይህም የሆነበት ምክንያት ልጆን ስናይ ዘር እያየን በመሆኑ ነው ።በዚህም ምክንያት አዘውትረን ስለዘሮቻችን በማንሳት እናዜማለን እናንጎራጉራለን ። (ቃለ መጠይቅ ወ/ሮ ሸዋዬ ኦንቶሎ 7/06 04)

(79) Wo'o waachchaa firoo faradi

Wo'llanchchme feego anno'imii

Woshsha murahim waaro lommanni

Annilom qaraa eesem qarookko

ውሀ ሞኝተው ሚሸገሩ ፈረሶች

በምርኮ አሸናፊ አባቶች

ነገርን ቋጭተው ሚመለሱ

አባትህን ወልደው እኔንም ወለዱ

(ታደለች ጌታቸው፣ወፍሎ ላይ የካቲት 7/2004)

ታደለች ልጇን በጀባ ላይ አስተኝታ ሽሮ እየፈጨች የጥንት አባቶች እንዴት ባለ ሁኔታ እንዳለፉ በዜማ ስሜቷን ትገልፃለች።

በወፍሎ መፍጨት አውድ ‹‹ውሀ ሞኝተው ሚሸገሩ ፈረሶች ›› በማለት የተጠቀሰው ሀሳብ ውሀው ጦርነትን፣ መከራን ፣ችግርን ያሳየናል።ስለሆነም ሰልፈኞቹ በጦርነቱ ሜዳ ታግለው የሚያልፉ መሆናቸውን ያሳየናል። በጥንት ጊዜ የነበሩት አባቶቻችን በውሳኔያቸው ወይም የጀመሩትን ጉዳይ ከፍፃሜው የሚያደርሱ መሆናቸውም ተገልጿል።የአንተን አባት ወልደው እኔንም ወለዱ ›› በማለት የተገለፀው ሀሳብ የልጇ አባት የተወለደው ከእነዚህ አሸናፊዎች አባቶች መሆኑ፣እሷም ደግሞ ከጀግኖች አባቶች እንደተወለደች የሚገልፅ ነው።

መሲታውት ደግሞ የዘሯን ማንነት የሚያሳስብ ዘፈን በወፍሎ ስራ ላይ አዚማለች።

(94) Maidaayyi orde'i

Murte'i deeban eesem qarookko

Saayyi dallichchi'nne

Sammo qaramoo

የማልደፉ አርጶ

ቆራጡ ዴበኖ እኔን ወልዶኛል

እንደ በሬ ሻኛ

አናት ላይ ኖሬያለሁኝ

(መስታወት ላሊሾ፣ወናጐ ፣ሰኞ 12/006/ 04)

የማልደፉ አርጶ ልጅ ዴበኖ ሲባል እሱም በብሄረሰቡ ዘንድ ወይም በዘሩ ጀግና ቆራጥ መሆኑ ተገልጿል።አቀንቃኟ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚሰጣትን ቦታና ግምት ለመናገር በንፅፅር የተጠቀመችው ቃል የበሬን ሻኛ ነው።የበሬ ሻኛ በበሬው ላይ ከፍ ብሎ ስለሚቀመጥ እሷም ከዘሯ የተነሳ በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍ ያለ ቦታ እንደሚሰጣት ያመላከተችበት ጥበባዊ ክህሎቷ ነው።የተወለደችውም ከቆራጡ ዴበኖ ነው።ከቆራጥ ተወልዳ እሷም ቆራጥ መሆኗን በዘፈኗ ገልፃለች።

አቀንቃኟ የራሷን ዘር ከአእዋፋት ጋር በማነፃፀር ስለ ራሷ ያላትን አመለካከት የሚናገር ዘፈን ዘፍናለች።

(86) Cii'i adilli'n

Cuqulluusi'nne

Cawa'imii moolli beeto

እንደ ወፎች ንጉስ

እንደ ንስር አሞራ

የጨሊሞ ዘር ልጅ ነኝ

(ላምቦ ሲባሞ፣ወናጐ ላይ ፣ 07/06/04/)

አቀንቀኟ በዚህ የስራ ኢጋጣሚ ላይ ያዜመችው የራሷን ዘር እያሞጋገሰች ወይም እያደነቀች ነው።አቀንቃኟ ከወፍ ንጉስ ከሆነው ከንስር አሞራ ጋር የራሷን ዘር አነፃዕራ ለች። የወፎች ንጉስ የሆነው ንስር አሞራ በባህሪው ጠንካራ ፣ብርቱ ፣በከፍታ ላይ የሚበር ወፍ ነው።ይህም ወፍ በብሄረሰቡ አመለካከት የወፎች ንጉስ በመባል እንደሚታወቅ (ቃለ መጠይቅ ላምቦ ሲባሞ፣07/06/04) ገልፃልኛለች።ይህ ወፍ ንጉስ ለመባል ምክንያት የሆነው

በሰማይ ላይ ከሚበሩት አእዋፋት ተለይቶ ወደ ሰማይ ራቅ ብሎ መብረር የሚችል በመሆኑ ነው።አቀንቃኟ የእኔም ዘር ከፍ ካሉት በላይ ከፍ ያለ ነው በማለት አቀንቅናለች።

ላምቦ ሲባሞ የተወለደችበትን የዘር ሀረግ በማድነቅ ያቀነቀነችበት ዘፈን ነው።

(80) An qaramumok qaquulli mari`nne

Qurun ceefina qulluxsooko

Wo`o waachcha friroo faradi

Wo`llanchanne feegoo anno`l qarookko

የተወለድኩበት ሀረግ እንደቆርጥ ሲጋ

ሁሉም ያስጎመጀል እንደ ሰምበር ምላስ

ውሀ ቀንቶ ሚሻገሩ ፈረሶች

ከምርኩ አሸናፊ የተወለድኩኝ ነኝ እንኳንም ወለዱኝ

(ላምቦ ሲባሞ፣ወናጎ ላይ 07/06/04)

ቆርጥ ሲጋ ፣ሰምበር ፣ምላስ፣ሻኛ የተባሉ የሲጋ አይነቶች በህብረተሰቡ ዘንድ ተወዳጅ ፣ተፈላጊ ናቸው።ኢርሞ ኬኤሚሶ፣(07/06/04)። እነዚህም የሲጋ አይነቶች በማህበረሰቡ ዘንድ ታዋቂ ፣ጀግና ፣ሀብታም ቤት እንደሚገኙ ይታሰባል።አቀንቃኟ የተወለደችበትን ሀረግ ከቆርጥ ጥሬ ሲጋ እና ሰምበር ምላስ ጋር በማነፃፀር አዚማለች።በዚህ ዘፈን ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት የአቀንቃኟ የዘር ሀረግ ምን ጊዜም ቢሆን የሚፈለግ ፣የሚወደድ መሆኑ ነው።በመቀጠልም ላምቦ የባሏን ጀግንነት በተምሳሌት እየገለፀች የሚከተለውን ዘፈን አቀንቅናለች ።

(89) Gooqqi illigenne

Gaallichchi buudine

Gobbukkimi nafara

Gosaanimii itoone

Gatee yillehe

በአውራ ጎዳና ፊት ለፊት

በአውራሪስ ቀንድ

ያጌጠ ደጆአፍ

ቡዳ አይብላህ

ቱቱቱ!በሉት ፈጣሪ ይሰውርህ

አቀንቃኟ የባሏን ቤት በአውራሪስ ቀንድ ያጌጠ ደጃፍ መሆኑን በዘፈኗ ጠቁማለች። ይህም ደጃፍ አይን አይግባህ ፈጣሪ ይሰውርህ ተብሎ ተዘፍኖለታል።አውራሪስ ትልቅ ቀንድ ያለው የዱር አራዊት ሲሆን ቀንዱንም ማህበረሰቡ ለጌጣ ጌጥ መስሪያ እንዲሁም ቆዳውን ደግሞ አውራሪሱን የገደለው አባወራ በቀብር ስነስርአት ጊዜ ልክ እንደ ፎጣ ትከሻው ላይ ጣል ያደርገዋል።ደስታ ደርጋሶ፣(25/07/04)።በገጠሩ አካባቢ አውራሪስን የገደለ ሰው ጀግና፣ የማይበገር ሰው ተብሎ ይቆጠራል።የአውራሪስ ቀንድ ከጌጥ ባለፈ ለህብረተሰቡ አገልግሎትን ይሰጣል። ጠቀሜታውም የቤቱን አባወራ ከአይን ይጠብቃል የሚል እምነት አላቸው።(ቃለ መጠይቅ፣ኤርሞ ኬኢሚሶ፣22/06/04)።

በአውዱ የአውራሪስ ቀንድ ሰው ሊያየው በሚችልበት በቤቱ ምሰሶ ላይ ከፍ ብሎ ተሰቅሏል።ይህም የሚሆንበት ምክንያት በዚያ ቤት ውስጥ የሚኖረው አባወራ ጀግንነቱን የሚያሳይበት ተምሳሌት በመሆኑ ነው። በብሄረሰቡ ባህል እንደሚታወቀው የአውራሪስ ቀንድ ሁሉም ቤት እንደማይሰቀል(ቃለ መጠይቅ፣ደስታ ደርጋሶ፣25/07/04) ተናግሯል።ቀንዱ የሚሰቀለው ጀግና ያለበት ቤት ነው።አቀንቃኟ‹‹ቡዳ አይብላህ ››በማለት የዘፈነችው ዘፈን የአውራሪስ ቀንድ በቤቱ አናት ላይ የሰቀለን አባወራ በሰፈሩ ያሉት ሰዎች ለማድነቅና ለማሞገስ ወደ ቀዬው ያመራሉ በመሆኑም ከሚመጡት ሰዎች መካከል ‹‹ቡዳ››ሊኖር ይችላል በሚል ስጋት በማህበረሰቡ እምነት እና ልማድ መሰረት ሁሉም ሰው ምራቃቸውን እንትፍ እንትፍ እንዲሉ የሚነግር ዘፈን ዘፍናለች። ሌላዋ አቀንቃኝ ደግሞ የወንዱን ጀግንነት የሚያወሱ ጉዳዮችን በማንሳት አወዳሽ ዘፈንን ዘፍናለች።

(99) Dut wocu woshsha

Dii mi'sa gindo

Karoo foolisa

Kooti iim leenco

Faradoo daanna

Feeri iim leenco

በሁሎች የተማከሩበት ነገር

እንደ እና ቤት ታደርጋለህ

የሚያስረውን ፖሊስ

ኪታች ወደ ላይ ትንጠምጣለህ

የሚፈርደውን ዳኛ

በንቀት ታፈጥበታለህ

(መሰረት ኢርሲሞ፣ወናሙ ላይ 7/5/04)

በወናሙ መኖሬኤት እውድ ተጠቃሽ የሆነው ወንድ የእቀንቀኚ ባል ነው፡፡አብዛኛውን ጊዜ በስራዎቼ ላይ አዜማለሁ የማዜመውም ስለ ባሌ ነው፡፡ምክንያቱም የእሱ ጀግንነት እና ትብዝና ለእኔ ኩራቴ ስለሆነ ነው ። (ቃለ መጠይቅ መሰረት ኢርሲሞ 7/5/04)

ከላይ በተጠቀሰው ግጥም ውስጥ ‹‹እንደ እና ቤት ታደርጋለህ››በመባል የተገለፀው ሀሳብ የባሏን ጀግንነት የሚያሳይ ነው። ጠላቶች በሰውየው ላይ ያደረጉትን ማንኛውም አይነት ሴራ እና ደቦ እንዳልነበረ አድርጎ እንደሚያፈራርሰው ተዜሟል፡፡በተጨማሪም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሰረት የመጣበትን ክስ ፣እንዲሁም አሸፈረኝ በማለት ፖሊሱንም ሳይቀር ከምንም የማይቆጥራቸው መሆኑ እና ልበ ደንዳና ፣የማይበገር ጀግና ፣የሚያስመካ ኩሩ ባል እንደሆነ የሚያትት ዜፈን ዘፍናለች።

ዲሾ ላሊሾ በባህላዊ ወፍጮ ማሽላ እየፈጨች ስለ ልጇ መዳር አዝናና ተከዛ የሚከተለውን ዜማ አቀንቅናለች፡(05/05/04)

(95) Landi ayyanee hadiyyane uungo

Annabbaayyi mah uwwukko

Allaachchi beyyonne mahikkito

Uungo uungo suuxo

የሀድያ ማንነት ያላት ሴት

አንቷ ምን ስጦታ ሰጣት

በእረኝነት ስፍራ እንዳት ቁልሽ

በርቺ ኮሶ እንዳትፈራ።

በወፍጮ መፍጨት አውድ የሀድያ ሴት ልጅ ኮሶ ልትጠጣ መሆኑ በዘፈኑ ተገልጿል።ይህችም ሴት በእረኝነት ስፍራ ውላ መምጣቷን የሚያሳየን ስንኝ ‹‹በእረኝነት ስፍራ እንዳት ቁልሽ ››ተብሎ የተጠቀሰው ነው። በሀድያ ባህል ሴት ልጅ ከመገረዟ በፊት ኮሶ እንድትጠጣ ይደረጋል።ስትገረዝ ቤተሰብ፣ጎረቤት፣ጓደኞቿ በቤቷ ውስጥ በመምጣት ዘፈንን እየዘፈኑ ስለ ቁስሉ እንዳታስብ እና እንዳትጨነቅ ያደርጓታል።በማህበረሰቡ እምነት ሴቶች ሲገረዙ ቢያማቸውም እንኳን እንዲጮሁ አይፈቀድም ።‹‹ስትገረዝ የጮኸች ሴት በማህበረሰቡ ትናቃለች።››(ቃለ መጠይቅ፣ዲሾ ላሊሾ፣05/05/04)።በቤቷ ያሉት ታዳሚዎችም ስለ እሷ ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ ይሆናል።በመሆኑም ወደፊት በህይወቷ ላይ የሚገጥሟትን ተግዳሮቶች መወጣት የማትችል ተደርጋ ትታሰባለች።ከታዳሚዎቹ መካከል የሚፈልጋት ወንድ ቢኖር እንኳን ይተዋታል።ሌላው የኮሶ መጠጣቷ ትዕምርት ስንብት መሆኑንም ያመላክታል።ስለዚህ አቀንቃኟ ይህ ከመሆኑ በፊት ልጇን‹‹ እንዳትፈራ በርቺ ››በማለት የሚያበረታታ ዘፈን ዘፍናለች።በሀድያ ባህል እንዲት ሴት ልጅ ኮሶ ስትጠጣ ከአባትም ሆነ ከእናቷ እንዲሁም ከዘመዶቿ ስጦታ ያደርጉላታል።ከዚህም የተነሳ የልጅቷ እናት የሰጣትን ስጦታ ለማወቅ ካላት ጉጉት የተነሳ ይመስላል‹‹አንቷ ምን ስጦታ ሰጣት›› በማለት ያቀነቀነችው።

## 5.5 በወተት መናጥ ጊዜ የተዘፈኑ

በወተት መናጥ አውድ ወ/ሮ ሸዋዬ ከወተት ጋር ግንኙነት ያለውን ዜማ እንደሚከተለው አዚመዋል።

(110) Ado firee *2

Buurii bire eeboo firee

Adii ojjgodane

Salalii mexeredane

ወተት ሆይ ቅቤ ይውጣህ

ቅቤ በገንዘብ ይግዛል

ወተት በእንስራ ይናጣል

በአይብ እቃ አይብ ይቀመጣል

(ወ/ሮ ሸዋዬ አንቶሉ፣ወተት መናጥ 13/06/04 )

አቀንቃኟ በእንስራ ውስጥ ያለውን ወተት በስሙ እየጠሩት ‹‹ወተት ሆይ ቅቤ ይውጣህ›› ይሉታል።በሆድያ ባህል ወተት አይሸጥም ወተትን መሸጥ ፀጋ ና በረከት ያስገፍፋል የሚል እምነት አላቸው።ቅቤ ግን ስለሚሸጥ አቀንቃኟ ቅቤ በገንዘብ እንደሚገዛ ለማሳየት ገንዘብን ከቅቤ ጋር አያይዘውታል።ከወተቱ መናጥ በኋላ የሚገኘውንም አይብ ማስቀመጫ እንዳለው በዜማቸው ጥቆማ ሰጥተዋል።

በሆድያ ብሄረሰብ አሁንም ድረስ ከወተት ጋር በተያያዘ መልኩ የሚታመንባቸው እምነቶች አሉ።ለአብነት ያህል ለመጥቀስ ‹‹ሴቶች ትኩስ ወተት አይጠጡም››የተባለበት ምክንያት ጓሚቷን የምታልባት ሴት ስለሆንች እዚያው እያለበች ወተቱን ትጨርሰዋለች በሚል ፍርሀት ነው።ሸዋዬ አንቶሉ፣(13/06/04)።

በሆድያ ባህል ወተቱን የሚንጡት እዛውንቶች ከሆኑ ዝም ብለው አይንጡም ያንጎራጉራሉ፣በሁካቸው ወደማያውቁት አለም ይገባሉ። ከነባራዊው የህይወት ልምምድ የተለየ በመሆኑ ‹‹ያለበትን ሁኔታ እንድንረሳ ያደርገናል።››ሸዋዬ አንቶሉ፣(13/06/04)።

አቀንቃኟ ወተት እየገፋው ልጆን አቅፌ እያባበልኩት አዜማለሁ ምክንያቱም እኛ ከወላጆቻችን የሰማነውን ወይም የተመለከትነውን የታሪክ አደራ በዘፈን አማካይነት ለልጆቻችን ማስተላለፍ ግዴታ ስላለብን ነው።በተጨማሪም በቤት ውስጥ ቁጭ ብዬ ስራን መስራት ስጀምር ወደ አእምሮዬ የሚመጣው የልጆን ዘር በዜማ ማንጎራጎር ነው። (ቃለ መጠይቅ፣ ደመቀች ባቾሬ ፣13/ 06/2004) ።

(100) Ororo ororo odem ororo

Weerei' oosichcho oroo

Wiit kullee'llane oroo

Maalda'y aduunchcho ororo

እሹሩሩሩ አሁንም እሹሩሩ

የዊሬ ልጆ እሹሩሩ

በዊት ዙሪያ ላይ

የማልዳዬ ድመት ነህ

( ደመቀች ባቾሬ፣ ወተት መናጥ ና ልጅ ማባበል 13/06/04 )

አቀንቃኟ ወተት እየገፋች ልጇን አቅፋ ‹‹እሹሩሩ ››በማለት ታባብለዋለች ቀጥላም ‹‹የዊሬ ልጆ እሹሩሩ ›› በማለት ጎሳውን ለልጇ በዜማ ትነግረዋለች።‹‹ዊት›› በጥንት ጊዜ ጦርነት የተካሄደባቸው ስፍራ ስም መጠሪያ ነው።(ቃለመጠይቅ፣ደመቀች ባቾሬ፣13/06/04) ማልደዩም ሀገሩ የተወለደበት ግንድ ወይም የአያት ስም ነው።ማልደዩ በምሻ ወረዳ የታወቀ ሰው በመሆኑ ነው በዘፈን ውስጥ የመጣው።‹‹ድመት›› የሚለው ቃል አንድም ቅልምጫ ሲሆን አንድም ደግሞ ድመት ወተት የምትጠጣ የቤት እንስሳ ስለሆነች አንተም እንደሷ ወተት ጠጪ ስለሆንክ የማልደዬ ድመት ነህ ትለዋለች።ልጇ ወተት ስለሚጠጣ ከድመት ጋር አነፃፅራዋለች።ሌላው አቀንቃኟ የማልደዬ ድመት ነህ ስትል ስለ ድመቷ ለመናገር ፈልጋ አይደለም።በዚህ ዘፈን ውስጥ ድመት ተምሳሌት ነች።የነብር ና የአቦሸማኔ ዝርያ በመሆኗ የማልደዬ ዘር ተደርጋለች። ነብርና አቦሸማኔ በጣም የሚፈሩ፣ ሀይለኞች አትንኩኝ ባዮች ናቸው።ስለዚህ አቀንቃኟ የማልደዬን ዘሮች የአቦሸማኔ ዘሮች በማድረግ ከልጇ የዘር ሀረግ ጋር በማያያዝ ዘፍናለች።

በመቀጠል አቀንቃኟ ወተቱን እየገፋች ልጇንም በማባበል ያዜመችው ዘፈን የሚከተለው ነው።

(104) Ayyi baditaatee

Atimii ororo geej man weere'l

Keesam qarookoo

Maldayi hadumii

Keesem qarookkoo

Oo! dillaam weerei' keesem quroolko

Oo! geejji weere keesem qarooiko

ማገን ፈርተህ

ትልቁ ዌሬ

አንተን ወለዷል

የማልደይ ሀዱሚ

አንተን ወለዷል

ያ ኃያሉ ዌሬ ወለደህል

ያ ታላቁ ዌሬ አንተን ወለደህል

አቀንቃኟ ልጇን እቅፏ ወተት እየገፋች ስለ ልጇ የዘር ሀረግ ታዜማለች።“ያ ሀያሉ ዋሬ ወለደህል” በሀድያ ብሄረሰብ “ዌሬ”በመባል የሚታወቀው አንድ ጎሳ ነው።ደመቀች ልጇም ሀያል ከሚባለው ጎሳ እንደተወለደ በዜማ ለልጇ ትነግረዋለች።ዌሬ የተባለው ጎሳ በሀድያ ብሄረሰብ ውስጥ ተፅእኖን መፍጠር የሚችል !የበላይነት ያለው! የሚፈራ ጎሳ መሆኑን ለማመላከት አዜማለች ።

በእላት ተደራርበው መምጣታቸውን የሚያወሱ ግጥሞች ተዚመዋል፡፡

(107) Dim girachchot ororo

Doona'l masqalli ororo

Dido'o ganaate ororo

Waaro kall'ii ororoo

Weerincho ororoo

Ka ibeeto ororo dirii waarakko

Kaba diriire anim baxoomo

ትንሹ ቡሄ ደርሷል

ትልቁ መስቀል ተቃርቧል

መፈጢው ገኛ ነው

ድግሱ ደርሷል፡፡

የዋሪ ልጆ እሹሩሩ

ልጄ እንቅልፍህ መጥቷል

አሁን ተኛ ስራዬን ልስራ

በዚህ ግጥም መስቀል ትልቅ በእል መሆኑ ፣ቡሄ ደግሞ ትንሽ መሆኑ ተገልጿል፡፡አቀንቃኟ ‹‹ትልቁ መስቀል ›› በማለት የዘፈነችው ዘፈን በሀድያ ብሄረሰብ የመስቀል በእል በተለየ ሁኔታ ስለሚከበር እና የመስቀልን በእል ሁሉም ማህበረሰብ የሚያከብረው በመሆኑ ነው፡፡የመስቀል በእል በእመት አንዴ በተለይም የክርስትናን እምነት በሚከተሉ በሀድያ ብሄረሰቦች ዘንድ በድምቀት የሚከበር ባህላዊ በእል ነው፡፡በእሉም ሲከበር የሚያስፈልጉት የምግብ አይነቶች በርበሬ፣ቅቤ፣ቃሪቦ ፣ቆጮ ፣ቡእላ ፣እተካና ፣ናቀሮ (ዳጣ) የመሳሰሉት በሴቶቹ ይዘጋጃሉ፡፡(ቃለ መጠይቅ፣ደመቀች ባቾረሬ፣13/06/04)፡፡ትንሹ ቡሄ በማለት የተገለፀው ሁነብ ለዚህ በእል ዘግጅት እምብዛም የማይደረግለት ስለሆነ ትንሹ በማለት ተዚሟል፡፡ከሁለቱ በእላት በኋላ የገና በእል እንዳለ ተገልጿል፡፡ በእነዚህ በእላት ደግሞ ድግስም እንደምትደግስ ለማመላከት ‹‹ድግሱ ደርሷል ››በማለት የሚያጋጥማትን የስራ ጫናዎች ግንዛቤ ውስጥ በመክተት እንጎራጉራለች፡፡

ደመቀች የልጇን እንቅልፍ መምጣት እየነገረችው ‹‹ብል ተኛ አሁን ››በማለት እኔም ወደስራዬ ልሰማራ መጪው በእል ድግስ ስላለብኝ አሁን ዘፈኑም ይብቃህ ተኛ ትለዋለች።ደመቀች ልጇን ማባበሏን እንደ አንድ ስራ ያልቆጠረችበት ምክንያት ዘፈኑ በምናዊ አዲስ ወደ ሆነ አለም ይዟት ስለሄደ ነው። ከዚያ አለም ስትባንን ስራዬን ልስራ በማለት አዚማለች ።

በሀድያ ብሄረሰብ ብዙውን ጊዜ ሴቶች ካገቡ በኋላ በባሎቻቸው ስም ነው የሚጠሩት ምክንያቱም ሴቶቹ በባላቸው ስለሚተዳደሩ ነው ።የዘር ሀረጉን ቆጠራ የሚያደርጉት በባለየው በኩል ያለውን ዘር ነው። (ቃለ መጠይቅ ፣አቶ ከበደ በላቸው ፣የካቲት 9/06/04)።ሌላዋ አቀንቃኝ ደግሞ የባሏን ትውልድ ሀገር እየጠራች ልጇን ታባብላለች።ልጁን የማባበለው ሲያለቅስ ወይም እንዲተኛልኝ ስል ብቻ አይደለም ። የትውልድ ቦታውንና የዘር ሀረጉን የምንገረው በማባበልና በዜማ በመሆኑ ነው።በተጨማሪም አሁን ካለሁበት ከህይወት ውጣ ውረድ ለመላቀቅና መንፈሴን ለማደስ ጭምር ነው። (ቃለ መጠይቅ፣ እቴነሽ ኤርሲዶ፣9/06/04)

(117) Leerango ciila ororoo

Leeroo anni beeto ororoo

Leilishshi landi ciilaa ororoo

Leemoosichchi beeto ororoo

የሌራንጎ ልጅ

የሌር አባት ልጅ

የሌልሽ ሴት ልጅ

የሌሞ ተወላጅ

(እቴነሽ ኤርሲዶ ፣ወተት መናገ 9/06/04)

በወተት መናገ አውድ የተጠቀሰው ህፃን ልጅ የሌሞ ወረዳ ተወላጅ ነው።ይህ ህፃን የትውልድ ሀረጉን እንዲያውቅ የአባቱን ስም አይደለም የሚነገረው።የስም ጉዳይ ሳይሆን በልጂ ትውልድ ሀረግ ውስጥ ለሀገር አንድ ትልቅ ጀብዱን የሰራ፣ ለመጪው ትውልድ

የሚሆን ቅሬታን ያቆየ ፣በህብቱ የታወቀ ሰው ስሙ ይጠራል ፡፡(ቃለ መጠይቅ፣እቴነሽ ከበደ፣9/06/04) ፡፡ይህም የሆነበት ምክንያት ልጁ ወደፊት ሲያድግ የአባቱን ፈለግ ተከትሎ እሱም የሀገሩን ስም በማስጠራት የራሱን ገድል እንዲጋደል ሲባል ነው፡፡

ሌላዋ አቀንቃኝ ልጃቸውን አቅፈው ወተት እየናጡ ስለ ልጃቸው የሚያወሳ ዘፈን እንደሚከተለው ዘፍነዋል፡፡

(115) Cilaa ororoo *2

Ajaabantitee ororoo

Adom agootto >>

Ganumannakuree >>

Ganaa waaroommo

Gabaalli shoginnee

ልጅ እሹሩሩ *2

ልጅ እትዋደድ

ወተት ትጠጣለህ

ነገረኝ የገረፈህን

ይመታል በእኔ

በዱላ በእርጩሜ

(ሙሉነሽ እርገን ፣ወተት መናጥ 29/06/04)

በዚህ አውድ የአቀንቃኟ ልጅ ያለቅሳል፡፡ሙሉነሽ ልጃቸውን የሚያባብሉት ምን እንደሚፈልግና ምን እንደሆነ ለማወቅ ሲሉ ነው፡፡‹‹ነገረኝ የገረፈህን ›› የሚለው ስንኝ ልጁን ሊገርፈው የሚችል ብዙ ነገር እንዳለ ጥቆምታ የሚሰጥ ነው፡፡ ለምሳሌ ራብ ፣ ሀመምና ጠላት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለእነዚህ አይነቶች ችግሮች እኔ ተገን እሆንሀለሁ የሚል ዘፈን ዘፍነዋል፡፡

በሀድያ ብሄረሰብ ሴቶች እናቶች ለባሎቻቸውና ለልጆቻቸው ከሚያዘጋጁቸው ባህላዊ ምግቦች እና መጠጦች መካከል እንደ አተካና፣ቡሌንታ፣ቦርዴ፣ሻሜታ እና ቆሎ ወዘተ

የመሳሰሉት ናቸው።አቀንቃኟ ወተት እየገፉ እነዚህም ምግቦች በምን እንደሚሰሩ የሚጠቁም ዘፈን አቀንቅነዋል።

(113) Gardamma endaat

Goo'n bullo salloommo

Ayyidaa'l so'o tumoommo

Awwodo'l so'l inqalo

Oosina haantoommu

ዘንጋዳ ጨምረን

ለባሎቻችን ቡሌንታ እንሰራለን

ለቦርዴ ገብስ እንወቅጣለን

የአወዶ ገብስ ቆሎ

ለልጆቻችን እንቆላለን

(ወረ' ሸዋዬ እንቶሎ፣ወተት መናጥ 13/06 /04)

አቀንቃኟ ወተት እየገፉ እኛ በማለት ያቤሙት መሳው የሀድያን ብሄረሰብ ሴቶች በማሰብ ነው።፡ቡሌንታ፡የተባለው የሀድያ ባህላዊ ምግብ ሲሆን ፤ከጎመን፣ ከቆጮ ከገብስ የሚሰራ የምግብ አይነት ነው።ሸዋዬ ግን ዘንጋዳ በተባለው የእህል አይነት ጨምረው እንደሚሰሩ በግጥሙ ገልፀዋል።ይህም ምግብ የሚዘጋጀው ለወንዶች ወይም ለባሎቻቸው መሆኑ ተጠቁሟል።ቦርዴ የተባለው ባህላዊ መጠጥ በገብስ እንደሚዘጋጅና ገብሱም በሴቶቹም እንደሚወቀጥ ተገልጿል።በተጨማሪም ለልጆቻቸው፡የአወዶ ገብስ ፡ቆሎ እንደሚቆሉ ተገልጿል።አወዶ ማለት ሀይል ሰጪ የገብስ አይነት ሲሆን በደጋ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች የአየር ንብረቱን ለመቋቋም የሚበሉት ነው።(ቃለ መጠይቅ፣ ሸዋዬ እንቶሎ፣13/06/04)፡፡

## 5.6 በእንጨት ለቀማ ላይ የተዘፈኑ

በሀድያ ብሄረሰብ ሴቶች ለጃገረዶች በመስክ ስራ ላይ ከሚከውኗቸው ስራዎች መካከል አንዱ እንጨት ለቀማ ነው።ሴቶቹ እንጨት ለቀማ ወደ መስክ ሲሄዱ የክት ልብሳቸውን ለብሰው፣ጌጣቸውን አድርገው ፣ተቀባብተው ነው።

በእንጨት ለቀማ እውድ እንጨት ለመልቀም እና ውሀ ለመቅዳት ወደ መስክ ስለ ወጣች ለጃገረድ ውበት የሚገልፅ ዘፈን ተዘፍኗል።

(126) Ababattee niyyaayya niina ababatte *2

Haqqina matteena ababattee

Haara edde'llamo >>

Wo'ina matteena >>

Worqa edde'llamo >>

አበባ ናት እህታችን አበባ ናት*2

እንጨት ልትለቅም ስትሄድ

ሀር ትለብሳለች

ውሀ ልትቀዳ ስትሄድ

ወርቅ ትለብሳለች

( ፈዲላ ረዲን፣እንጨት ለቀማ 18/06/04)

አቀንቃኟ ስለ እህቷ ቆንጆና ፣ውበት ለመናገር የተጠቀመችበት በአቅራቢያዋ የምታውቀውን አበባ ነው። አበባ ውጪው የሚያምር፣ ጥሩ መዓዛ ያለው ነው።ቆንጆ በመሆኑ ትኩረትን ይስባል።የቢች ሴት ውጫዊ ገፅታም ልክ እንደዚህ አበባ ነው በማለት አቀንቅናለች።ይህች ሴት ለይ እንጨት ስትለቅም የምትለብሰው የልብስ አይነት ሀር መሆኑ በዜማ ተገንፉንፏል።።ሀር። በሀድያ ብሄረሰብ ባህል በሴቶች የሚወደድ ልብስ ነው። አብዛኛውን ጊዜ በመስክ ስራ ላይ ሴቶቹ ተውበውና አምረው መታየት የሚፈልጉት በዋናነት እጮኛ ለማግኘት ወይም የሚወዱትን ወንድ ለማግኘት ነው።(ቃለ መጠይቅ፣አያንቱ አሼቦ፣22/06/04)።አቀንቃኟ እህታችን ወርቅና ሀር ልብስ ለብሳለች ምንም የሚጎድላት

ነገር የለም ስለዚህ አበባ ናት በማለት አቀንቅናለች።እናም እንደዚች ያለች ቆንጆ ልጃገረድ ምን እንደምትበላና እንደምትጠጣ በቀጣዩ ዘፈኗ ገልፃለች።

(127) Ittamokki

Injeeram

Agamokki

Aranchaata

እሷ የምትበላው

የጤፍ እንጀራ ነው

እሷ የምትጠጣው

የማር ጠጅ ነው።

አቀንቃኟ የጤፍ እንጀራ እንደምትበላ ፣ይህችም ልጃገረድ የማር ጠጅ እንደምትጠጣ በዘፈኗ ገልፃለች።የጤፍ እንጀራ እና የማር ጠጅ በሀድያ ብሄረሰብ ዘንድ የወትሮ ምግብ እና መጠጥ አይደሉም።የጤፍ እንጀራ እና የማር ጠጅ የሚዘጋጀው እንደ ሰርግ፣አመት በአል ባሉት ቀናቶች ነው።(ቃለ መጠይቅ ፣ፈዲላ ረዲን፣18/06/04)። ሌላው የልጅቷ ቤተሰቦች ሀብታሞች ያላቸው መሆናቸውንም ያሳየናል።

ሌላዋ አቀንቃኝ ደግሞ ዘፈኖቿ ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው።ይሁን እንጂ ዘፈኖቹ የማበረታቻንም ስሜት የያዙ ናቸው።

(129) Ashsham haqqaano *4

Ashsham haqqaano

Afarenne sho'lle'ee ashsham

Doo'm wo'l siigeeda

Daadewsoo meesaana

ኖር የሚገዶ እንጨት ለቃሚዎች

አሻም እንጨት ለቃሚዎች

በጀርባችሁ አይክበድ

የሚካውን እንጨት

የሚበጣጥሰው ጠገራ ነው።

(ክዷ የካቲት 9/2004 በእንጨት ለቀማና ሸክም ላይ )

እንጨት ለመሸከም በመንገድ የሚሄዱትን የስራ ባልደረቦቿን ‹‹አሻም የማገዶ እንጨት ለቃሚዎች›› ትላቸዋለች ክዷ ጓደኞቿ ስለ ሚሸከሙት እንጨት ሀሳብ እንዳይገባቸው ከመጀመሪያ ሰላምታን በማቅረብ እና አይዟችሁ ትላቸዋለች። በተጨማሪም‹‹በጀርባችሁ አይክበድ››የሚለው ስንኝ ገና የምትሸከሙትን እንጨት እያሰባችሁ አትጨናነቁ የጫካውን እንጨት የሚቆራርጠው ጠገራ የተባለው መቁረጫ (መጥረቢያ) ነው።ስለዚህ አትፍሩ በማለት የማበረታቻ ዜማን አቀንቅናለች።ክዷ ይህንን ዘፈን እንድትዘፍን ያነሳሳት ጓደኞቿ ከሸክሙ ክብደት የተነሳ እንዳይሰላቹ ፣እንዳይደክሙና እንዳይታክቱ ለማድረግ መሆኑን ገልፃለች። (ቃለ መጠይቅ ክዷ አንቶሎ፣የካቲት 29/2004)።

(130) UUllam oonteena ashsham

Iyyiinoom gudeer

Adi I ijaajo aa'nnaatii

Atoota iiinseena

ገርላችንን ለማክበር

ግንድ እንሸከማለን

የመንግስት መመሪያ የተቀበልነው

ምርቃችንን ለማሳደግ ነው።

(ክዷ አንቶሎ፣እንጨት ሸክም 9/06/2004)

አቀንቃኟ እንጨትን ተሸክማ ወደ መንደሯ በመሄድ ላይ እያለች ያዜመችው የቃል ግጥም ስለ ግንድ ጠቀሜታ ነው።በስራ አጋጣሚው ላይ አቀንቃኟ ሴቶች ግንድ የሚሸከሙት

ለምን አላማ መሆኑን እና ስለ እንጨት አገልግሎት የገለፀችበት ነው። ሴቶች የቤታቸውን አጥር ለማጠር ግንድ እንደሚሸከሙ በዘፈኑ ተጠቁሟል።በተጨማሪም ክቧ ይህንን የቃል ዜማ በማዜሟ የሚሰማትን ስሜት እና ጠቀሜታውን በተመለከተ የተናገረቸው፤አብዛኛውን ጊዜ ስራዎቼን ስሰራ አቀንቅናለሁኝ የማዜምበትም ምክንያት አንድም ደስ ሲለኝ ፤አንድም ስራውን በምሰራበት ወቅት የሚሰማኝን ድካምና መሰላቸት ላለማዳመጥ ስል ነው ብላለች።

አቀንቃኟ ‹‹የመንግስትን መመሪያ የተቀበልነው ›› በማለት ያነሳችው ሀሳብ የደን ምንጠራ መስፋፋት ያስፈለገበት ዋነኛው ምክንያት መሬቱ ለእርሻ ምርት እንዲሆን ነው።እኛም ይሄንን የመንግስት መመሪያን ተቀበለን ምርታችንን ለማሳደግ ነው በማለት በዘፈኗ አቀንቅናለች።

## 5.7 በእረኝነት ስፍራ የተዘፈኑ

አብዛኛውን ጊዜ በገጠሩ አካባቢ የእረኝነትን ስራ የሚሰሩት በእድሜ አነስ ያሉ ሴቶችና ወንዶች ልጆች ናቸው።እረኞች ማለዳ ላይ የየቤቱን ከብቶች ከባለቤቶቻቸው ቆጥረው በመረከብ ወደ ግጦሽ ካሰማሩቸው በኋላ አመሻሽ ላይ ተሰባስበው ወደየ ቤታቸው ይመለሳሉ።በዚህ ስራ ከተሰማሩት መካከል ዱባለች የሚከተለውን ዘፈን ዘፍናለች።

(139) Lani neese waallummo*4

Waasho'iiibado waallummo

Wio borinnee waallummo

Wo'iisa angoommo waallummo

እኛ የከብቶች እረኞች መጥተናል

የጥጆን ትኩስ ወተት ››

በቀጭኑ ፍንጭቃችን ››

እንደ ውሀ እንጠጣለን ››

(ዱባለች ፍቅሬ ፣የእረኝነት ስራ 29/06/2004 )

ዱባለች የከብት እረኛ መሆኗን በግጥሟ ገልፃለች።በገጠሩ አካባቢ ያሉ ላሞችና በሬዎች የየራሳቸው ስም አሏቸው።"ቀሾን ትኩስ ወተት"የሚለው ሀሳብ የሚያመላክተው የላሟ ስም "ቀሾ" መሆኑንና ወተት የምትታለብ መሆኗን ነው። በግጥሙ ውስጥ የእረኞቹም ጥርሶች ፍንጭት መሆናቸው፣እንዲሁም እረኞቹ ወተቱን በፍንጭት ጥርሶቻቸው እንደ ውሀ እንደሚጠጡ ምኞታቸውን ገልፀዋል።ከልምድ፣ ከባህል አንፃር የከብት እረኞች ሁል ጊዜ ወተትን ይፈልጋሉ።ከወተት ውጪ ሌላ ምግብ ወይም የሚጠጣ ነገር ሲሰጣቸው ስራቸውን እንደሚያቆሙ የከብቶቹ ባለቤት የሆኑት (ወ/ሮ አበራሽ ደስታ፣29/06/04) ተናግረዋል።በአንዳንድ አካባቢ የከብቶቹ ባለቤቶች ለእረኞቹ ጥጃን ወይንም ወይፈንን ይሰጧቸዋል ።ይህንንም የሚያደርጉት ልጆቹ ከከብቶቹ ጋር ያላቸውን ፍቅር ለማሳደግ ሲሉ ነው።እረኞቹ ወደ ከብቶቹ ባለቤት ቀዬ ሲቃረቡ ዱባለች የከብቶች ባለቤት የሆኑትን ቀሾን አልበው ወተቱን ለእረኞቹ እንዲሰጧቸው ለማነሳሳት መጣንላችሁ በማለት አዜማለች።

በገጠሩ አካባቢ በሬ ትልቅ ስፍራ ከሚሰጡት የቤት እንስሳት መካከል አንዱ ነው። አብዛኛው ጊዜ እርሻ በወንዶች ስለሚታረስ በሬና ወንዶች ቅርበታቸው ከሴቶች ይልቅ የሰፋ ሲሆን እንዲሁም በሬን የሚያበላው፣ የሚቀልበው ወንድ ልጅ ነው።እረኞች በአንድነት ሆነው የበሬውን ስለ ውበትና ጉብዝናን የሚገልፅ ዘፈን ዘፍነዋል።

(131)Mirgo'i saabbaamo

Moor dallichchaamo

Midaadi haraara

Mii'n woro axiso

Geejjee di'iree

በሬ ጉልበታሙ

ባለሻኛው ሰንጋ

ሰፊ ነው ጉኑ

ለቤት ግርማ ሞገስ

ስብ ሁን ወፍር እንቶስ

( አሚራ አሊ እና ሰዐር አሊ ፣እረኝነት ስራ ላይ፣23/06/04)

አቀንቃኞቹ በአንድ ላይ በመሆን በሬን ጉልበታም ፤ባለሻኛ በማለት የሙገሳ ዘፈን አዚመዋል፡፡‹‹በሬ ጉልበታሙ›› የተባለበት ምክንያት በሬ የእርሻን መሬት የሚያርሰው ባለው አቅም ፤ጥንካሬው በመሆኑ ነው፡፡ በሬውም ለቤት ግርማ ሞገስ መሆኑ በግጥሙ ተገልጿል፡፡በጥሩ እንክብካቤ የተያዘ በሬ መሆኑን የሚገልፁ ቃላት ሰንጋ እና ጎነ ሰፊ በመባል የተጠቀሱት ናቸው፡፡በሬውን ...ከምትሰራው ስራ አንፃር ስትታይ አንተስ ስብ ሁን፤ወፍር ይገባሀል በማለት አሞጋሽ ዘፈንን ዘፍነዋል፡፡አባቶቻችን ገበሬዎች ስለሆኑ ይህንን ዘፈን ይዘፍኑታል እኛም ከእነሱ የሰማነውን ዘፈን እንዘፍናለን ይህንንም ዜማ ስናዜም በሬውም ይሰማናል ደስም ይለዋል፡፡እኛም በዚህ እንዝናናለን፤የሳርግጦሽ ሜዳ ላይ መሆናችንን እንኳን እንድንረሳ ያደርገናል፡፡(ቃለ መጠይቅ ሰሀር አሊ እና አሚራ አሊ፤23/06/04)

የበሬውን አቅም አይበገሬነትን የሚያወሱና አድናቆትን አዘል መልእክቶች የተላለፉባቸው ዘፈኖች ተዘፍነዋል፡፡

(136) Biqee sagada

Biir haraar uulla

Baadulli qaroxaio

Binneessoo goonch o

ዳገትና ቁልቁለት፣

ለጥ ያለ መሬት

ድንገል መሬት፣

ጀግናው በታታኝ

ዘፋኞቹ የበሬውን አቅምና ችሎታ በዘፈናቻቸው ያመላከቱበት ነው፡፡‹‹ዳገትና ቁልቁለት ››የሚለው ስንኝ በሬውን የሚገጥሙት ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ በሬው ግን እነዚህን ተግዳሮቶች ሁሉ ማለፍ የሚችልና ጀግና መሆኑ በግጥሙ ተገልጿል፡፡እንዲሁም ‹‹ድንግል መሬት ››በማለት የተገለፀው ሀሳብ መሬቱም ከዚህ ቀደም ያልታረሰ ፤አስቸጋሪ ና ጠንካራ መሆኑን በምናባችን እንድናይ ያደርገናል፡፡ይሁንና የመሬቱም አስቸጋሪነት በበሬው ጀግንነትና ጥንካሬ መፍትሄ እንደሚያገኝ በዘፈኑ ተገልጿል፡

በመቀጠል አቀንቃኞቹ በሬው ባረሰው መሬት ምክንያት የሚከፈለውን ወሮታ የሚያወሱ ዘፈኖች ዘፍነዋል።

(137) Annii kiyyanni

Anga dabareenaa Er makk hixennee

Abooyyoomaaree Axo fatta' yitaattoto

እንኳን የኔ ሆንክልኝ

ለውለታህ ምላሽ በሳር ድርቆሽ

እንከባከብሀለሁ አደልብሀለሁኝ።

ይህ ዘፈን አረኞች ‹‹እንኳን የእኔ ሆንክልኝ ››በማለት የውስጥ ደስታቸውን ያንፀባረቁበት ነው።በሬው ባረሰው መሬት የተገኘው ምርት ትልቅ ጥቅም በማስገኘቱ ለበሬው የሚሆን ስጦታ ተዘጋጅቶለታል። የስጦታውም አይነት በግጥሙ ‹‹ሳር ድርቆሽ›› መሆኑ ተገልጿል።

ሰሀር እና አሚራ የበሬው ትልቅ እና ጠንካራ መሆን ያበረከተውን አስተዋፅኦ የሚያሳይ ዜማ አዜመዋል።

(134) Kadoo warjaamo

Kee maa'lli axxaqqa

Karaa miraanaa

Kaaboo wogala Karakkam heechcho

Ki gudumonnee Ki'isa goonchi ayyi

ማረሻ ሞፈር

ከበሬን ቀንበር

ምሬን አበር

ማሰሪያ ወገል፣የማሰሪያ ገመድ

ዋንተ ሜዳ ላይ ማን እንዳንተ ታጋይ።

አቀንቃኞቹ በዜማቸው የበሬ ጫንቃ ላይ የሚታሰሩትን ቁሶች በስማቸው ጠቅሰዋል፡፡ ‹‹ምራን›› የተባለው ቁስ ሞፈሩንና ቀንበሩን የሚያስተሳስር ከቆዳ የተሰራ ገመድ ነው፡፡ ወገል የተባለው ቁስ አገልግሎቱም ማረሻንና ሞፈሩን የሚያስተሳስር ሽቦ መሰል ማሰሪያ መሆኑን ዱባለች ፍቅሬና አርፋጨ ባቾሬ፣(22/07/04) ነግረውኛል፡፡ማረሻ ሞፈር፣ቀንበር፣ምራን እና ወገል የተባሉትን ቁሶች ሁሉ ተሸክመህ የተጣለብህን አደራ የምትወጣ እንዳንተ ማን አለ፡፡ አንተ ብዙ ሀላፊነትን የተጣለብህ ስለሆንክ ከአንተ በላይ ሀላፊነትን ሊሸከም የሚችል የለም የሚል እንድምታ አለው፡፡

በመቀጠል ለበሬው መልካም ምኞትን የሚገልፁ መልእክቶች በአቀንቃኞቹ ተቀንቅነዋል፡፡

(135) Gatee saaxee

Gadaanehoo liqqee

Goombbalii uulia fii'e

ከፋ አያግኝህ

ያሰበር ጠላትህ

ዳሊጋህ መሬት ይዳስ

ከላይ በተጠቀሰው ግጥም ውስጥ በሬው ጠላት እንዳለው ፣በክፉ ሊገኝ እንደሚችል ተገልጿል፡፡ የበሬው ጠላትና ክፉ የበሬው ባለቤት ጠላት የሆነ በሬውን የሚሰርቅ ሰው ነው፡፡ሌላው በሽታ እና የሰው አይን ናቸው፡፡ በሬውም ከእነዚህ በአንዱ እንዳይገኝ ወይም እንዳይነካ በማሰብ ስለበሬው ያላቸውን መልካም ምኞታቸውን በዜማ አቀንቅነዋል፡የበሬውም ጠላት እንዲሰበር ተረግሟል የበሬው ‹‹ዳልጋ›› መሬት እንዲዳስስ በረከትን ተባርኳል፡፡አቀንቃኞቹ ለበሬው ያላቸውን አመለካከት ወፍር፣ ስብ ሁን፣ ይመርብህ እያሉ በዜማቸው ምኞታቸውን አሰምተዋል፡፡

ሌላዋ አቀንቃኝ ደግሞ የሀድያ ብሄረሰብ ባህላዊ ዘፈኖችና ጭፈራዎች በምን ጊዜ እና በእንዴት ባለ ሁኔታ እንደሚዘፈኑ የሚያሳይ ገፅታ ያለው ዘፈን አቀንቅናለች፡፡

(143) Hiyyoyyo Hibbo'o lellimmi *2

Oosooma'nnanne Allaachchiballanne

Guuto'I ballanne

Geejji hadiyyi oosi

ሂዮዩ ሂዮ ዘፈን/ጨዋታ

በለጆነት በአረኝነት ቦታ

ቀንጮ በነበሩበት ወቅት

የትልቁ ሀድያ ልጆች

(አቶ ፊ ሮማኖ፣በአረኝነት ላይ ፣29/06/04)

በዚህ ግጥም ውስጥ ዘፈን በየትኛው አውድ እና በማን ሊባል እንደሚችል በግጥሙ ተጠቁሟል።የዘፈን አይነቶቹም ።ሂዮዮ እና ሂዮ ።መባላቸው ተገልጿል። የሀድያ ልጆችም በወንድ አቀራረባቸውም።ቀንጮ።በነበሩበት ዘመን ወይም ጊዜ ሂዮ እና ሂዮ የተባለውን ዘፈን በመዝፈን እንደሚጫወቱ በግጥሙ ተጠቅሷል።አቀንቃኟ ትላንቷን የምታስታውስበት ወይም የምታደበት ትዝታን የሚያጭር ዘፈንን ዘፍናለች።ከሁኔታዊው አውድ በመነሳት ዘፋኖቹ የሚዘፈኑት በትልቁ ሀድያ ልጆች መሆናቸው በግጥሙ ውስጥ ተገልጿል።

## 5.8 በውቀጣ ላይ የተዘፈኑ

አብዛኛውን ጊዜ በሀድያ ብሄረሰብ እንደ ገብስ፣ስንዴ፣በቆሎ ወዘተ የመሳሰሉትን የእህል አይነቶች በሙቀጫ የሚወቅጡት ሴቶች ናቸው።በወቀጣው አውድ ሁለት ሴቶች እየወቀጡ በመቀባበል የተለያዩ ግጥሞችን ሲያዜሙ ተሳታፊዎች በአቅራቢያው በመሆን በጭብጨባ ስራቸውንና ዘፋኖቹን ያጅባሉ።

(155) Hadiyyi sum weeshiso

Anim kuroom keemaal miroore

Malayyam hadiyyi anim kuroomo

የሀድያን ስም የምታስጠራ

የማደንቅህ ትልቁ ምሮሬ

ሀይለኛ መሆንህን ለሰው መስከሬ

(ትእግስት አርሞና፣ ደመቀች ደሁኔ ፣ወቀጣ 24/06/04 )

በወቀጣ አውድ ላይ አቀንቃኞቹ የዌራ ልጅ የሆነውን ወንድማቸውን በማሞገስ ትልቅነቱን እና ጀግንነቱን በዘፈናቸው ውስጥ አስምተዋል ።ትእግስት የሀድያን ብሄረሰብ ስም የምታስጠራ ነህ በማለት እኔ አደንቅሀለሁ ትልቁ ሞሮሬ ነህ የአንተን ጉብዝናና ጥንካሬ ለሰው እመሰክራለሁኝ እያለች ምኞቷን ትገልፃለች፡፡

ቀጥሎም አቀንቃኞቹ በመቀባበል የሚከተለውን ቃል ግጥም አዚመዋል፡፡

(150) AbbaaY Abbaay

Sure aam gooncho

Weere'o oosichcho

Wit kulleel landbeeto

Koemmaal Sullibeeto

ወንድሜ ወንድሜ

ስራ የታጠቅከው

የዌራ ልጅ ነህ

የዊት ሰፈር ልጅ ነህ

የትልቅ ዘር ልጅ ነህ

አቀንቃኞቹ ወንድማቸውን ተራ በተራ ወንድሜ ወንድሜ በማለት የሚሰማቸውን ስሜት በዘፈኖቻቸው አንፀባርቀዋል፡፡አቀንቃኞቹ ወንድማቸው ጎበዝ መሆኑን ለመናገር ያመላከቱበት ፡፡ስራ የታጠቅከው ፡፡በማለት ያዜሙት ስንኝ ነው፡፡አቀንቃኞቹ በዘይቤ የገለፁት ቃል ወንድማቸው ስለሚለብሰው ስራ ሳይሆን ስለ ወንድማቸው ጀግንነት እና ጉብዝና ነው፡፡በዚህ አውድ ፡፡ስራ፡፡ የሚለው ቃል የጀግንነት ተምሳሌት ነው፡፡በመቀጠል ወንድማቸው ከዌራ ጎሳ የተወለደ መሆኑን ይናገራሉ፡፡፡ዌራ፡፡የሀድያ ብሄረሰብ አንዱ ጎሳ

ነው።(ቃለመጠይቅ፣ትዕግስት፣24/06/04)። ‹‹ዊት›› የትግል ቦታ ሲሆን አባቶች ታግለው ያሸነፉበት ስፍራ ነው።በመሆኑም አቀንቃኞቹ ወንድማቸው የተወለደበትን አካባቢ እና ጎሳ አስታውቀዋል።በዚያ አካባቢ የተወለዱ ልጆች የትልቅ ዘር ልጆች ስለሆኑ አንተም የትልቅ ዘር ነህ እያሉት አዚመዋል።በአንፃሩ እነርሱም ትልቅ ወይም ስመ ጥር ከሆነ ዘር እንደተወለዱ በዘፈናቸው ገልፀዋል ።

## ማጠቃለያ

የጥናቱ አላማ የሀድያ ሴቶች በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎቻቸው ላይ የሚዘፍኗቸውን ዘፈኖች በፅሁፍ፣ በምስልና በድምፅ ቀርፆ ማስቀመጥ ሲሆን፣ጥናቱም ተተኳሪ ያደረጋቸው የሴቶች የስራ አጋጣሚዎች ወተት መናጥ፣ሙቀጫ መውቀጥ፣ስንደዶ ለቀማ፣እረኝነት፣እንሰት መፋቅ፣ወፍጮ መፍጨት፣የጓሮ አትክልቶችን መኮትኮት፣እንጨት ለቀማ ናቸው።ይህም ማለት የሀድያ ሴቶች በመስክም ሆነ በቤት ውስጥ የሚሰሯቸው ስራዎች እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት አይደለም።

ትንታኔው ቃልግጥሞቹ በተነገሩበት አውድ ፣በምልከታና በቃለመጠይቅ ስልቶች ላይ ሊያተኩር እንዲሁም ከማህበራዊ እና ከግለሰባዊ አውዶች አንፃር ተተንትኗል።በተጨማሪም የስራዎቹ የአከዋወን ሂደት ምን እንደሚመስል እና ባዜሟቸውም ዘፈኖች ውስጥ ምን ምን ጉዳዮች እንደተነሱ በጥናቱ ተገልጿል።

ሴቶች በዘፈኗቸው ዘፈኖች ውስጥ የመጡት ጉዳዮች እና ከቃል መረጃ ሰጪዎቹ ያገኘሁት መረጃ ከነዋኔው በበለጠ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ በተለይም ሴቶች በመሆናቸው በማህበረሰቡም ሆነ በባሎቻቸው ተቀባይነትን የማያገኙባቸውን ጉዳዮች በዘፈኖቻቸው በማንሳታቸው አጋጣሚው ጥሩ መቼቶች እንደሆኑላቸው በጥናቱ ተረጋግጧል።

በስራቱም ወረዳዎች ሴቶች ካዜሟቸው ስንቃሎች መካከል ገሚሶቹ ከስራው አይነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ናቸው።ገሚሶቹ ደግሞ ከስራው አይነት ጋር ምንም ተያያዥነት የሌላቸው መሆናቸው በጥናቱ ተረጋግጧል።

ትምህርት፣ስራ፣ጨዋታ ለሰው ልጅ እድገት ወሳኝ መሆናቸው በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎች ላይ ተደጋግመው ተዚመዋል።ስራን መስራት እንደሚያስከብር በአንፃሩ አለመስራት ደግሞ እንደሚያዋርድ በግጥሞቹ ውስጥ ተገልፀዋል።እንዲሁም የሀድያ ሴቶች በቡድን የመስራት ባህል እንዳላቸው በጥናቱ ተገልጿል።የሴቶች የቡድን ስራ መጠሪያቸውም ጌጃ፣ጉላና ዋጃ በመባል ታውቋል።

በሀድያ ብሄረሰብ የአኗኗር ዘይቤ የቀን እንቅልፍ እንደ ትልቅ አስነዋሪ ነገር ተደርጎ መቆጠሩ በጥናቱ ተጠቁሟል።ከዚሁ ጋር ተያይዞ በብሄረሰብ ልማድና ስርአት መሰረት ሴቶች ስራቸውን ከመጀመራቸው በፊት ፈጣሪያቸው ከቀን እንቅልፍ እንዲጠብቃቸው በተደጋጋሚ በተለያዩ ዘፈኖቻቸው ጠቁመዋል።

ሴቶቹ በስራ አጋጣሚዎቻቸው ጊዜ ዘፈኖችን የመዝፈናቸው ምክንያት የስራውን አድካሚነት ለመርሳት ፣ በስራ የደከመውን አካላቸውን ና መንፈሳቸውን ለማበረታታት ፣እንዲሁም በዘፈኑ እንደሚዝናኑ ና እንደሚደሰቱ በጥናቱ ተገልጿል።

የሀድያ ሴቶች በባህላዊ ወፍጮ እህልን ሲፈጩ እና ወተት ሲንጡ የዘራቸውን ሀረግ በማንሳት እንደሚያዜሙ ተስተውለዋል። አንድ ሰው የሀድያ ተወላጅ መሆኑንም ወይም የዘር ሀረጉ ሀድያ መሆኑን የሚያውቁበት መንገድ በስራ አጋጣሚዎች ላይ በሚዘፈኑት ዘፈኖች አማካይነት መሆኑ በጥናቱ ተገልጿል።

ሴቶች በተናጥል ወይም በቡድን ሆነው የሚከውኗቸው ስራዎችም ሆኑ የሚያዜሟቸው ዘፈኖች የተለያዩ ናቸው። አብዛኛውን ጊዜ በተናጥል ሆነው ከሚሰሯቸው ስራዎች መካከል እንዱ ወፍጮ መፍጨት ሲሆን በዚህ የስራ አጋጣሚ ላይ የሚያዜሟቸው ዘፈኖች ስለ ግል ህይወታቸው ፣ስለ ልጆቻቸውና ስለ ባሎቻቸው የሚናገሩ ሲሆኑ በቡድን ሆነው በሚከውኗቸው የስራ አጋጣሚዎች ላይ ደግሞ የማህበረሰቡን ባህል፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁነቶች የሚያሳዩ ናቸው።

በአጠቃላይ በሀድያ ብሄረሰብ የሚዜሙት ስንኞች በዘመኑ የነበሩትን ሁነቶች ለተተኪው ትውልድ አሻራን ብቻ ጥለው የሚያልፉ ሳይሆኑ አሁን ላይ ትላንትናን እና ነገንም የሚያሳዩ መስታወቶች ናቸው።በተጨማሪም ሴቶቹ በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎቻቸው ላይ ያዜሟቸው ቃል ግጥሞች ማህበረሰቡ ያለበትን የኑሮ ደረጃ ፣ዘመኑን እንድናስብ እና የማህበረሰብ የኑሮ ሁኔታ ወደፊት እያመራ እንዳለ ይጠቁሙናል።

ሌቶቹ በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎቻቸው ላይ የሚያዜሟቸው ስነቃሎች ቅርሶች እንደመሆናቸው መጠን የአካባቢው ነዋሪዎች ለአጥኚዎች መረጃ በመስጠት እና ቃል ግጥሞቹን ለመከወን ፈቃደኞች ቢሆኑ፣እንዲሁም የዞኑ አስተዳደር እና ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች በስራ አጋጣሚዎቹ ላይ የሚባሉትን ቃል ግጥሞች በወጉ ለመሰብሰብና ለማስተመጥ የተቻላቸውን ያህል ጥረት ቢያደርጉ መልካም ነው እላለሁ።

## የአማርኛ ምንጮች


ኻውል በቀለ። ‹‹የሀድያ ወጣቶች የከንፈር ወዳጅ የዘፈን ግጥሞች ጥናት ››አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሁፍ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1989 ዓ.ም።

ብርሀኑ አሳዬ። ‹‹በባንጃና በአንካሻ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች በአዊኛ የሚያዜሟቸው የስራ ላይ ዘፈኖች ጭብጥ ገለፃና ትንተና››ለኢትዮጵያ ስነፅሁፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሁፍ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999 ዓ.ም።

በተለያዩ የሀድያ ምሁራን የተዘጋጀ ።የሀድያ ብሄረሰብ በቋንቋ፣ በታሪክ፣ በባህልና በስነ-ቃሎች ላይ የተደረጉ ጥናቶችን የያዘ መፅሀፍ።ሆሳዕና፣1998/2006ዓ.ም።

አስቴር ሳሙኤል፡፡‹‹የሀድያ ብሄረሰብ የዘፈን ግጥሞች ››ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሁፍ ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1974 ዓ.ም።

አዳነ ኩሳ፡፡‹‹የሀድያ ሴቶች በቡድን በሚከውኗቸው ተግባራት ላይ የተመሰረተ ቁሳዊ ባህል ጥናት›› ለኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለ ኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሁፍ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣2002 ዓ.ም።

አመነ ወርቁ፡፡ ‹‹በቸሃ አካባቢ የሴቶች የስራ ላይ ግጥሞች ይዘት ትንተና››ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሁፍ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1993 ዓ.ም።

አለባቸው ኬሰምሶ እና ሳሙኤል ሀንዳሞ ።የሀድያ ህዝብ ታሪክና ባህል።ሰፊር አታሚ
አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ፣2002 ዓ.ም።

ዘሀራ ሰይድ። ‹‹የጾሲ ዙሪያ ሴቶች የስራ ላይ ግጥሞች ይዘት ትንተና››ለኢትዮጵያ
ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ
ፅሁፍ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1992 ዓ.ም።

ዘሪሁን አስፋው።የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን።አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣1992
ዓ.ም።

ዮሀንስ አግደ።፡‹‹የልማት ፅንስ ሀሳብና አካባቢያዊ የልማት ስራ እንቅስቃሴዎች››በሀድያ
በሀድያ ህዝብ ቋንቋ ታሪክ ባህልና ስነ ቃሎች ሲምፖዚየም ላይ የቀረበ፣
ሆሳዕና፣1997 ዓ.ም።

ዮኒ አለም አረዶ ። ‹‹የጥቼ አካባቢ ሴቶች የስራ ላይ ግጥሞች ይዘትና ትንተና››ለኢትዮጵያ
ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሁፍ፣
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1997 ዓ.ም።

ፈቃደ አዘዘ ። የስነቃል መምሪያ። አዲስ አበባ ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት ፣1991ዓ.ም።

## የእንግሊዝኛ ምንጮች


Barry,Phillips."Some Aspects of Folk Song."Journal of American Folklore,1987.

Braukamper.U."The Correlation of Oral traditions and Historical Records in Southern Ethiopia."ACase study of the Hadiya/Sidamo past Journal Ethiopian Studies,Vol.Xi,Haile sellase University Institute of Ethiopian Studies,1973

Braukamper,U and Tilahun Mishago , Praise and Teasing.Narrative Songs of The Hadiya in Southern Ethiopia.Frankfurt: Forbenius Institute,1999.

Bauman,Richard.<<The Field of Folklore in Context.>>A Hand book of American folklore.Ed.Richard M.Dorson,1983.

Ben-Amos,Dan. Folklore in Context.South Asian Publishers: New Delhi, Madres, 1982.

Dundes Alan."The Study of Folk Lore Englewood Cliffs,N.J.:Prentice-Hall.Inc. 1965.

Finnegan,Ruth.Oral Literature in Africa.Nairobi:Oxford University Press,1970.

Fekade Azeze "The State of Oral literature Research in Ethiopia,retrospect And Prospect."Journal of Ethiopian Studies 2001.

Gedion Addis."A Socio-Economic and Cultural History of The Hadiyya 1941-1991"Fulfilment of the Requirements for the degree of Mast

Ers of Arts in History,2008.

Goldsteine,J. Kenneth.A Guide for Field Workers in Folklore.Pensylvania: hat Boro,Folklore Associates,Inc,1964.

Haile Bubamo Arficho."Some Notes on the Traditional Hadiya Women"Ethio Pian Studies,Vol.xx.No 2. Haile Sellase University: Institute of Ethiopian studies,1973.

*http://www.texas.edu/courses/stross/ant 393b files/Articles/Identity.pdf.*

Lewis P.Hinhman and Sandra K.Hinchman .The Idea of Narative in the Human Science .University of New York Press, Albany 2001.

Leach,Maria .Standard Dictionary of Folklore Mythology and Legened .New York, 1949.

Kumar,Ranjit.Research methodology:A step by step Guide for Bingers. London:SAGE publication Ltd,1996.

LewisP.Hinchman and Sandra K.Hinchman.The Idea of Narative in the Human Science .State University of New York Press,Albany,2001.

Martha c.sims. Living folklore:Utah State University Press, Logan ,Utah 2005.

MacDonald. A.<<Field Work Collection in Oral literature.>> folk life: An Intro-Duction.Ed Richard Dorson Chicago: University of Chicago Press,1972.

Okpewho,Isidore.African Oral Literature;Back Grounds, Character and Conti

Nulty.Blooming: Indiana University press,1992.

*WWW.echt.chm.msu.edu/blockiii/Docs/../B3CCLancetDescStudies.pdf*

*W.http://en.wikipedia.org/wiki/Identity formation pdf.*

Trask .William R.(ed). The Unwritten Song.New York: The macmillan Compa

Ny,1966.

አባሪ 1

## ከተለያዩ የስራ እውዶች ላይ የተሰበሰቡ ዘፈኖች ዝርዝር

### በእንሰት ፍቅት ላይ የተዘፈኑ

| | |
|---|---|
| 1.Weesaa ororoo | እንሰት እሹሩሩ |
| Weeshshichcho ororoo | የኔ እንሰት እሹሩሩ |
| Uu'ini lobane | ኡእን ከሚባል እንሰት |
| Uunjammi lobane | ኡንጀማ ይሻላል ለወንድ |
| A'mmichchi bishashane sirbo'l lobane | እሚቾ ደርቦ ይሻላል |
| Weesa ororoo | እንሰት እሹሩሩ |
| Weeshshichcho ororoo | የኔ እንሰት እሹሩሩ |
| | |
| 2 Koyya gassookkok xororaam | ጦሮራ ለእንግዳ እራት የሚሰጥ |
| Kokka kanookkok disho'l lobane | ዲሾ በደረቅ መሬት ሚበቅለው |
| Abeet abet | አቤት አቤት |
| | |
| Annichchi iltoo oradam | አባወራው የሚወደው ኦራዳ |
| Meenti sabookkok gishiraam | እማወራዋ ምትጠላው ግሽራ |
| Goon iltokkok astaram | ወንድ የሚወደው አስተራ |
| | |
| 3. Duuggaano kaa'aa gassoo qalima | አሸንፎ ፋቲዎችን |
| Dakkaano kaa'aa | ለጀባ እንጣፊዎች |
| Dahakku'uuyyi garakkam mine | እንግዳ የሚበዛበት |
| Weesa ororoo *4 | እንሰት እሹሩሩ*4 |

| | |
|---|---|
| (4) Gibbi wotta'lli'n | እንደ አውራረስ ልጆች |
| Gojo'I woronne | በቆሎው ጉድጓድ |
| Gii'mmamoo bu'o | የተኛው ቡላው |
| Weesa ororoo *4 | እንስት እሹሩረ*4 |
| Weeshshichcho ororoo | የኔ እንስት እሹሩሩ |
| | |
| (5) Hawwaa'n qaraare | የችግረኞች መድሀኒት |
| Hoongaa'n lubato | የደካሞች ዋስ |
| Hiimina ballina | ለቀንና ማታ |
| Haabaam hurbaata | ወደር የለሽ ምግብ |
| Weesa ororoo *4 | እንስት እሹሩሩ*4 |
| | |
| 6. Ka weeshshichchikk | ለዚህ እንስት |
| Kurakkam luwwi | የሚነገርለት |
| Kumaa kaakumaa | ከቁጥር በላይ ነው |
| | |
| 7. Ta'llomo hibongoo*2 | ሂቦንጎ ልጫወት ሂቦንጎ |
| Ta hadiyyoosi landahibongoo | የሀድያ ሴቶች ሂቦንጎ |
| Barxaa inteena hibongoo | ሂቦንጎ ስርተን እንበላለን |
| Balli inso waa'ihoore hibongoo | ከቀን መኸታ እግዜር ይጠብቀን |
| | |
| 8.Leilimma taa korii leile hibongo | ተራ በተራ እንጫወት |
| Leiloo losanoo hibongo | ጨዋታና ትምህርት |

| | |
|---|---|
| Lamom langoommo hibongo | ሁሉቱንም እንችላለን |
| 9.Gundi woraadanne hibongo | በአሜጭር ወንዶች ላይ |
| Geesho'o tumoommo hibongo | ጌሾ እንወቅጣለን |
| Ayya'l landichi kuroommo hibongo | እኔ የሴትየዋ ልጅ |
| Ana'l kuroomo lelloommo | እሜወታለሁኝ |
| | |
| (10)Garooyyo garooyyo | የምንፍቀው እንስት አያሸንፈንም |
| Meco'l garooyyo ahaa | እንዱም ሳይተርፍ ሁሉን እንፍቃለን |
